NMA ብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ
NATIONAL METEOROLOGY AGENCY

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ



# የሁለተኛው የአምስት ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና የአፈጻጸም ግምገማ
(2008-2012)

ግንቦት 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ

## የሁለተኛው የአምስት ዓመት
## የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ
## እና የአፈጻጸም ግምገማ (2008-2012)

ግንቦት 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## Contents (ይዘት)


የዋና ዳይሬክተሩ መልዕክት ........ Vii
መግቢያ ........ 1
የተቋሙ ርዕይ፣ ተልኮ እና ዕሴቶች ........ 3

**ክፍል አንድ** ........ 4

**1.** የመጀመሪያው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም ........ 4
1.1. የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች አውታር ዝርጋታ አፈፃፀም ግምገማ ........ 4
1.1.1. የገፀ-ምድር የመረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች ዝርጋታ አፈጻጸም ........ 4
1.1.2. ዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ የመረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች ዝርጋታ አፈጻጸም ........ 6
1.2. ዘመናዊ የመረጃ አቅርቦትና ስርጭት አፈፃፀም ........ 7
1.3. የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የምክር አገልግሎት አፈጻጸም........9
1.3.1. የሚቲዎሮሎጂ የትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስራዎች........ 9
1.3.2. የልማት ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ........10
1.3.3. የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ........11
1.4. የሰው ሀብት ልማትና የአቅም ግንባታ አፈጻጸም ግምገማ ........12
1.5. የባለ ብዙ ዘርፍ ስራዎች አፈጻጸም ........ 14
1.5.1. የሴቶች ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፡፡ ........14
1.5.2. የአረንጓዴ ልማት ትግበራ አፈጻጸም ........14
1.5.3. የኤጀንሲው አገለግሎትን የማስተዋወቅ፣ የገፅታ ግንባታ እና ኮሙኒኬሽን ስራዎች ........16
1.5.4. የለውጥ ስራዊት ግንባታ እና የመልካም አስተዳደር ስራዎች አፈጻጸም ........16
1.6. የበጀትና ፋይናንስ አፈጻጸም ........ 19
1.7. የክትትል እና ግምገማ ስርአት፣ጥንካሬዎች እና ድክመቶች እንዲሁም ያጋጠሙችግሮች ........ 19
1.7.1. የእቅዱ የክትትል እና ግምገማ ስርአት፣ ........ 19
1.7.2. በእቅድ ትግበራው ሂደት የነበሩ ጥንካሬዎች፣ ........ 19
1.7.3. በእቅድ ትግበራው ሂደት ያጋጠሙ ድክመት ........ 20
1.7.4. ያጋጠሙ ችግሮች ........ 20

**ክፍል ሁለት** ........ 22

**2.** የሁለተኛው ዕድገትና ትራስፎርሜሽን ዕቅድ........ 22
2.1. የሁለተኛው ዕድገትና ትራስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻ ሁኔታዎች ግምገማ ........ 22
2.1.1. ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ........ 22
2.1.2. ሀገራዊ ሁኔታ ........ 25
2.1.3. የበጀት ወይም ፋይናንስ የማፈላለግ (Resource Moblization) ሁኔታ ........ 27
2.1.4. የውስጣዊ (ጥንካሬዎች እና ድክመቶች) እና ውጫዊ ሁኔታ (ምቹ ሁኔታዎችና ስጋቶች) ትንተና ........ 28
2.2. የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓላማዎች ........ 31

2.3. የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች ..............................31

2.4. የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫዎች ............... 33
2.4.1. ጥራቱን የጠበቀ ደንበኛ ተኮር የመሰረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አቅርቦት ..... 33
2.4.2. አስተማማኝ የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና የምክር አገልግሎት ........................................................................................ 33
2.4.3. በጥናትና ምርምር የዳበረ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ......................................... 33

2.5. የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ምሰሶዎች (Pillars) ....................... 34
2.5.1. የመረጃ አቅርቦት ሽፋን፣ጥራት እና ተደራሽነትን ማረጋገጥ ................................ 34
2.5.2. የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አገልግሎትን ተደራሽ ማድረግ ........................................................................................ 36
2.5.3. የልማት ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ማሻሻል ............................................... 36
2.5.4. ውጤታማ የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መስጠት ............................. 38
2.5.5. ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ስራዎችን መተግበር ............................................. 39
2.5.6. ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ በማዋል የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት አሰጣጥን ማሳለጥ..... 41
2.5.7. የሰው ሃብት ልማት ና የማስፈጸም አቅም መገንባት .......................................... 44
2.5.8. የሪፎርምና መልካም አስተዳደር ስራዎችን መተግበር ........................................ 45
2.5.9. ዘርፈ ብዙ (የወጣቶችና ሴቶች ተጠቃሚነት ማረጋገጥ) ...................................... 45
2.5.10. የአረንጓዴ ልማት ትግበራ ዕቅድን ማሳካት ........................................................ 46
2.5.11. ኮሙኒኬሽን እና የተቋሙን በጎ ገጽታ መገንባት ................................................. 47

2.6. የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መርሀ ግብር ............................... 48
2.6.1. የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ዝርጋታ እና መረጃ አቅርቦት ጥራትና ተደራሽነት ማረጋገጥ ዕቅድ ........................................................................................ 48
2.6.2. የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ዕቅድ ..... 53
2.6.3. የልማት ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ዕቅድ ............................................................ 55
2.6.4. የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ................................................................... 56
2.6.5. የጥናትና ምርምር ሥራዎች ............................................................................... 57
2.6.6. ሰው ሃብት አስተዳደርና ልማት ........................................................................ 58
2.6.7. የለውጥ ሠራዊት ገንባታ ዕቅድ ...................................................................... 64
2.6.8. ዘርፈ ብዙ (የወጣቶችና ሴቶች ተጠቃሚነት ማረጋገጥ) ...................................... 66
2.6.9. ዕቅድን ለማስፈፀም የሚያስፈልግ የፋይናስ ፍላጎት ............................................ 69

**ክፍል ሶስት** ........................................................................................................ **66**

**3**. የሁለተኛው ዕድገትና ትራስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ .............................71
3.1. የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች አውታር ዝርጋታ አፈፃፀም ግምገማ ......................... 71
3.1.1. የገፀ-ምድር የመረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች ዝርጋታ አፈጻጸም ............................71
3.1.2. ዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ የመረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች ዝርጋታ አፈጻጸም........... 73
3.1.3. ዘመናዊ የመረጃ አቅርቦትና ስርጭት አፈፃፀም ....................................................75
3.2. የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የምክር አገልግሎት አፈጻጸም ...77
3.2.1. የሚቲዎሮሎጂ የትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስራዎች ......................................78
3.2.2. የልማት ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የ2ኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም ........................................................................................ 79

3.2.3. የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የ2ኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም ............ 82

3.3. የሚቲዎሮሎጂ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት 2ኛው ዕትዕ አፈጻጸም ............ 84

3.4. የሰው ሀብት ልማትና የአቅም ግንባታ አፈጻጸም ግምገማ ............ 84

3.5. የባለ ብዙ ዘርፍ ስራዎች አፈጻጸም ............ 87
3.5.1. የሴቶች ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ............ 87
3.5.2. የአረንጓዴ ልማት ትግበራ አፈጻጸም (የአካባቢ ጥበቃ) ............ 87
3.5.3. የኤጀንሲው አገለግሎትን የማስተዋወቅ፣ የገፅታ ግንባታ እናኮሙኒኬሽን ስራዎች ............ 89
3.5.4. የለውጥ እና የሪፎረም ስራዎች አፈጻጸም ............ 90

3.6. የዓለም አቀፍ ትብብር እና ግንኙነት ስራዎች ............ 92
3.6.1. ከሀገራት ጋር የተደረጉ የሁለትዮሽ ትብብሮች ............ 93
3.6.2. ከልማት አጋሮች ጋር የተደረጉ የብዘሀ ዘርፍ (Multilateral cooperation) ትብብሮች ............ 96
3.6.3. አህጉራዊ እና ቀጠናዊ የትብብር መስኮችን በተመለከተ ............ 97
3.6.4. ከዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት ጋር የተደረጉ ትብብሮች ............ 98

3.7. በጀትና ፋይናንስ አፈጻጸም ............ 100

3.8. የክትትል እና ግምገማ ስርአት፣ ጥንካሬዎች ድክመቶች እና ችግሮች............ 100
3.8.1. የእቅዱ የክትትል እና ግምገማ ስርአት፣ ............ 100
3.8.2. በእቅድ ትግበራው ሂደት የነበሩ ጥንካሬዎች፣ ............ 100
3.8.3. በእቅድ ትግበራው ሂደት የነበሩ ድክመት ............ 101
3.8.4. ያጋጠሙ ችግሮች ............ 101

# በሰነዱ ውስጥ የሚገኙ ምስሎች ዝርዝር


ምስል 1 ዓለም አቀፍ የሚቲዎሮሎጂ ጣብያዎች ገፅታ ........ 4

ምስል 2 የሳይኖፕቲክ ጣቢያዎች ለአለም አቀፍ መረጃ ልውውጥ የሚውሉ ........ 5

ምስል 3 የተላያዩ ደረጃ ያላቸው የገጸ ምድር ጣቢያዎች ስርጭት በኢትዮጵያ ........ 6

ምስል 4 በዓለም አቀፍ የአውሮፕላን ጣቢያዎች የሚገኙትን Automatic Weather Observing System (AWOS) ........ 7

ምስል 5 የኤጀንሲው የመረጃ አርካይቭ እና ኪላይ ዳታ ሶፊትዌር ........ 8

ምስል 6 የኤጀንሲው የአጭር ጊዜ የአየር ሁኔታ ትንበያ ማሰራጫ መንገድ (ዌብሳይት)........ 9

ምስል 7 በልማት ሚቲዎሮሎጂ የግብርና እና የውሃ ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ........10

ምስል 8 የኢትዮጵያ አየር መንግድ ዓለምአቀፍ እና የሀገር ውስጥ በረራ ስርጭት ........11

ምስል 9 በተለያዩ ጊዜ የተሰጡ የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎች በከፊል ........13

ምስል 10 የኤጀንሲውን አገልግሎት በተለያዩ ሚዲያዎች የማስተዋወቅ ሥራ........16

ምስል 11 በለውጥ ስራዊት ግንባታ እና የመልካም አስተዳደር ዙሪያ የተሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ........ 18

ምስል 12 የኤጀንሲው የበጀትና ፋይናንስ አፈጻጸም ........ 19

ምስል 13 ዓለም አቀፋዊ ትብብሮች ........ 22

ምስል 14 ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የልማት አጋሮቻችን ........ 27

ምስል 15 ከተለያዩ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች በከፊል ........ 71

ምስል 16 የአዳማና ሀዋሳ የአየር ብክለት መከታተያ ጣቢያ ምረቃ ........ 74

ምስል 17 የትንበያና የምክር አገልግሎት ........ 77

ምስል 18 ከሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች ........ 79

ምስል 19 ከምስል 15 ጋር ተመሳሳይ ........ 81

ምስል 20 የኤጀንሲው የሰው ሀይል ........ 85

ምስል 21 በተለያየ ምክንያት ከኤጀንሲው የለቀቁ ........85

ምስል 22 የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ........ 88

ምስል 23 በተለያየ ጊዜ የተሰጡ መግለጫዎች ....89

ምስል 24 የቦሌ የሚቲዎሮሎጂ ዘመናዊ ህንፃ የማስገንባት ሂደት .... 91

ምስል 25 የተለያዩ ዓለም አቀፋዊ ትብብሮች በከፊል .... 93

ምስል 26 ዓለም አቀፍ መድረኮችና ግንኙነቶች በከፊል .... 94

ምስል 27 ዓላም አቀፋዊ ትብብሮች .... 95

ምስል 28 ከተለያዩ የልማት አጋሮች ጋር የተደረጉ ውይይቶች .... 96

ምስል 29 የተለያዩ ዎርክሾፕና የአንድነት ፓርክ ጉብኝት .... 98

ምስል 30 የዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት የአፍርካ አህጉር ጽ/ቤትን በኢትዮጵያ የማስጀመር ሂደት .... 99

ምስል 31 በሁለተኛው ዕትዕ ዓመታት ለኤጀንሲው የተፈቀደ በጀት....100

## በሰነዱ ውስጥ የሚገኙ የሰንጠረዥ ዝርዝር

ሰንጠረዥ 1 ውስጣዊ ጠንካራ እና ደካማ ጎን .... 28

ሰንጠረዥ 2 ውጫዊ ምቹ ሁኔታዎችና ስጋቶች .... 29

ሰንጠረዥ 3 በኤጀንሲው የተቋቋሙ የጣብያዎች ሽፋን .... 49

# የዋና ዳይሬክተሩ መልዕክት



አቶ ፈጠነ ተሾመ

የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር

ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የመጀመሪያውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን በተሳካ ሁኔታ በመከናወን ለሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻ የሚሆኑትን በመለየት ጉድለቶች ታርመው በጥንካሬ የሚታዩት የእቅዱ አካል እንድሆኑ ተወስዶዋል፡፡ በዚህም መሰረት በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎረሜሽን እቅድ ዘመን በሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ዝርጋታ፣ በዘመናዊ መረጃ አቅርቦትና ስርጭት፣ በሚቲዎሮሎጂ ትንበያና ቅድመ-ማስጠንቀቂያ አገልግሎት መሻሻል፣ በአቅም ግንባታ ዘርፍ፣ የኤጀንሲውን አገልግሎት ለማስተዋወቅ በተከናወኑ የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ተግባራት… ወዘተ እመርታዊ ለውጥ በታየበት መልኩ ተከናውኗል፡፡ ይኸው የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም በየደረጃው በጥልቀት የተገመገመ ሲሆን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ተለይተው ለሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መደላድልና ምቹ ሁኔታ በመሆን ጠቀሜታው በጉልህ እየታየ ነው፡፡

በአንደኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ኤጀንሲው ራዕዩንና ተልዕኮውን ወደ ኅብረተሰቡ ለማስረጽና የሚቲዎሮሎጂን ጠቀሜታ በተለይም ለግብርናው፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለውኃ ልማት፣ ለጤና፣ እንዲሁም ለኅብረተሰቡ ሕይወትና ንብረት ከአደጋ መጠበቅ የጎላ አስተዋጽዖ ማድረጉ በዋነኛነት የሚጠቀስ ሲሆን፣ ከየሴክተሮቹ ጋር ያለው መስተጋብርም መሻሻል ማሳየቱ በዋነኛነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ከዚህም በላይ በተለይ ዘመናዊ ሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎችን በማቋቋም ረገድ በኤጀንሲው ታሪክ ውስጥ አስደናቂ ውጤት የተመዘገበበት ሆኖ አልፏል፡፡

ይህንን በአንደኛው የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተገኙትን ስኬቶች በግብዓትነት በመያዝ ሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በማዘገጀት በእቅዱ ዘመን መጀመሪያ ወደትግበራ የተገባ ሲሆን ከ መጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የተገኘውን መልካም ተሞክሮ በማስፋት በዕቅዱ ዘመን እጅግ በጣም አበራታች ውጤቶች ተመዝግቦዋል፡፡፡ የሁለተኛው ዕትዕ በተለይ በየክልሉ ያሉትን የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላትን በማጠናከር፣ በየደረጃው የሚገኘውን ባለሙያ የሙያና የክህሎት ማሻሻያ ሥልጠናዎችን በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ በመስጠት የተሻለ ስኬት የማስመዝገብ ስራዎች ተከናውኖዋል፡፡ በየክልሎቹ የሚቋቋሙትን የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ኅብረተሰቡ ራሱ በባለቤትነት እንዲይዛቸው የግንዛቤ ማስጫበጫ ስራዎች በመከናወናቸው በሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ላይ የሚደርሰው ውድመትና ስርቆትን መቀነስ ተችሎዋል፡፡ የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዋነኛ ዓላማ፡- አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ለኅብረተሰቡ ለማዳረስና አገራችን ከአየር ሁኔታና ጠባይ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የተፈጥሮ አደጋ ተጋላጭነትን መቀነስ፣ የሀገሪቱን መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ እና የአየር ሁኔታ ተለዋዋጭነት በሚገባ የሚወክል ዘመናዊና አውቶማቲክ የሆኑ መረጃ የሚሰበሰብባቸውን የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መረብ ማስፋፋትና ማስተዳደር፣ መረጃ በመሰብሰብ፣ በማደራጀት፣ በመተንተንና ጥራቱን በማረጋገጥ ሁሉም ተጠቃሚ በቀላሉ እንዲያገኝ ማድረግ፣ በተጨማሪም ደረጃውን የጠበቀ አስተማማኝ የአየር ሁኔታና ጠባይ የትንበያና ቅድመ-ማስጠንቀቂያ እንዲሁም ዘርፍ-ተኮር የምክር አገልግሎት መስጠት በዋነኛነት ተጠቅሰዋል፡፡



በመሆኑም ኤጀንሲው የውስጥ አሠራሩን እያሻሻለና የፈጻሚውን ብቃት እያጎለበተ በተጨማሪም የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነቱን እያዳበረ ከአንደኛው ዕትዕ አፈጻጸም ባገኘው ተሞክሮ ላይ በመንተራስ ሁለተኛውን የእደገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸምን በመገምገም በቀጣይ አስር ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ ትግበራ ዘመን የኢትዮጵያን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት የሚያግዝ ዓለም አቀፋዊ ደረጃውን የጠበቀ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት በመስጠት ፤ የአገልግሎት ተጠቃሚዎቻችንን ለማርካት ከምንጊዜውም በተሸለ መልኩ ተግተን እንደምንሰራ ለመግለጽ እወደለሁ፡፡

## መግቢያ

ሚቲዎሮሎጂ የከባቢ አየር ሁኔታ እና ፀባይን የሚመዘግብ፤ የሚከታተል፤ የሚገመግም፣ የሚተነትን እና የሚያጠና የመጪውን የአየር ሁኔታ በቅድሚያ የሚተነብይና የከባቢ አየር ሁኔታን ጠንቅቆ በጥናት በማወቅ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ሳይንስ ነዉ። በሳይንሱ የተደገፈ ማንኛዉም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የልማት እንቅስቃሴ ውጤታማነቱ በከፍተኛ የሚጨምር ከመሆኑም በላይ ዉስን የሆነዉን የተፈጥሮ ሀብት በአግባብ ጥቅም ላይ ለማዋልና አስጊ የሆኑ የአየር ሁኔታ ተጽኖዎችን ለመከላከል ያግዛል። ስለዚህ አመቺ የአየር ሁኔታ መኖሩን በማወቅ ለተጠቃሚዎች አስፈላጊዉን የቅድመ ሁኔታዎች ጥቆማ መስጠት ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የልማት ሥራዎችን ተገቢ መረጃን መሠረት በማድረግ ለማቀድና ዉጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በሌላ በኩል  አደገኛና አስጊ የአየር ሁኔታ እና ጠባይ ክስተቶች በህይወትም ሆነ በንብረት ላይ ሊያደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን በቅድሚያ በመረዳት ለመከላከልና የጉዳቱን መጠን ለመቀነስ አስፈላጊዉን እርምጃ መዉሰድ ያስችላል። ይህም ሳይንሳዊ ፊጠራ እና  ተጽዕኖ ላይ የተመሠረተ ቅድመ ማስጠንቀቂያዎች ላይ መሠረት ያደረገ ነው፡፡

በመሆኑም የአየር ሁኔታንና ጠባይን በመከታተልና በማጥናት፣ የአየርን ጠቃሚ ዉጤቶች ለኢኮኖሚና ለማህበራዊ ልማት እንዲውሉ ለማድረግ እና የአየር ሁኔታና ጠባይ አስጊ ውጤቶችን ለመከላከል እና ለመቀነስ እንዲሁም ሚቲዎሮሎጂን በሚመለከት ሀገሪቱን በመወከል ዓለም አቀፍ ግዴታዎችን እንዲወጣ ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ተቋቁሟል። ይህም ሀገራችን የአየር ጠባይ ተፈጥሯዊ ሀብቷን በውጤታማነት ጥቅም ላይ እንድታውል በማሰብ ነው፡፡ በዓለም አቀፋዊው የአየር ጠባይ ለውጥ ምክንያት የዓለምንም ሆነ የሀገራችንን የአየር ጠባይ ይበልጥ ተለዋዋጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ጽንፍ (weather extremes) በዝተው መደጋገም እና ተያያዥ አደጋዎች እያደጉ መምጣትን አስከትሏል፡፡ ይህም የአየር ሁኔታና ጠባይን አስቀድሞ የመተንበይ አቅም ይበልጥ እየተፈታተነ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የአየር ጠባይ ለውጥን ለመላመድም ሆነ የመቋቋም አቅምን ለማሳደግ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ከምን

ጊዜውም በላይ ተጠናክሮ ሊሠራ እና በሀገራችን ያሉ የማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስትራቴጂካዊ ውሳኔዎች በበቂ የአየር ጠባይ መረጃን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ሊሆኑ ይገባል፡፡
የሀገራችን ኢኮኖሚ በአየር ጠባይ ሀብት በከፍተኛ ሁኔታ ጥገኛ ነው፡፡ የኢኮኖሚያችን የጀርባ አጥንት የሆነው ግብርናችን የዝናብ ውሃ ላይ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የሀገራችን ስነ ምህዳር፣ ብዝሃ ህይወታችንና የውሃ ሀብታችን፣ የኃይል ማመንጫ ግድቦች፣ የፀሀይና የንፋስ ኃይል ማመንጫዎች በሙሉ የአየር ጠባይ ሀብትን መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡

የሀገራችን ኢኮኖሚ በተፈጥሮ ሀብታችን ላይ መሰረት ያደረገ እንደ መሆኑ መጠን እየተመዘገበ ያለዉን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ የምንገነባውን የብዝሃ ዘርፍ ኢኮኖሚ የሀገራችን እምቅ አቅሞች በሚገባና ቀጣዩን ትውልድ ጥቅም ባገናዘበ መልኩ ወደ ውጤት መቀየር የሚችል የአየር ንብረት ተጽእኖን መቋቋም የሚያስችል የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መስጠት ከፍተኛ ሚና አለው። ጥንካሬያቸውና ድግግሞሻቸው እየተጠናከረ የመጡት እንደ ድርቅ እና ጎርፍ ያሉ ጎጂ የአየር ጠባይ ክስተቶችም ባለፉት ጊዜያት የሀገራችንን እድገት ቀጣይነት ሲፈታተኑት መቆየታቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንጻር ኤጀንሲው ደረጃዉን የጠበቀ የአየር ሁኔታ ትንበያና ሌሎች የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶችን አጠናክሮ በመስጠት ሰዉ ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋን አስቀድሞ በመተንበይ እና መረጃውን ለውሳኔ ሰጭ አካላትና ለህብረተሰቡ በማድረስ የሀገራችን ልማት ዕዉን ለማድረግ ድርሻዉን እየተወጣ የሚገኝ ተቋም ነዉ። የሚቲዎሮሎጂን አገልግሎት በማሻሻል የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ለማርካት የሚካሄደዉ ጥረት በቀላሉ የሚገመት ባይሆንም በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ ከደንበኞች እርካታ አንጻር ገና ብዙ መስራት እንደሚገባዉ ይታመናል። በዚሁ መሰረት በክፍል አንድ የመጀመሪያውን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም በክፍል ሁለት የሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንዲሁም በክፍል ሶስት ደግሞ የሁለተኛውን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በመከሄድ እንደሚከተለው ቀርቦዋል፡፡

## የተቋሙ ርዕይ፣ ተልኮ እና ዕሴቶች

**ርዕይ፤** የኢትዮጵያን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት የሚያግዝ ዓለም አቀፋዊ ደረጃውን የጠበቀ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም እውን ሆኖ ማየት፤

**ተልዕኮ ፡** የሚቲዎሮሎጂ እና ተዛማጅ መረጃዎችን በመሰብሰብ በማደራጀት፣ በመተንተን የአየር ጠባይ ፣ የአየር ሁኔታ የአየር ጠባይ ለውጥና የአየር ብክለት በመከታተል እና በመተንበይ ለሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት እንቅስቃሴዎች እንዲሁም ለህይወትና ንብረት ከአደጋ መጠበቅ እገዛ የሚያደርግ አገልግሎት መስጠት፤


**ዕሴቶች**

- ጥራት ያለው አገልግሎት ፣ አስተማማኝ፣ ወቅቱን የጠበቀ፣ ውጤታማ፣
- ተደራሽና ደንበኛ ተኮር የአየር ጠባይ አገልግሎት
- ፈጠራ
- ሙያዊ ስነምግባር ፣ በቡድን መሥራት፣ ግልጽነት፣ ዕውቀትን ማካፈል
- ለወጣበት ዋጋ የሚመጥን ግልጋሎት

# ክፍል አንድ

## 1. የመጀመሪያው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም

### 1.1. የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች አውታር ዝርጋታ አፈፃፀም ግምገማ





**ምስል 1 ዓለም አቀፍ የሚቲዎሮሎጂ ጣብያዎች ገፅታ**

#### 1.1.1. የገፀ-ምድር የመረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች ዝርጋታ አፈጻጸም

የአገራችንን ልዩ ልዩ ክፍሎች የአየር ሁኔታና ጠባይ ክትትልና የትንበያን ሽፋን እንዲሁም የጥራት ደረጃዎችን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት የሚቻለው፤ አገሪቱ ያላትን የቆዳ ስፋትና የመልከአ ምድራዊ አቀማመጥ የሚወክሉ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች በማቋቋም ሲሆን መነሻውም ኤጀንሲው ባጠናውና በየጊዜው በሚከልሰው የጣቢያዎች ስርጭት ማስተር ፕላን ነው። በመሆኑም ኤጀንሲው የሚያስተዳድራቸው አራት አይነት ደረጃ ያላቸው መደበኛ የገፀ-ምድር /conventional/ መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች ይገኛሉ። እነዚህም የመጀመሪያው የሳይኖፕቲክ ጣቢያዎች ለአለም አቀፍ መረጃ ልውውጥ የሚውሉ በርካታ መረጃ የሚሰበሰብባቸው፣ ናቸው፡፡ ሁለተኛው የአብይ ጣቢያዎች ለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ግብዓት የሚውል በርካታ ወቅታዊ መረጃ


የሚሰበሰብባቸው፣ ናቸው፡፡ ሶስተኛው 3ኛ ደረጃ ጣቢያዎች ዝቅተኛና ከፍተኛ የአየር ሙቀትና ዝናብ መረጃ የሚሰበሰብባቸው፣ሲሆኑ አራተኛው ደግሞ 4ኛ ደረጃ ጣቢያ ሲሆን የዝናብ መረጃ ብቻ የሚሰበብባቸው ናቸው፡፡




ምስል 2 የሳይኖፕቲክ ጣቢያዎች ለአለም አቀፍ መረጃ ልውውጥ የሚውሉ

በአጠቃላይ በመጀመሪያው የዕትዕ ዘመን ውስጥ በጣቢያ ስርጭት ማስተር ፕላን መሠረት ብዛታቸው 1,097 የሆኑ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው መደበኛ የገጸ ምድር የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎችን በትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመኑ መጨረሻ 1,220 ለማድረስ ታቅዶ 1,203 ጣቢያዎች ለማድረስ ተችሏል ፡፡ ይህም የዕቅዱ (98.6%) ነው፡፡ በዚህም መሰረት፣ የሳይኖፕቲክ ጣቢያዎች በዕትዕ መጀመሪያ 18 የነበሩትን ወደ 28 ለማድረስ የታቀደ ቢሆንም በዕቅዱ ዘመን ለአብይ ጣቢያዎች እና ለሶስተኛ ደረጃ ጣቢያዎች ትኩረት ተሰጥቶ የተከናወነ በመሆኑ በዕቅዱ መሰረት አልተከናወነም።

አብይ ጣቢያ በዕትዕ መጀመሪያ 162 የነበሩትን ወደ 177 ለማድረስ ታቅዶ 173 ለማድረስ ተችሏል፡፡ ይህም የዕቅዱ (97.7%) ነው፡፡ 3ኛ ደረጃ ጣቢያን አሰመልክቶ በዕትዕ ዘመን መጀመሪያ 507 የነበሩትን ወደ 562 ለማድረስ ታቅዶ 627 ተቋቁሟል፡፡ ይህም የዕቅዱ (112%) ሲሆን 4ኛ ደረጃ በዕትዕ ዘመን መጀመሪያ 410 የነበሩትን ወደ 451 ለማድረስ ታቅዶ 403 ተቋቁሟል ፡፡ ይህም የዕቅዱ (89.4%) ነው ።




ምስል 3 የተላያዩ ደረጃ ያላቸው የገጸ ምድር ጣቢያዎች ስርጭት በኢትዮጵያ

### 1.1.2. ዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ የመረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች ዝርጋታ አፈጻጸም

የከፍታ አየር መመዝገቢያ ጣቢያ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ 2 የነበረውን አንድ ተጨማሪ በመቀሌ በመትከል ወደ 3 ለማሳደግ ታቅዶ በዕቀዱ ዘመን የግዥ ሂደቱን 45% ለማድረስ ተችሎዋል፡፡ የአየር ብክለት መከታተያና መመዝገቢያ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ በሀገሪቱ ያልነበረዉን ሁለት ለማቋቋም ታቅዶ አንድ በአዲስ አበባ ተቋቁሞ ሥራ ጀምሯል። ተጨማሪ አንድ በአዳማ ለማቋቋም የግዥ ሂደት 50% ተከናዎኖዋል፡፡ የሳተላይት መረጃ መቀበያ ጣቢያ በዕድገትና ትራንሰፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጀመሪያ ሁለት ብቻ የነበረውን ወደ 13 ለማድረስ ታቅዶ 13 ለማድረስ ተችሏል። አፈፃፀሙም (100%) ነው።



**Figure 4 በዓለም አቀፍ የአውሮፕላን ጣቢያዎች የሚገኙትን Automatic Weather Observing System (AWOS)**


ሰው አልባ አውቶማቲክ የአየር ሁኔታ መመዝገቢያ ጣቢያ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ 20 የነበረውን በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ 187 ለማድርስ ታቅዶ 107 ተቋቁሟል ይህም የዕቅዱ (57.2%) ነው፡፡

በዓለም አቀፍ የአውሮፕላን ጣቢያዎች የሚገኙትን Automatic Weather Observing System (AWOS) በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ 4 የነበረውን በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ ወደ 5 ለማሳደግ ታቅዶ በእቅዱ መሰረት ተከናውኗል (100%) ፡፡ Small Automatic Weather Observing System (S-AWOS) በመጋቢ አውሮፕላን ማረፊያ በዕቅዕ መጀመሪያ ያልነበረ ሲሆን፣ በዕትዕ ዘመን 4 ለማቋቋም ታቅዶ 4 ተቋቁሟል (100%) ፡፡

## 1.2. ዘመናዊ የመረጃ አቅርቦትና ስርጭት አፈፃፀም

የተሻለ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ጥራት ያለው የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ለመሰብሰብ በኮምፒዩተር መረብ ቢሮዎችን በማስተሳሰር የWAN እና የLAN የመገናኛ ዘዴዎችን መጠቀም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን

መጀመሪያ በዋናው መሥሪያ ቤት ብቻ ተወስኖ የነበረውን የመረጃ መረብ የኤጀንሲው የሥልጠና፣ ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ የአቪየሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የዳይሬክቶሬት እና 11ዱንም የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላት፣ ከዋናው መሥሪያ ቤት እና እርስ በርሳቸው በማስተሳሰር የመረጃ ፍሰቱ ቀልጣፋና የተሳለጠ ለማድረግ ተችሏል፡፡







ምስል 5 የኤጀንሲው የመረጃ አርካይቭ እና ኪላይ ዳታ ሶፊትዌር

በዕትዕ መጀመሪያ ላይ ውሱን መረጃዎችን ይሰራጭበት የነበረው የኤጀንሲው ድረገጽ በዕትዕ መጠናቀቂያ ዘመን 10 ኪሜ በ 10ኪሜ ግሪድ የተደራጀ መረጃን ጨምሮ ወቅታዊነቱን ጠብቆ የሚታደስ የተሟላ መረጃ የሚያቀርብ ሆኗል።

ወጥና ዘመናዊ የመረጃ ቋት ሥርዓት ማደራጀትና የጥራት ቁጥጥር ማድረግ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ በወር ከ1000 ጣቢያ


የሚሰበሰበውን መረጃ በተሟላ ሁኔታ ለማደራጀት ታቅዶ የ880 ጣቢያዎች መረጃን ለማደራጀት ተችሏል ይህም የዕቅዱ (88%) ነው።

የተለያዩ የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎችና አጋዥ ቁሳቁሶችን ማምረት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ 896 የነበረውን በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ 4,896 ለማድረስ ታቅዶ ክንውኑ 4, 896 (100%)ነው፡፡ የመረጃ አገልግሎት ተጠቃሚ ደንበኞች በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ በአመት ከነበረበት በአማካይ 733 ወደ 800 ለማድረስ ታቅዶ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ በአማካይ 866(108.3%)ደርሷል።

## 1.3. የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የምክር አገልግሎት አፈጻጸም

### 1.3.1. የሚቲዎሮሎጂ የትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስራዎች

አለም አቀፋዊና አህጉራዊ የትንበያ ሞዴሎችንና ውጤቶችን ወደ አካባቢያዊ ቦታዎች በመቀየር (Down Scaling) የትንበያን አቅም ማሳደግ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ በየአስር ቀን የነበረውን /36/ አሀዛዊ ትንበያ በመጠቀም ወደ እለታዊ ትንበያ (353) ለማሳደግ ታቅዶ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ 353 ይህም የዕቅዱ (100%) ተሰርቷል።





ምስል 6 የኤጀንሲው የአጭር ጊዜ የአየር ሁኔታ ትንበያ ማሰራጫ መንገድ (ዌብሳይት)

የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ፣10 ቀናት ፣ወርሀዊና ወቅታዊ ትንበያ /አገልግሎትና መጽሔቶች ስርጭት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ በአመት ለ65ተጠቃሚ የፌዴራልና የክልል ተቋማት ይሰራጭ የነበረውን በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ 375 ለማድረስ ታቅዶ 375 (100%) ለማድረስ ተችሏል ፡፡

## 1.3.2. የልማት ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት

ለአርሶ አደሩና ለአርብቶ አደሩ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ተደራሽነት ማሳደግ ፣ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ በየአመቱ በቁጥር 400 የነበረውን የግብርና ሚቲዎሮሎጂ የምክር አገልግሎት መጽሔት ስርጭት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ በየአመቱ 4,200 ለማድረስ ታቅዶ 4,000 ደርሷል፡፡ ይህም የዕቅዱ (95%) ነው።

የሀይድሮ ሚቲዎሮሎጂ ትንበያንና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የምክር አገልግሎት ተደራሽነትን በማሳደግ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ በቁጥር 300 የነበረውን የሀይድሮ ሚቲዎሮሎጂ የምክር አገልግሎት መጽሔት ስርጭት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ በየአመቱ 500 ለማድረስ ታቅዶ 400 ደርሷል፡፡ይህም የዕቅዱ (80%) ነው።





**ምስል 7 በልማት ሚቲዎሮሎጂ የግብርና እና የውሃ ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት**

በጤናው ዘርፍ የአገልግሎት የአፕላይድ ሚቲዎሮሎጂ ትንበያንና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተደራሽነትን በማሳደግ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ በቁጥር በአመት 300 የነበረውን የጤና ሚቲዎሮሎጂ የምክር

አገልግሎት መፅሄት ስርጭት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ በአመት 500 ለማድረስ ታቅዶ 400 የዕቅዱ (80%) ደርሷል፡፡

### 1.3.3. የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት




**ምስል 8 የኢትዮጵያ አየር መንግድ ዓለምአቀፍ እና የሀገር ውስጥ በረራ ስርጭት**

የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ በአለምአቀፍ፣ በአህጉርና በሀገር ደረጃ ከፍተኛ ዕድገት እያሳየ ይገኛል። በሀገራችን የአቪዬሽን ኢንዲስትሪ በተደራጀና በተቀናጀ አሠራር ከተጀመረ ስድስት አሥርት ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ሲሆን ከፍተኛ ዕድገት እያስመዘገበ ይገኛል። በሀገሪቱ በሚገኙ መጋቢ እና አለም አቀፋዊ የአውሮፕላን በረራ ጥራቱን እና ደረጃው የጠበቀ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ለመስጠት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዙ ሲስተሞች እና መሳሪያዎች ተከላ ከመከናወኑ ባሻገር የባለሙያ የብቃት ማረጋገጫ ጥራት ስራ አመራር ስርአትን በመዘርጋት /በከፊል/ ተግባራዊ ለማድርግ ጥረት ተደርጓል፡፡ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻ ለአውሮፕላን በረራ የሚሰጠው የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ከ9 አውሮፕላን ማረፊያዎች በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ ወደ 15 ማድረስ ታቅዶ በ15 አውሮፕላን ማረፊያዎች አገልግሎት ለመስጠት ተችሏል፡፡ ይህም የዕቅዱ (100%) ነው፡፡

### 1.4. የሰው ሀብት ልማትና የአቅም ግንባታ አፈጻጸም ግምገማ

ከሰው ሀብት አደረጃጀት እና አሰራር አኳያ በእድገትና ትራንስፎርሜሽኑ መጀመሪያ ከነበረው የሰው ኃይል /800/ ውስጥ 80 በመቶ የነበረው የተሟላ የሰው ኃይል መቶ በመቶ ለሟሟላት ታቅዶ 90 በመቶ ተከናውኗል፡፡ ቅጥር እድገት አሰራር እና አደረጃጀት በፌድራል የመንግስት ሰራተኞች ሚኒስቴር በወጡ የቅጥር እና ዕድገት አሰራር መመሪያ መሰረት የኤጀንሲውን የሰው ሀይል ፍላጎት የሚሟላት ስራዎች ተከናዎኖዋል፡፡ በዋና መስሪያ ቤትና በአስራ አንዱ ቅርንጫፍ የሚቲዎሮሎጂ ዳይሬክቶሬቶች የሚያስፈልገው አደረጃጀትን በማሻሻል በበቂ የሰው ኃይል ለሟሟላት የስራ መደቦች ተፈቅደዋል፡፡ በዚሁም መሰረት በዕትዕ ዘመኑ 300.ያህል አዳዲስ የስራ መደቦች በእድገት እና በቅጥር ተሟልቷል፡፡

በመሰረታዊ የአሰራር ለውጥ ሂደት ለየስራ ዘርፉ የሚያስፈለገው የሰው ኃይል እና አደረጃጀት እየተከለሰ እንዲሟላ ተደርጓል፡፡ የተቋሙን ልዩ ባህርይ መሰረት ያደረገ የሙያ መሰላልና ልዩ ደመወዝ ሰኬል ጥናት ቀርቦ በመንግስትም ተፈቅዶ ተግባራዊ ሆኗል ፡፡ በኤጀንሲው የሰው ሀብት ልማትና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ለማከናወን የሚቲዎሮሎጂ ትምህርትና ስልጠና ዳይሬክቶሬት አደረጃጀት ተዋቅሮ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የትምህርትና ስልጠናን ተግባራት ተከናውኗል፡፡

ከሰው ኃይል አቅም ግንባታ አኳያ በጀማሪ ፣በመካከለኛና በከፍተኛ ሚቲዎሮሎጂ ቴክኒሽያን የሀገር አቀፍ የሙያ ደረጃ/Occupetional Standard / የምዘና ስርዐት /Assesment Tools/ እና የምዘና ማዕከል / Assesment Center / በማጥናት እውቅና እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ የኤጀንሲው የትምህርት እና ስልጠና መመሪያ ተሻሽሎ ተግባራዊ ሆኗል፡፡

የሰው ሀብት ልማቱን ለማበራከትና ለማስፋት በራሱ አቅም፣ በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ባሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር ትስስር መፍጠርና በተገቢው ሁኔታ ክፍተቶችን መሙላት ፣ ከአዳዲስ ቴክኖሎጂና የጥናትና የምርምር ግኝቶች በመስኩ ከሌሎች ዘርፎች ጋር አብሮ ለመጓዝ በተለያየ እርከን የአቅም ግንባታ ሥራዎችን አቅዱ መሰረት ተከናውኖዋል፡፡



**ምስል 9 በተለያዩ ጊዜ የተሰጡ የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎች በከፊል**

በመሆኑም ከአጭር ጊዜ ስልጠናዎች አፈጻጸም አኳያ ለሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማሻሻያ የሚያግዙ ስልጠናዎች ለዋናው መ/ቤት እና ለቅ/ዳይሬክቶሬቶች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር /በኢ.ጋድ የአየር ጠባይ ትንበያና ትግበራ ማዕከል፣ በአውሮፓ የመካከለኛ ጊዜ አየር ሁኔታ ትንበያ ማዕከል የአፍሪካ ሚቲዎሮሎጂ ትግበራና ልማት ማዕከልና በተለያዩ የአለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት የሚቲዎሮሎጂ የስልጠና ማዕከላት ወዘተ /ተስጥዋል፡፡ በኤጀንሲው ለሚገኙ ለመካከለኛ አመራሮች እና ሰራተኞች የጥራት ስራ አመራር የመሰረታዊ ኮምፒዩተር ፣የቢሮ አስተዳደር ፣የስራ አመራር ስልጠና፣ የሚዛናዊ ውጤት ተኮር ምዘና ፣የምርታማነት ማሻሻያ ወዘተ ተስጥቷል፡፡ የአለም የሚቲዎሮሎጂ ድርጅት እና የአለም አቀፍ የሲቭል አቬሽን ድርጅት ባዘጋጁአቸው ስልጠናዎች እና ሰብሰባዎች ላይ የኤጀንሲው ባለሙያ ተሳትፈዋል፡፡ የኢጀንሲው የበላይ አመራር የመካከለኛ አመራር እና ባለሙያዎች በተለያዩ ሀገሮች የልምድ ልውውጥ አድርጓል፡፡

ከረጅም ጊዜ ስልጠናዎች አፈጻጸም አኳያ በአለም የሚቲዎሮሎጂ ድርጅት እና በሀገር ውስጥ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በተደረገ ግንኙነት እና ስምምነት መሰረት ከመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽ እቅድ ማጠናቀቂያ ላይ 10 የነበረውን በሁለተኛ ድግሪ የተመረቁ ባለሙያዎች ቁጥር ወደ 22 ለማድረስ ተችሏል፡፡

በሚቲዎሮሎጂ የድህረ ምረቃ ዲፕሎማ በናይሮቢ ዩኒቨርስቲ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽ እቅድ አንድ ባለሙያ ማሰልጠን ተችሏል፡፡

## 1.5. የባለ ብዙ ዘርፍ ስራዎች አፈጻጸም

### 1.5.1. የሴቶች ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፡፡

የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አኳያ ሴቶች በእድገት በቅጥርና በትምህርት ልዩ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንጻር ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችንና የኃይል ጥቃቶችን ለመከላከል የግንዛቤ የማስጨበጥ ሰፊ ሥራዎች በኢጀንሲው ተሰርቷል። በዚህም መሰረት በኤጀንሲው በሁሉም መስክ ተሳታፊና ተጠቃሚነት በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መጀመሪያ ከነበረው 25 በመቶ ወደ ሃምሳ በመቶ ለማሳደግ ታቅዶ የሴቶች በውሳኔ ሰጭነትና አመራር ተሳትፎ ወደ 35% ለማድረስ ተችሏል፡፡

### 1.5.2. የአረንጓዴ ልማት ትግበራ አፈጻጸም

ለአየር ጠባይ ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ከአየር ጠባይ ጋር መላመድ ሆነ ለአየር ጠባይ ለውጥ ተጽኖዎች ላይ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ቁልፍ እና የማይተካ ሚና አለው ። በዚሁ መሰረት ከብሔራዊ የአየር ጠባይ መላመድ ድርጊት መርሀ ግብር /NAPA/ከተለዩ ፕሮጀክት ጽንሰ ሀሳብ በመነሳት የአየር ጠባይ መረጃና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት የማጠናከር /SCIEWS/ፕሮጀክትና ሌሎች ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች ተቀርጸ ተግባራዊ ተደርጎዋል፡፡፡ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ በመሰብሰብና በመተንተን ሀገሪቱ ለተያያዘችው የአረንጓዴ ልማት እቅድ ስኬት ግብዐት የታዳሽ ኃይል የሆኑ የንፋስ፣ የፀሐይ ብርሃንና የዝናብ ታሪካዊ መረጃዎችን

እና ትንበያዎችን በጥራት በማደራጀት አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ የአየር ጠባይ ለውጥ መግለጫዎችን በመረጃ በማስደገፍ ህብረተሰቡ ትክክለኛና ሳይንሳዊ ግንዛቤ እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ የአየር ጠባይ ለውጥ መረጃ በማዘጋጀት በተለየያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች የሚያስከትለውን ተጽዕኖ እና የተጋላጭነት መጠን በተጠኑት ጅምር ስራዎች ከአየር ጠባይ ለውጥ ጋር በማላመድ ለመኖር በሚደረግ ጥረት እና የልማት አቅጣጫ ላይ መረጃ መሠረት በማድረግ የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል፤

### 1.5.3. የኤጀንሲው አገለግሎትን የማስተዋወቅ፣ የገፅታ ግንባታ እና ኮሙኒኬሽን ስራዎች

በዓመታዊ ዕቅዶችና አፈፃፀሞች፣ በአገልግሎት አሰጣጥና አጠቃላይ የኤጀንሲውን እንቅስቃሴ በሚያሳዩ ወቅታዊ አጀንዳዎች ዙሪያ ሁነቶችን፣ የምክክር መድረኮችን ከአገልግሎታችን ተጠቃሚዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር በማዘጋጀት የኤጀንሲውን አገልግሎት ለማስተዋወቅ ጥረት ተደርጎል፣ እንደ ተቋም የተደራጀ የኮሙኒኬሽን ሥራን ለማከናወን በየሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላት ደረጃ አደረጃጀት ለመፍጠርም ጥረት ተደርጎል፣

በሚቲዎሮሎጂ ሳይንስና በኤጀንሲው ወቅታዊ እንቅስቃሴ ላይ ትኩረት ያደረጉ የህትመት ውጤቶችን በማዘጋጀት የህትመት እና የኤሌክሮንክስ ሚዲያዎችን በመጠቀም ወቅታዊ መረጃዎችን በፍጥነት ወደ ህብረተሰቡ ከማድረስም ባሻገር ህብረተሰቡ በሚሰጡ አገልግሎቶችና በመረጃው አስፈላግነት ዙሪያ ያለው ግንዛቤ እየተሸሻለ መምጣቱና የግንዛቤ ደረጃውም 70%ላይ መድረሱን በተደረገው የዳሰሳ ጥናት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡



ምስል 10 የኤጀንሲውን አገልግሎት በተለያዩ ሚዲያዎች የማስተዋወቅ ሥራ

### 1.5.4. የለውጥ ስራዊት ግንባታ እና የመልካም አስተዳደር ስራዎች አፈጻጸም

ከለውጥ ሰራዊት ግንባታ ስራዎች አፈጻጸም አኳያ የኤጀንሲው የከፍተኛ አመራሩ ሁኔታ የፕሮሳስ ካውንስል መደበኛ ስብሰባ በየሁለት ሳምንት፣ የየዳይሬክቶሬቶቹ ሳምንታዊ ስብሰባ በየሳምንቱ እየተደረጉ ስብሰባዎችም የተፈለገውን ግብ ያሳኩ መሆናቸውን በየጊዜው በመገምገም ችግሮችን በመለየት ባለቤት እንዲኖራቸው ሆነው የአጭር፣የመካከለኛና ረጅም ጊዜ ዕቅድ ውስጥ ተካተው የመፍትሄ እርምጃዎች ስሰጡ ነበር። የኤጀንሲውን መካካለኛ አመራሪና ፈፃሚዎችን በአመለካካት፣በፀረ-ኪራይ ሰብሳቢነት፣በክህሎትና በዕውቀት ከማብቃት አኳያ ዘርፈ-ብዙ የአቅም ግንባታ ተግባራት ቀጣይነት ባለው መልኩ ተከውኗል። የኤጀንሲው የበላይ አመራር በመንግሥት ደረጃ የተቀመጠውን ግልጽ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ለመፈፀም የሪፎርም ሥራዎችን በየደረጃው ያለው አመራር በአግባቡ ይዞ እንዲተገብር ለማድረግ በሁሉም ደረጃ የሚስተዋለውን የአመለካከት፣የክህሎትና የአቅርቦት ማነቆዎችን ለመፈታት በርካታ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ በኤጀንሲ ያጋጠመውን የህንፃ መሰንጠቅ በሠራተኛው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳይኖረው ለማድረግ ቀደም

ሲል በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የተወሰደውን ሕንፃ በማስመለስ ምቹ የስራ አከባቢ መፍጠር የተቻለ ሲሆን ችግሩን በዘለቄታ ከመፍታት አኳያ ከመንግስት ጋር በመነጋገር ዘመን ተሻጋሪ ሕንፃ ለማስገንባት የረጅም ጊዜ አቅድ አስይዞ መስራት ጀምሮዋል፡፡

የፈጻሚ የሲቪል ሰርቪሳችን ሁኔታን ስንመለከት ባለፉት አምስት አመታት በርካታ ተግባራትን ተከናውኖዋል። ፈፃሚው በተደራጀው የለውጥ ቡድኖች በየዕለቱ ተግባራት ታቅደው እያከናወኑ የእርስ በርስ ግምገማ / የዕለቱ ውሎ ግምገማ መደረጉ፤ ሳምንታዊ፤ ወርሃዊ እና በግምገማዊ ስልጠናዎች አማካይነት በየጊዜው አቅማቸውን ለማሳደግ የሚያደርጉት ከፍተኛ ጥረት መስተዋሉ፤ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ተሳትፎ ማሳደጉ፤ የዳይሬክቶሬቱን ዕቅድ ለማሳካት ተግብረው የአፈጻጸም ሪፖርቱን በማዘጋጀት ለቅርብ ሃላፊ አቅርቦ የማስገምገም እንዲሁም እርስ በርስ የመማማርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ሂደት ልምዶች እየዳበሩ መምጣት ችለዋል። ከስራ ሂደቱ፣ ከቡድኑ የወረደለትን ተግባራት ከፋፍሎ በጥራት፣ በመጠንና በጊዜ በማቀድ፣ ሪፖርት የማቅረብ ሥራዎች በአምስት አመቱ ውስጥ የታዩ መልካም ጅምሮች ናቸው።

የህዝብ ክንፉንም ሁኔታ ስንመለከት ኤጀንሲው የራሱን የሕዝብ ክንፍ ቀደም ብሎ በመለየት ቋሚ መድረኮችን በየግዜው ከአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ጋር በመፍጠር በአፈፃፀም ሂደት የታዩትን ክፍተቶች ወይም ከተጠቃሚዎቹ የሚነሱ ጉዳዮችን በዝርዝር በመፈተሽ በቀጣይ እቅድ ውስጥ በማካተት ለቀጣይ የህዝብ መድረክ የተሻለ አፈፃፀም ይዞ ከመቅረብ አንፃር በዋና መ/ቤት ደረጃ ተጨባጭ ውጤትና በርካታ ልምዶች ተገኝቶበታል፡፡ በተካሄዱ ዉይይቶች የህዝብ ክንፉ አብሮ ለመስራት ፍላጎት ማሳየቱ በዋናው መ/ቤትና በቅርንጫፍ ዳይሬክቶርቶች በተዘጋጁ መድረኮች ላይ በአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የሚረዱ ገንቢ አስተያየቶችን መገኘቱና አዳዲስ ሃሳቦችም የሚፈልቁበትና የተለያዩ ምርጥ ተሞክሮዎችም የሚገኙበት መድረከ እየሆነ መቷል፡፤

ከመልካም አስተዳደር ስራዎች አፈጻጸም አንጻር በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጠንካራ የማስፈፀም አቅም ያለው ፈጻሚ ለመፍጠር፣ ግልፅነትን የማስፈንና ኪራይ ሰብሳቢነትን ከምንጩ የማድረቅና ተሳትፎን

የማረጋገጥ አቅጣጫዎች ተይዘው በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል። በዚህም መሠረት፡-







**ምስል 11 በለውጥ ስራዊት ግንባታ እና የመልካም አስተዳደር ዙሪያ የተሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች**

የግልጽነትና የተጠያቂነት አሠራርን በማስፈን የኪራይ ሰብሳብሳቢነት አመለካከትና ተግባራትን ለመቀነስ በየደረጃው ጥረቶች ተደርገዋል፤፡ የኤጀንሲው አገልግሎት ተጠቃሚዎች ተሳትፎ በማጠናከርና ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ በተፈጠረው ቋሚ የግንኙነት መድረክ የተገኙትን ግብረ መልሶች ለአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያነት ማዋል ተችሏል፡፡ አደረጃጀትና አሠራር የማሻሻልና የለውጥና ኮሙኒኬሽን ሥራዎች ተከናውኗል፤
የዋና መስሪያ ቤቱና የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላት የመልካም አስተዳደር ችግሮች ተለይተው መንስኤያቸውንና መፍትሂያቸውን በማመላከት ወደ ተግባር በመግባት ችግሮቹን የመቅረፍ ስራ ተከናውኖዋል፡፡

## 1.6. የበጀትና ፋይናንስ አፈጻጸም





Figure 12 የኤጀንሲው የበጀትና ፋይናንስ አፈጻጸም

## 1.7. የክትትል እና ግምገማ ስርአት፣ጥንካሬዎች እና ድክመቶች እንዲሁም ያጋጠሙችግሮች

### 1.7.1. የእቅዱ የክትትል እና ግምገማ ስርአት፣

- የክትትልና ግምገማ ሥራ በየደረጃው ለማካሄድ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሆኗል ፡፡
- በሪፖርት፣ በአካላዊ ግምገማ እና በሱፐርቪዥን መልክ የክትትልና ግምገማ ተካሂዷል ፤
- በየደረጃው የሚቀርቡ ሪፖርቶችን በመለየትና ክትትልና ግምገማ ተከናውኗል፡፡

### 1.7.2. በእቅድ ትግበራው ሂደት የነበሩ ጥንካሬዎች፣

- በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችና ሲስተሞች ተጠቃሚ መሆን መቻሉ
- በተሰጠው የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ አገልግሎት የትንበያው ተዐማኒነት መጨመሩ
- የማህበረሰቡን ለሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ መቻሉ
- የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማበራከት የተሰሩ የአቅም ግንባታ ሥራዎች

- ❖ ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር ያለው ትስስር መጠናከሩና በዘርፉ የተገኘው ሀብት ለዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ መሣሪያዎች ማስፋፍያና ለአቅም ግንባታ አስተዋፆ ማድረጉ

### 1.7.3. በእቅድ ትግበራው ሂደት ያጋጠሙ ድክመት

- ❖ በአንዳንድ የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ላይ የተስተዋለው የማስፈጸምና የመፈጸም አቅም ክፍተት
- ❖ ለኤጀንሲው የተመደበውን በጀት አሟጦ ለመጠቀም አለመቻል ፣
- ❖ የኤጀንሲው የእቅድ ፣ክትትልና ግምገማ ስርዓት ጠንካራ አለመሆን ፣
- ❖ መሰረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አቅርቦት አገልግሎትን የሀገሪቱን ስነምህዳር በወከለ መልኩ በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ አለመቻል ፣
- ❖ ወቅታዊና ጥራታቸውን የጠበቁ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችል አቅም ውስን መሆን ፣
- ❖ የአጭር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ትንበያዎች ተጠቃሚዎች በሚፈልጉት ጥራት፣ ጊዜና ቦታ አንጻር በሁሉም ደረጃ በሚፈለገው መጠንና አይነት ተደራሽ አለማድረግ፣
- ❖ በአውሮፕላን በረራ ደህንነት ከተገልጋዮች የሚጠበቀውን አገልግሎት ለማቅረብ የግብአት አቅርቦት ማነስ፣
- ❖ በግብርና በውኃ በኢነርጂና በጤና መስክ በተጠቃሚዎች የሚፈልጉ አገልግሎቶችን ለማቅረብ አቅም ማነስ፣
- ❖ ቀልጣፋ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ለመስጠት የሚያስችል የኢንፍርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አቅምና ሽፋን በሚፈለገው ደረጃ መጠቀመም አለመቻል

### 1.7.4. ያጋጠሙ ችግሮች

- ❖ በሚቲዎሮሎጂ ሙያ የሰለጠነና ልምድ ያለው የሰዉ ሀይል ከገበያ ተሟልቶ አለመገኘት፣
- ❖ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ላይ የሚፈፀም ስርቆት፣የቴሌኮምና የኤሌክትሪክ አገልግሎት ሽፋን የተሟላ አለመሆን እና መቆራረጥ

- ለሚቲዎሮሎጂ መሣሪያዎች ግዥ የውጭ ምንዛሪ መናር፣ በተፈለገው ጊዜ አይነትና መጠን አለመገኘት፣
- የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ለማቋቋም ወካይ ቦታ ለማግኘት አለመቻልና የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ አለማግኘት፣
- በሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎችና አጋዥ ቁሳቁሶች ጥገና ወቅታዊ ቅኝት እና ካሊብሬሽን ለማድረግ የተሽከርካሪ እጥረት መኖር

## ክፍል ሁለት

# 2. የሁለተኛው ዕድገትና ትራስፎርሜሽን ዕቅድ

## 2.1. የሁለተኛው ዕድገትና ትራስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻ ሁኔታዎች ግምገማ




**ምስል 13 ዓለም አቀፋዊ ትብብሮች**

### 2.1.1. ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ

በሚቲዎሮሎጂ መስክ ያለው ዓለም አቀፍ ትብብር ወደ 137 ዓመታት አካባቢ እንደሚጠጋ የዓለም ሚቲዎሮሎጂ ታሪክ ያመለክታል፡፡ ለዚህም ዋነኛ መንስኤ የአየር ጠባይ በአገሮች ድንበር የሚወሰን ሳይሆን፣ የራሱ የሆነ የተፈጥሮ ሕግጋት ስላለዉና በአንድ አካባቢ የደረሰው የአየር ሁኔታ ጠባይና በሌላ አካባቢ ካሉት የከባቢ አየር ክስተቶች ጋር የተዛመደ በመሆኑ፣ በመረጃ ልውውጥ እንዲሁም ብዙ አገሮችን ሊነኩ የሚችሉ የአካባቢ አየር ክስተቶችን በመከታተል ዓለም አቀፋዊ ትብብር አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

ይህ ዓለም አቀፍ ግንኙነት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገሮች መካከል ያለውን ትብብር እያጠናከረው መጥቷል። በተለይ የአየር ሁኔታና ጠባይ የማይነካው የኢኮኖሚ ዘርፍ የሌለ በመሆኑ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አሳሳቢ እየሆኑ በመጡት የአየር ጠባይ ለውጥ፣ የድርቅና የጎርፍ፣ ወዘተ ክስተቶች በአጠቃላይ በአየር ሁኔታ መዛባትን ለመግታት በሚደረግ ጥረት ሳቢያ ያለው ትብብር በመረጃ ልውውጥና የአየር ጠባይ ክስተቶችን በመከታተል ሳይገደብ፣ ጥናትና ምርምር ሥራዎችም ዓለም አቀፋዊ ትብብርን የበለጠ የሚሹ ሆነው ተገኝተዋል። በተለይም በዓለማችን በአሁኑ ጊዜ ከአየር ጠባይ ተለዋዋጭነት ና ለውጥ (Climate Variability and Change) ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ እንደ ድርቅ፣ ጎርፍ፣ የባህር ማዕበል (Tropical Cyclone)፣ የመሬት መንሸራተት፣ በዋልታዎች የሚገኘው ግግር በረዶ እየቀለጠ መሄድ የመሳሰሉት ክስተቶች ዓለም-አቀፋዊ ትኩረት እየሳቡ መጥተዋል።

የምድር ከባቢ አየር የቅኝት መርሀ ግብር (World Weather Watch Programme)፣ የዓለም ከባቢ አየር የምርምር መርሀ ግብር (Global Atmospheric Research Programme) የተባበሩት መንግስታት የአየር ጠባይ ለውጥ ስምምነት ማዕቀፍ (United Nations Frame Work Convention on Climate Change, UNFCCC)፣ በአገሮች መካከል ሊኖር የሚችለውን የቴክኖሎጂ ሽግግር በማጠናከር በኩል በአብነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ዓለም አቀፍ የትብብር ውጤቶች ናቸው።

እንደዚህ አይነቱ ዓለም ዓቀፋዊ ትብብር በአንድ ጎኑ በሚቲዎሮሎጂ መስክ አይነተኛ ባህሪ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ እያደገና እየጎለበተ በከፍተኛ ፍጥነት እየተለዋወጠ በሚሄደው የሚቲዎሮልጂ ሳይንስና የቴክኖሎጂ ውህደት አንፃር እያንዳንዱ ብሔራዊ የሚቲዎሎጂ ተቋም ራሱን አጠናክሮ መገኘት አለበት፡፡ ከአህጉራዊና ክፍለ አህጉራዊ የምርምር፣ የአየር ትንበያና የስልጠና ማዕከል በሚገኘው የቴክኖሎጂ ሽግግር በአገራቱ ለሚገኙ ተገልጋዮች የተሻለና የተጠናከረ አገልግሎት በማበርከት መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል፡፡

የዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት አባል የሆኑ ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ እና ሀይድሮሎጂ ድርጅቶች በየአገሮቻቸው ዕድገትና ልማት ላይ የሚኖራቸው ሚና ፣ የሕይወትና ንብረት ደህንነትን ከልዩ ልዩ ጎጂ የአየር ጠባይ ሁኔታዎች

በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አማካይነት፣ በተፈጥሮ አደጋዎች ሳቢያ ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችን ለመከላከል፣ ለአየር ትራንስፖርት ደህንነት፣ የግብርና ምርትን ለማሳደግ፣ ለአካባቢ ጥበቃና ለመገናኛ ብዙሃን አስፈላጊ የተጠናቀሩና የተተነተኑ መረጃዎች ማቅረብ ዋነኞቹ እንደሆኑ ግንዛቤ ተወስዷል።

በአብዛኛዎቹ የሚቲዎሮሎጂ ድርጅቶች በዋናነት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ሆነው የቀረቡት ዘመናዊ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎች ተግባራዊ ማድረግ (Modernization) አቅም ግንባታ፣ እያደገ ለመጣው የአየር ትራንስፖርት ደህንነት (Air navigation safety) አስተማማኝ መረጃ የማዘጋጀት እንዱሁም በአገራዊ ዕይታ የሚቲዎሮሎጂ ድርጅቶች ሚና ምን መሆን እንደሚገባው የሚያተኩሩ ናቸው።

በአጠቃላይ ሲታይ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚንፀባረቁት ሁኔታዎች ይህን ሲመስሉ በአገሮች መካከል ካለ ኢኮኖሚያዊና የልማት ዕድገት ልዩነት አንፃር በየአገራቱ ያሉ የሚቲዎሮሎጂ ድርጅቶች አጠቃላይ ሚና እንደየ አገራቱ ተጨባጭ ሁኔታ ሊለያይ እንደሚችል ግንዛቤ መውሰድ ያስፈልጋል።

የአየር ሁኔታና ጠባይ (Weather & Climate) ድንበር የማያግዳቸው ክስተቶች በመሆናቸው አስጊ የሆኑ የአየር ሁኔታ ገፅታዎችን በሚመለከት ከወዲሁ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በማዘጋጀትና በማሰራጨት ዕለት ተዕለት የመረጃ ልውውጥ በአገሮች መካከል ማካሄድ አስፈላጊ ነዉ። ይህ አይነቱን የመረጃ ልውውጥ ውጤታማ ለማድረግ የመገናኛ አውታር በዓለም አቀፍ ፣ አህጉራዊና አካባቢ ማዕከላትና በኢንተርኔት መስመር ጋር ግንኙነት በማድረግ መረጃዎችን በስፋት ለመለዋወጥ ይቻላል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣውን የሚቲዎሎጂ ሳይንስና እየረቀቀ የመጣውን አኃዛዊ ትንበያ (Numerical weather prediction, NWP) የመጠቀም አቅምም ውስንነት ቢኖርም ከሱፐር ኮምፒዩተሮች የተገኙ ውጤቶችን NWP ሞዴሎችን በመደበኛ ኮምፒዩተር እየተጠቀመ ይገኛል። ስለሆነም ከዓለም የሚቲዎሮሎጂ ድርጅት አባል ሀገራት ጋር የተፈጠረው መልካም ግንኙነት፣ የዓለም የሚቲዎሮሎጂ ድርጅት የትንበያ ማዕከላትና የትምህርትና ስልጠና ማዕከላትን በመጠቀም የተሸለ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ዕድል መኖሩ ለዕቅዱ ስኬት እንደ ጥሩ አጋጣሚ ተወስዷል፡፡

### 2.1.2. ሀገራዊ ሁኔታ

በአገራችን በተለያዩ ዓመታት በተከሰቱት የአየር ሁኔታና ጠባይ ተለዋዋጭነት እና ለውጥ ምክንያት ተፈጥረው የነበሩት እንደ ድርቅ፣ ረሃብ እና ጎርፍ የመሳሰሉት ክስተቶች በህዝቦች ማህበራዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ላይ ከፍተኛ ሚና ነበራቸው። የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በአዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት እነዚህን አደጋዎች አስቀድሞ በመተንበይ የአደጋዎቹን ጉዳት በመቀነስ እና ህብረተሰቡ ቅድሚያ ጥንቃቄ እንዲያደርግ፣ የትንበያ እና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መግለጫዎችን ሲሰጥ ቆይቷል። በዚህ መሰረት በአለፉት ዓመታት በሀገራችን የተከሰቱትን የድርቅ እና የጎርፍ ክስተቶችን አስቀድሞ በመተንበይ ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት እና ለህብረተሰቡ በመስጠት ሊደርስ የሚችለውን ድንገተኛ አደጋ ለመቀነስ ተችሏል። ከሌሎች የዓለም ክፍሎች ይልቅ በሀሩር ክልል (በትሮፒካል ክልል) በሚገኙ አገሮች ላይ የድርቅና የዝናብ ወቅቶች መፈራረቅ በጎላ መልኩ የሚታይ ሲሆን፣ ከወቅት ወቅት ወይም ከዓመት ዓመት የሚታየው የአየር ጠባይ ተለዋዋጭነት ተደጋጋሚነቱ እየጨመረ ይገኛል።

ለዚህም የቅድሚያ ማስጠንቀቂያዎች፣ የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንተናና ትንበያ በመስጠት የድርቅና የጎርፍ አደጋዎችን በመቀነስ ለተለያዩ ሶሽዮ-ኢኮኖሚያዊ ስራዎችና ለህብረተሰቡ ደህንነት ከፍተኛ እገዛ በሚያደርግ መልኩ አስተማማኝና ወቅታዊ መሆን ይኖርበታል። መንግስት በነደፋቸው የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ተፈጻሚነት ባለፉት አስራ አንድ ዓመታት ኢኮኖሚው በአማካይ በዓመት 10 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል።

ኤጀንሲው በሚሰጣቸው አገልግሎት የሚያካሂደውን የልማት ስራዎችን ለመደገፍ ሁሉንም ክልሎች የሚሸፍን አስራ አንድ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላት በማዋቀር የሚቲዎሮሎጂ መረጃን ለመንግሥት ውሳኔ ሰጪ አካላትና ለአካባቢው ህብረተሰብ በማሠራጨት ላይ ይገኛል። ኤጄንሲው በድረ-ገፅ የ24 ሰዓት፣ የሶስት ቀናት፣ የአስር ቀናት፣ የወራትና የወቅቶች ትንበያ መረጃዎች ጊዜያቸውን ጠብቀው በመሠራጨት ላይ ናቸው። በዚሁ መሰረትም በቀን አራት ጊዜ ስለአየር ሁኔታ መረጃ የሚሰጥ

የሳተላይት ምስሎች፣ የቱሪስት መስህብ ያላቸው በተጨማሪም የዋና ዋና ከተሞች እና የአጭር ጊዜ የአየር ሁኔታ ትንበያዎች፣ እንዲሁም በሬዲዮና በቴሌቪዥን በ2 ቋንቋዎች የአየር ሁኔታ ትንበያዎች በማሰራጨት ላይ ይገኛል።

በአጠቃላይ ኤጀንሲዉ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ሥራዎች የበኩሉን አስተዋፅኦ የሚያበረክትባቸው መስኮች፡ ለግብርና ልማት ዘርፍ ስኬታማነት የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት Response Farming መሰረት ያደረገ የGrassroot Meteorological Service (GRAMS) አገልግሎትን መስጠት፣ ለዉሀና ኢነርጅ ዘርፍ የሃይድሮሚቲዎሮሎጂ ትንበያና የምክር አገልግሎት መስጠት፣ የጤና ሚቲዎሎጂ ትንበያና የምክር አገልግሎትን /ወባ፣ ማጅራት፣ ገትር/ እንዲሁም በአየር ሁኔታና ጠባይ ሳቢያ ሊከሰቱ የሚችሉ ወረርሽኞችን ቀድሞ ለመከላከል የሚያስችል አገልግሎት ተግባራዊ ማድረግ፣ ለግንባታው ዘርፍ የሚቲዎሮሎጂ መረጃን መጠቀም ለግንባታ ሥራ ውጤታማነት ላይ እሴት ይጨምራል።

የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ዘመኑ በሚጠይቃቸው የቴክኖሎጂ አሰራሮችና መመሪያዎች መሠረት ጊዜውንና ደህንነቱ ለተጠበቀ ውጤታማ ለአውሮፕላን የበረራ አገልግሎት የሚውል ጥራቱንና ደረጃ የጠበቀ የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

በአጠቃላይ የአየር ሁኔታ ገፅታዎችን በማጥናት ሊያስከትሉ የሚችሉ ተፅዕኖዎችን በቅድሚያ ለመተንበይ የሚያስችል ሳይንሳዊ መሠረት ያላቸው የትንበያ ዘዴዎች በመገንባትና በመጠቀም በአገሪቱ ሊከሰት የሚችለውን የአየር ጠባይ ተለዋዋጭነትና ለውጥን እንዲሁም በተፈጥሮ ሀብት ላይ ሊደርስ የሚችለውን የአየር ብክለትና ሌሎች ጎጂ ክስተቶችን በቅድሚያ መረዳት የሚያስችሉ ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችሉ ተግባራት ታቅደዋል። በሌላ በኩል የአገሪቱን መልከአ ምድራዊ ገፅታዎች የሚወክሉትን የአየር ሁኔታ መረጃ መመዝገቢያ ጣቢያዎች በማቋቋም መረጃዎችን መመዝገብ፣ ማጠናቀር፣ መተንተንና በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት የመረጃ ልውውጥ እንዲሁም መረጃዎቹ የሀገር ሀብት እንደመሆናቸው ለተተኪ ትውልድ ጠቀሜታ እንዲውል ማከማቸት ሌላው

ዋና ተግባር ነው ፡፡ ኤጀንሲው ያቋቋማቸው የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላትን በሰው ኃይል፣ በዘመናዊ የመገናኛ አውታር በሌሎች መሠረተ ልማት በማጠናከር ለክልሎች አስፈሊጊውን የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት በብቃት እንዲሰጡ ማድረግ፣ ከአየር ጠባይ ገጽታዎች ለታዳሽ የኃይል ምንጮች አጠቃቀም ግብአት የሚሆን የሃይድሮ፣ የንፋስና የፀሐይ ጨረር ኃይል እምቅ ሀብቶች ጥናት ለማካሄድ የሚያስችሉ የትንተና አገልግሎቶች በማጠናከር የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ማሳካት ትኩረት ተሰጥቶታል። በመሆኑም በሀገራችን በተለያዩ ጊዜዎች እየተከሰቱ ባሉት የድርቅና የጎርፍ አደጋዎችን በራስ አቅም ለመከላከል ትኩረት የተሰጠው በመሆኑ ኤጀንሲው የተሸለ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚያስገድደው በመሆኑ ለዕቅዱ መሳካት በጎ ተፅዕኖ ፈጥሮዋል፡፡

### 2.1.3. የበጀት ወይም ፋይናንስ የማፈላለግ (Resource Moblization) ሁኔታ




ምስል 14 ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የልማት አጋሮቻችን

የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ለማልማት የሚጠይቀው ከፍተኛ የመዋለ ንዋይ ፍላጎት የመንግስት የኢንቨስትመንት ድርሻን በአብላጫ የያዘ ነው። ለምሳሌ የዘመናዊ ሚቲዎሮሎጂ ጣቢያ ግንባታ አስራ አራት በመቶ ለመሸፈን ብቻ ወደ ሁለት ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር የተጠጋ ወጪ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ በሁለተኛውም የዕትዕ በየዓመቱ ከሁለት ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር በላይ በጀት እንደሚያስፈልገው ተተንብየዋል። ይህንን ጫና ለመቀነስ የሚረዳ ስትራቴጂክ መፍትሔ ለመስጠት የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የአውሮኘላን በረራዎችን የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት በመስጠት ወጭ መሸፈን (cost recovery) ተግባራዊ በማድረግ እንዲሁም ለጋሽ ድርጅቶችን በማሳተፍ በሚቲዎሮሎጂ መሣሪያዎች ምርትና ጣቢያዎች ግንባታ ማፋጠን በዕቅድ ዘመኑ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ በዚህም መሰረት ከተለያዩ የልማት አጋሮች ጋር በመተባበር የኤጀንሲውን የአገልግሎት አሰጣጥ የሚያሰልጡ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ የሀብት ማፈላለግ ስራዎች በዕቅዱ ዘመን የተለየ ትኩረት በመስጠት የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው፡

### 2.1.4. የውስጣዊ (ጥንካሬዎች እና ድክመቶች) እና ውጫዊ ሁኔታ (ምቹ ሁኔታዎችና ስጋቶች) ትንተና

ሰንጠረዥ 1 ውስጣዊ ጠንካራ እና ደካማ ጎን

**ሀ) ጠንካራ ጎን (Strength)**

- በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችና ሲስተሞች ተጠቃሚ መሆን
- በተሰጠው የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የትንበያው ተዐማኒነት መጨመሩ
- ማህበረሰቡ ለሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ያለውን ግንዛቤ ማደግ
- የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማበራከት የተሰሩ የአቅም ግንባታ ሥራዎች

**ለ) ደካማ ጎን (Weakness)**

- የኤጀንሲው የእቅድ፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት ጠንካራ አለመሆን ፣
- መሰረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አቅርቦት አገልግሎትን የሀገሪቱን ስነምህዳር በወከለ መልኩ በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ አለመቻል ፣
- ወቅታዊና ጥራታቸውን የጠበቁ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችል አቅም ውስን መሆን ፣

- ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር ያለው ትስስር መጠናከሩና በዘርፉ የተገኘው ሀብት ለሚቲዎሮሎጂ መሣሪያዎች ማስፋፍያና ለአቅም ግንባታ አስተዋፆ ማድረጉ
- በዓለም አቀፍ እና በአህጉር የተፈጠሩ የአየር ጠባይ ለውጥ ድጋፍ የፋይናንስ ምንጮችን አሟጦ የመጠቀም አቅም እየተገነባ መሆኑ

- ሕብረተሰቡ ስለሚቲዎሮሎጂ ሣይንስና አገልግሎት ያለዉ ግንዛቤ በሚፈለገው ደረጃ አለመዳበር፣
- ትንበያዎች ተጠቃሚዎች በሚፈልጉት ጥራት፣ ጊዜና ቦታ አንጻር በሁሉም ደረጃ በሚፈለገው መጠንና አይነት ተደራሽ አለማድረግ፣
- የኢንፍርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አቅምና ሽፋን

በሁለተኛ ዕትዕ ትግበራ ወቅት ዕቅዱ እንዲከናወን የሚያደርጉ መልካም አጋጣሚዎች እንዳሉ ሁሉ የዕቅዱን ትግበራ የሚያጓትቱ ወይም የሚያደናቅፉ አጋጣሚዎች እንዳሉ ይታወቃል። ስለዚህ ከትግበራው በፊት እነዚህን ምቹ ሁኔታዎችንና ስጋቶች በስፋት መዳሰስ የመልካም አጋጣሚዎችን አዎንታዊ ጎን ለመጠቀምና የስጋቶቹን አሉታዊ ተጽዕኖ የሚቀነስበትን አቅጣጫ ተነድፎዋል።

**ሰንጠረዥ 2 ውጫዊ ምቹ ሁኔታዎችና ስጋቶች**

**ምቹ ሁኔታዎች (Opportunities)**

- ከውሳኔ ሰጪ፣ እና ከባለድርሻ አካላት፣ ጋር የሚደረግ የተቀናጀ ትግበራ ውስንነቶችን መቀነስ ማስቻሉ፣
- የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን የማጠናከር ሥራ የሚደግፉ የተለያዩ የሀብት ምንጮችን መኖር
- በክልል ደረጃ ለህብረተሰብ

**ስጋቶች (Threats)**

- ዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ መሣሪያዎችና መለዋወጫቸውን ለመግዛት የሚያስፈልግ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት እና የውጭ ምንዛሪ የሚያስፈልግ መሆኑ፣
- የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ጥራት ያለው እና ያልተቆራረጠ ለማድረግ ወሳኝ የሆኑ መሰረተ ልማት

አገልግሎት የሚሰጥ የተዘረጋ ያልተማከለ የመንግሥት መዋቅርና አሰራር መኖሩ፣

- እየመጣ ያለው የመሠረተ ልማት መስፋፋት የኤጀንሲውን ተደራሽነት ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑ

- የአየር ጠባይ ተለዋዋጭነትና ለውጥ በዓለም አቀፍና በብሄራዊ ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት መሰጠቱ ለሚቲዎሮሎጂ ሳይንስ ዘርፍ አገልግሎት ፍላጎት መጨመሩ፣ እና የመንግሥት ትኩረትና ድጋፍ መጨመሩ

- በዓለም አቀፍ ለትብብር ማዕቀፋት ከፍተኛ ትኩረት መሰጠቱ፣

- ኤጀንሲው ዓለም አቀፋዊ ልምድና መልካም ተሞክሮ የሚቀስምበት የተለያዩ መድረኮች ላይ የመሳተፍ ዕድል መኖሩ ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላት ጋር የተፈጠሩ የትብብር ግንኙነት መኖራቸው

አገልግሎቶች ለምሳሌ የቴሌኮም እና ኤሌክትሪክ ኔትወርክ መቆራረጥ፣

- ጣቢያ ለማቋቋም፣ ወቅታዊ የጣቢያ የመስክ ቅኝት፣ የመስክ ላይ የመሣሪያዎች ጥገና እና ካሊብሬሽን ስራን ለማከናወን በቂ ተሽከርካሪ አለማግኘት፣

- የባለሙያ ፍልሰት እና ከገበያ አለማግኘት፣

- የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያ ለማስፋፋት የሚሆን ወካይ እና ተገቢ ስፋት ያለው መሬት አለማግኘት፣ የሚመለከታቸው የመስተዳድር አካላት ለነባር ይዞታዎች ህጋዊ ሰነድ አለመስጠትና መውሰድ፣

## 2.2. የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓላማዎች

ሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አላማ አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ለህብረተሰቡ ለማዳረስና ሀገራችንን ከአየር ሁኔታና

ጠባይ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመታደግ ኤጀንሲው ለሚከተሉት ዓላማዎች ተቀምጠዋል

- የሀገሪቱን መልካምድራዊ አቀማመጥ እና የአየር ጠባይ ተለዋዋጭነት በሚገባ የሚወክል ዘመናዊ እና መደበኛ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መረብ በማስፋፋትና በማስተዳደር፣ መረጃ በመሰብሰብ፣ በማደራጀት ፣ በመተንተን እና ጥራቱን በማረጋገጥ ሁሉም ተጠቃሚ በቀላሉ እንዲያገኝ ማድረግ፤
- ወቅቱንና ደረጃውን የጠበቀ አስተማማኝ የአየር ሁኔታና ጠባይ የትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እንዲሁም ዘርፍ ተኮር የምክር አገልግሎት በመስጠት የሀገሪቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማረጋገጥ፤
    - በሚቲዎሮሎጂና ተዛማጅ ሳይንስ ዘርፍ ችግር ፈቺ የሆነ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማካሄድና ሥራ ላይ ማዋል፤
    - የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ለማቀላጠፍ ዘመናዊ ጣቢያዎች፣ የመረጃ ልውውጥ አውታር፣ የመረጃ ማደራጀትና መተንተን፣ የትንበያ እና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እንዲሁም የመረጃ አቅርቦት እና ስርጭት አገልግሎትን ማዘመን፤
    - የለውጥና መልካም አሰተዳደር ሥርዓትን በማጠናከር ሙሉ ቁመና ያለው የለውጥ ሠራዊት በመገንባት የኤጀንሲውን ግቦች ማሳካት

## 2.3. የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች

1. የሀገሪቱን የአየር ሁኔታና ጠባይ በመከታተል ጥራቱን የጠበቀና ወቅታዊ የሆነ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት አስተዋጾ የሚያደርግ የአየር ሁኔታና አየር ጠባይ ትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አገልግሎት ተደራሽነት ከ75% ወደ 85% ማድረስ፤
2. በተለያዩ የሀገሪቱ መልካምድራዊ ቦታዎች የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ ለመሰብሰብ የሚያስችል አሁን ካሉት 1334 የተለያየ ዓይነትና ደረጃ ካላቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ወደ 2600 በማድረስና መረጃ በመሰብሰብ፣ በማጠናቀርና በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ፤
3. ሚቲዎሮሎጂን በሚመለከት ኢትዮጵያ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የገባቻቸውን ስምምነቶች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ፤ (GTS, ICAO, IPCC QMS, RCC, NCC, WMO-ARI)

4. ጥራቱንና ወቅታዊነቱን የጠበቀ የልማት ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ተደራሽነትን ከ70% ወደ 85% ማሳደግ፤
5. ለአየር ትራንስፖርት ደህንነትና ስኬታማነት ዓለም አቀፍ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮጂ አገልግሎት በአውሮፕላን ማረፊያዎች ቁጥር ከ15 ወደ 22 ማድረስ፤
6. የሚቲዎሮሎጂ እና ተዛማጅ ሳይንስ ዘርፎች ላይ ትኩረት ያደረጉና ችግር ፈቺ የሆኑ 36 ጥናትና ምርምር ስራዎችን ማሳተም፤
7. የኤጀንሲውን አገልግሎቶች የማስተዋወቅና ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በማጠናከር የህብረተሰቡን ግንዛቤ 70% ወደ 80% ማሳደግ፣ በኤጀንሲው የሥርዓተ ጾታ ተኮር አሰራርን አጠናክሮ በመቀጠል የሴቶችን እኩል ተጠቃሚነትና ተሳትፎ ከ40 በመቶ ወደ 50 በመቶ ማሳደግ፣ እንዲሁም ኤጀንሲው በሚሰጣቸው የአየር ጠባይ ለውጥ እና መላመድ ጋር በሚሰጡ አገልግሎት የሴቶችን ተጠቃሚነት ማሳደግ
8. በኤጀንሲው የሪፎርምና ልማታዊ መልካም አስተዳደርን በማጠናከር ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት በመስጠት የተገልጋዮችን እርካታ ከ70% ወደ 85% ማሳደግ፣
9. የኤጀንሲውን የሰው ሀይል ፍላጎት የማሟላት እና አቅም ግንባታ ስራዎችን አጠናክሮ በመቀጠል የሰው ሀይል ፍላጎቱ ከ62% ወደ 90% ማሟላት፤
10. ለኤጀንሲዉ የተፈቀደዉን በጀት ወጪ ቆጣቢና ዉጤታማ በሆነ መንገድ ስራ ላይ እንዲዉል በማድረግ የኤጀንሲዉን የመደበኛና የካፒታል የፋይናንስ አፈጻጸም ከ80% ወደ 100% ማሳደግ፤

## 2.4. የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫዎች

### 2.4.1. ጥራቱን የጠበቀ ደንበኛ ተኮር የመሰረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አቅርቦት

ደንበኛ ተኮር መሰረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አቅርቦት የኤጀንሲው አንዱ ዋና ተግባር ነው። ይህ የትኩረት መስክ ለተጠቃሚዎች በዋነኝነት የሚያቀርበው መሠረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ነው። መሠረታዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ማለት

በሚቲዎሮሎጂ መሣሪያዎችና በሰው ተመዝግበው የከባቢ አየር ሁኔታንና ባህርያትን የሚገልጹ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች የሚያጠቃልል ሲሆን ለጥናትና ምርምር ለዕቅድ ለዲዛይን ጥናት የአየር ጠባይ ለውጥን ለማጥናት ወዘተ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው።

### 2.4.2. አስተማማኝ የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና የምክር አገልግሎት

ከብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ዋና ዋና ተግባራት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አግልግሎትን ለተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፎች ማቅረብ አንዱ ነው:: በመሆኑም አሁን እየተሰጠ ያለውን የአንድ ወቅት ቅድሚያ ትንበያን በማሳደግ ሁለት ወቅቶችን አስቀድሞ መተንበይ፣ የተሻሻሉ የትንበያ ሞዴሎች፣ ማኑዋሎችንና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ደህንነቱ ለተጠበቀ፣ መደበኛና ወቅታዊ የሆነ የአውሮፕላን በረራ የሚውል አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት፣ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል የእርሻ ሚቲዎሮሎጂ፣ የውሀና ኢነርጂ ልማትን ለማሳደግ የሚያስችል የሀይድሮ ሚቲዎሮሎጂና ለጤና አጋዥ የሆነ የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና የምክር አገልግሎትን መስጠት ነው፡፡

### 2.4.3. በጥናትና ምርምር የዳበረ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት

የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ አንዱ ቁልፍ ተግባር በሚቲዎሮሎጂና ተዛማጅ መስኮች የጥናትና የምርምር ተግባሮችን ማካሄድ፣ ጠቃሚ ውጤቶችንም በስራ ላይ ማዋል ነው። ይህም በኤጀንሲው ማቋቋሚያ አዋጁ በግልፅ ተካቶ የሚገኝ ነው። በሚቲዎሮሎጂ እና ተዛማች የሳይንስ ዘርፎች የጥናትና ምርምር ዉጤቶች ማለትም አዳዲስ በጥናትና ምርምር የተገኙ ሳይንሳዊ መረጃዎች፣ እውቀቶች፣ ሞዴሎች፣ አዳዲስ የአሰራር ዘዴዎችና ቴክኖሎጂዎችን ለተጠቃሚዎች በማቅረብ አስተማማኝና በመረጃ የተደገፈ አገልግሎት ማቅረብ እንዲሁም ግኝቶችን በማስተዋወቅ አዳዲስ ተጠቃሚዎችን ማፈራት የሚጠበቅበት በመሆኑ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ በኤጀንሲው ትኩራት የሚደረግበቸው የጥናት ዘርፎችን በመለየት ለሚቲዎሮሎጂ

አገልግሎት መሻሻል ሚና በሚኖራቸው የጥናትና የምርምር ዘርፎች ዙሪያ ትኩረት ተሰጥቶዋል፡፡

### 2.5. የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ምሰሶዎች (Pillars)

#### 2.5.1. የመረጃ አቅርቦት ሽፋን፣ጥራት እና ተደራሽነትን ማረጋገጥ

የሚቲዎሮሎጂ መረጃ በመሣሪያዎችና በሰው ተመዝግቦ የከባቢ አየር ሁኔታንና ጠባይ የሚገልጽ ማናቸውም መረጃ ማለት ሲሆን፤ በሀገራችን ክልል በማንኛውም ቦታ እና በዙሪያችን ከገጸ-ምድር አንድ ሜትር ጥልቀት ጀምሮ በከባቢ አየር እስከ 30 ኪ.ሜ ከፍታ ያለውን ማንኛውንም የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ያጠቃልላል። ይህ መረጃ የሚሰበሰበው በመሬት ላይ በሚተከሉ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው ጣቢያዎች (Surface observation stations)፣ ከከፍታ አየር መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች (Upper air observation stations)፣ ከሳተላይት መረጃ መቀበያ ጣቢያ፣ ከራዳር ጣቢያ፣ ከአውቶማቲክ የሚቲዎሮሎጂ መሰብሰቢያ ጣቢያ፣ ከአየር ብክለት መከታተያ ጣቢያዎች፣ ከመብረቅ ስርጭት መከታተያ ጣቢያ አውታር፣ ከአውሮፕላኖች፤ ከአህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የሚቲዎሮሎጂ ተቋሚት ወዘተ... የሚሰበሰቡ መረጃዎችን የሚያጠቃልል ነው።

የመረጃ ሽፋን ወካይነትን ለማረጋገጥ በየአስር ዓመት የሚከለስ የጣቢያ ስርጭት ማስተር ፕላን በማጥናት የአየር ሁኔታ መከታተያ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው መደበኛ እና ዘመናዊ ጣቢያዎች በማስፋፋት፤ በማስተዳደር መረጃ ይሰበሰባል። በዓመት ሁለት ጊዜ የጣቢያ ላይ ቅኝት በማድረግ፣ ጣቢያዎች እና መሣሪያዎች ያሉበት ሁኔታ በመገምገም ማስተካከያ፣ ቅድመ ብልሽት እንክብካቤ እና ድህረብልሽት ጥገና በማካሄድ የመረጃ ክፍተት እንዳይኖር እና ጥራቱ እንዲረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡

የመረጃ ጥራትን ለማረጋገጥ መረጃ መመዝገቢያ መሣሪያዎችን በዓለም የሚቲዎሮሎጂ ድርጅት በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት ከ6ወር እስከ 2 ዓመት በሚሆን የጊዜ ድግግሞሽ ካሊብሬት የማድረግ እና ወቅታዊ ጥገና ማካሄድ ይገባል፡፡ ከደንበኞች በሚቀርብ ጥያቄ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያ ማቋቋም፣ ሚቲዎሮሎጂ መሣሪያዎችና የመሣሪያ ግብዓቶችን ምርት እንዲሁም የሚቲዎሮሎጂ መሣሪያዎች ካሊብሬሽንና ጥገና አገልግሎቶች ኤጀንሲው ለማያስተዳድራቸው ጣቢያዎች አገልግሎት ይሰጣል። በሀገር ውስጥ ለሚቋቋሙ

ማናቸውም አይነት የሚቲዎሮሎጂ መሣሪያ እና ጣቢያ ደረጃው የተሟላ መሆኑን አረጋግጦ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አንድ ጊዜ የሚቲዎሮሎጂ ክስተት ካለፈ በኋላ ወደ ኋላ ተመልሶ መመዝገብ የማይቻል በመሆኑና የአየር ጠባይን ባህሪያት ለማወቅ እና የአየር ጠባይ ለውጥ ጥናት ለማካሄድ የበርካታ ዓመታት መረጃን መጠቀም ስለሚጠይቅ መረጃውን በሀገር ሀብትነት በጥንቃቄ በማዕከል መቀመጥ እና ለትውልድ መተላለፍ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም መረጃውን ከአደጋ በመጠበቅ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና የመረጃ ቋት በማደራጀት እና በመተንተን በቀላሉ ለተጠቃሚዎች ሊቀርብ በሚችልበት መንገድ ማስተዳደር ይገባል፡፡

ከተለያዩ መሣሪያዎች የሚሰበሰቡ መረጃዎች ሥራ ላይ ከመዋላቸው አስቀድሞ ከጣቢያ ጀምሮ በአሥራ አንዱ ቅርንጫፍ ዳሬክቶሬቶች እና በማዕከል በየደረጃው የመረጃ ጥራት ቁጥጥር እና የመረጃ ጥራት ማረጋገጫ ሥርአት ተዘርግቶ በመፈተሽ የጥራት ማረጋገጫ ይደረግለታል፡፡ ጥራታቸው የተጓደለ መረጃዎችም ጥቅም ላይ እንዳይውሉ እና ተመሳሳይ የጥራት ጉድለት እንዳይከሰት የማስተካከያ እርምጃዎች መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

የተለያየ ደረጃ ካላቸው ጣቢያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደ ተጠቃሚው ፍላጎት ተጠናቅረው (Processed data)፣ በሰንጠረዥ መልክ፣ በግራፍ መልክ፣ በካርታ ላይ ተተንትነው፤ በሪፖርት መልክ (statistically, temporally, spatially, and climatologically analyzed data) በባለሙያ ተተንትነው፣ በመጽሐፍና በአትላስ መልክ ተዘጋጅተው በሶፍት ኮፒ እና በወረቀት ለደንበኞች እና ለባለድርሻዎች ይሰራጫሉ።

የመረጃ ክፍተትን ለመሙላት ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበሰቡ መረጃዎችን በማዳቀል እና በሒሳባዊ ቀመር በማዋሃድ ለተጠቃሚዎች ይቀርባሉ ። አገሪቱ በገባችው ስምምነት እና የኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ በሚፈቅደው መሠረት ለዚህ አገልግሎት ከተመረጡ ጣቢያዎች የሚሰበሰቡ መረጃዎች ለዓለም ዓቀፍ ጥቅም ይሰራጫሉ።

### 2.5.2. የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አገልግሎትን ተደራሽ ማድረግ

የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቅቂያ አገልግሎት የአጭር፣ የመካከለኛ ጊዜና የረጅም ጊዜ የአየር ጠባይ ትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረጃዎች እስከ ማሰራጨት (Public Weather Service /PWS) ያሉትን የአገልግሎት ዘርፎች ያካትታል። በተጨማሪም በአጠቃላይ በህብረተሰቡ ላይ አደጋ ሊያመጡ የሚችሉ የአየር ሁኔታና ጠባይ ገፅታዎች ላይ ትኩረት በማድረግ በየቀኑ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን እና ድረገጽ ከሚሰራጩ የአጭር ጊዜ የሚቲዎሮሎጂ ትንበያዎች አንስቶ የመካከለኛ ጊዜ የአየር ሁኔታ ትንበያንና እስከ ወቅታዊና ከዛም ባለፈ የጊዜ እርከን ተዘጋጅተው የሚሰራጩና በተገልጋዮችም በተፈለጉ ጊዜ የሚስተናገዱ የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያዎችን ያጠቃልላል። በመሆኑም ኤጀንሲው የሀገሪቱ የአየር ሁኔታና ጠባይ ክስተቶችንና አዝማሚያዎችን በመከታተል ሳይንሳዊ ልኬቶችንና የትንበያ ሞዴሎችን በመተንተንና በመገምገም የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና የቅድሚያ ማሰጠንቀቂያ አገልግሎቶችን በወቅቱና በብቃት መሰጠትን ተቀዳሚ አድርጎ ይሰራል።

### 2.5.3. የልማት ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ማሻሻል

*ሀ) የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል*

የሃገራችን ግብርና በዝናብ ላይ መሠረት ያደረገ ስለሆነ፤ የአየር ሁኔታና ጠባይ በመከታተል ለዘርፉ የሚሰጥ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ለግብርና ምርትና ምርታማነት ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ በግብርናው መስክ የግብርና ምርትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የግብርና ግብዓቶችን አጠቃቀም፣ ዕለታዊ፣ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊና ወቅታዊ የሰብሎች ዝናብ መጠን ፍላጎት ስርጭትን፣ የዘር ጊዜ፣ የደረቅ ሰሞኖችና ያልተጠበቀ ዝናብ እንዲሁም የሰብል የዕድገት ደረጃ ትንበያ፣ ግምገማና የሰብሎች የውሃ ፍላጎት እርካታ ጠቋሚ መረጃዎች፤ የተቀላጠፈ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ትንበያና ምክር አገልግሎቶች በተጨማሪም የአርብቶ አደርና የከፊል አርብቶ አደር አካባቢን የውሃና ግጦሽ አቅርቦት ሽፋን የሚያግዝ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃና የምክር አገልግሎት በመስጠት የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ለማረጋገጥ ታሳቢ ያደረገ ነው።

በተጨማሪም ከአየር ሁኔታ እና ጠባይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሰብል ተባይና በሽታዎችን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡

የግብርናና የገጠር ልማትን እውን ለማድረግ የአየር ጠባይ እምቅ ሀብትን ማወቅ ተገቢ ነው። በዚህ ረገድ ኤጀንሲው የአግሮክላይማቲክ የእርጥበት ቀጠናዎች ክፍፍል በዞንና በወረዳ ደረጃ ተግባራዊ ሊያደርጉ የሚችሉ ጥናቶችን በማካሄድ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ የምክር አገልግሎቶች ለገጠሩ ሕብረተሰብ ለማዳረስ ታሳቢ ተደርጓል።

በተጨማሪም ለግብርና ልማት መጎልበት አስተዋጽኦ ያላቸው እንደ አማካይ የዝናብ መጠን፣ የዝናብ መለዋወጥ ባህሪ (Rainfall variability)፣ የሙቀት መጠን፣ የትነት መጠን፣ የድርቅ ክስተት ሁኔታ (Drought probability map)፣ ወዘተ ስራዎችን በማጠናከር ለተገልጋዩ በተሸለ ሁኔታ ለማቅረብ ኤጀንሲው ለአርሶ አደርና ለአርብቶ አደሩ የአየር ሁኔታ፣ የአየር ፀባይና የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶችን ተደራሽ ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ ፡ ከሚመለከታቸው የግብርና ዘርፍ ተቋማት ጋር በመቀናጀት የምግብ ዋስትና ማረጋገጥን እና የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያግዝ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ለማቅረብ የትኩረት አቅጣጫው አድረጎዋል፡፡

### ለ) የሀይድሮ ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት

የሃይድሮሚቲዎሮሎጂ ግብአት መሰብሰቢያ ጣቢያዎች መረጃ በመጠቀም የአገሪቱን ተፋሰሶች መሠረት ያደረገ የሀይድሮሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን በመተንተን ከከባድ ዝናብ ክስተቶች ጋር በተያያዘ የጎርፍና ቅፅበታዊ ጎርፍ ክስተቶችን በመከታተል በተፋሰሶችና በንዑስ ተፋሰሶች ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖዎችን በመከታተልና በመተንበይ የውሃውንና ኢነርጂን ዘርፍ ለማገዝ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በሀገሪቱ ተፋሰስና ንኡስ ተፋሰሶች ያለውን የውኃ በጀትን (water balance) ለማቀድ የሚያስችሉ የሃይድሮሚቲዎሮሎጂ ትንተና በማጠናከር፣ ከውኃው ዘርፍ ጋር ለተያያዙ የመሠረተ ልማት ሥራዎች የምክር አገልግሎቶችን በስፋት መስጠት የሚጠበቅ በመሆኑ ከሚመለከታቸው የተፋሰስ ባለሥልጣናት እና የውሃ ዘርፍ ተቋማት ጋር በመቀናጀት የውሀ ሀብት

አስተዳደርና ጎርፍ ትንበያ ሥርዓትን መዘርጋትና በማጠናከር ተጋላጭነትን መቀነስ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡

**ሐ) ለጤናና መድን የሚውል የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት**

በአየር ሁኔታና ጠባይ ምክንያት የሚፈጠሩ የወባና መሰል በሽታዎችን ለመከላከል ለጤናው ዘርፍ አመቺ የሆኑ የአየር ሁኔታና ጠባይ መረጃዎችን በመከታተል የጤናውን ዘርፍ ለማገዝ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ አየር ሁኔታና ጠባይ መሠረት ያደረገ የሰብልና የእንስሳት ሀብት ልማትን ያማከለ የመድህን ሽፋን በማስፋፋት ከአየር ሁኔታ መዛባት ጋር ተያይዞ የሚደርሱ ጉዳቶችን አርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን ለማገዝ ሚና እንደሚኖራው ግንዛቤ ተወስዶዋል፡፡

**2.5.4. ውጤታማ የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መስጠት**

የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ በዓለምአቀፍ፣ በአህጉርና በሀገር ደረጃ ከፍተኛ ዕድገት እያሳየ ይገኛል። በሀገራችን የአቪዬሽን ኢንዲስትሪ በተደራጀና በተቀናጀ አሠራር ከተጀመረ ሰባት አሥርት ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ሲሆን ከፍተኛ ዕድገት እያስመዘገበ ይገኛል። የአቪየሽን ኢንዱስትሪ ለተለያዩ አደገኛ የአየር ሁኔታ ክስተቶች አደጋ የተጋለጠ ነው፡፡ የሁለተኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ሲጠናቀቅ የሀገሪቱ አየር ትራንስፖርት በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ እና ደህንነቱ የተረጋገጠ የኢኮኖሚ ዘርፍ እንደሚሆን እና በሀገራችን የሚገኙ አውሮፕላን ማረፊያዎችም ዓለም አቀፍ ደረጃ ያሟላ የአቪየሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት እንዲሰጡ ይጠበቃል።

በመሆኑም ጊዜውን ለጠበቀ፣ መደበኛና ደህንነቱ ለተሟላ የአውሮፕላን በረራ አገልግሎት (ቅድመ በረራ፣ መንደርደሪያ፣ መነሻ፣ የበረራ መስመር፣ መቃረቢያ እና ማረፊያ የበረራ ሂደቶች) እንዲሁም የአውሮፕላን ጣቢያ ላይ ለሚከናወኑ የበረራ እንቅስቃሴዎች (ground operation and air traffic services) ዕቅድና ትግበራ መሣካት ከሚያስፈልጉ ግብዐቶች አንዱ የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ነው። ደህንነቱና አስተማማኝነቱ የተረጋገጠ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት በሀገሪቱ ተግባራዊ እንዲሆን

የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን በዘርፉ ለተሰማሩ ተጠቃሚዎች /ባለድርሻዎች/ መስጠት የኤጀንሲያችን ተግባርና ኃላፊነት ነው። በዚሁ መሰረት የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት በዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን እና የዓለም የሚቲዎሮሎጂ ድርጅት በጋራ እና በተናጠል የተቀረጹ መመሪያዎች መሰረት ጥራቱንና ጊዜውን የጠበቀ ኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰብሰብና ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣ እንዲሁም ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ፣ መግለጫና የምክር አገልግሎት በመስጠት፣ የአቪየሽን የበረራ ደህንነትን አስተማማኝ ለማድረግ የአቭየሽን ሚቲዎሮሎጂ መሰረተልማት የሚሟላት ስራ በሁለተኛው የዕትዕ ውስጥ ልዩ ትኩረት የተሰጠው ተግባር ይሆናል።

### 2.5.5. ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ስራዎችን መተግበር

የአየር ሁኔታና ጠባይ በተለያዩ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖና ለዘርፎቹ እድገት የሚያበረክቱትን ድርሻ በሚገባ ለማወቅና ለመጠቀም የሚቲዎሮሎጂ ጥናትና ምርምር ማካሄድ ወሳኝ ተግባር ነው። የሚቲዎሮሎጂ የሳይንስ ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ብዙ ጥናቶች የሚያስፈልጉት ሲሆን፣ በተለይ ሀገራችን በምትገኝበት የሀሩር ክልል በቂ ጥናት ያልተካሄደ እና የአየር ጠባይና ሁኔታው ከፍተኛ ተለዋዋጭነት ያለው በመሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ጥናትና ምርምር በስፋት ማካሄድ ያስፈልጋል። የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ተጠቃሚዎችን መሰረት ያደረገ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ለመስጠት እንዲቻለው ዘርፍ ተኮር የሚቲዎሮሎጂ ጥናትና ምርምር ተግባራትን ማከናወን ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡

የአየር ጠባይ ለውጥ በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ትኩረት ካገኙት ዓለም አቀፋዊ አጀንዳዎች መካከል አንዱ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ በአየር ጠባይ ለውጥ ምክንያት ሊደርሱ የሚችሉ የልማት መሰናክሎችን በተመለከተ ጥናትና ምርምር በማካሄድ ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መንገድ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን እንዲያቀርብ በተባበሩት መንግሥታት የአካባቢ ድርጅት (UNEP) እና የዓለም የሚቲዎሮሎጂ ድርጅት (WMO) በጋራ ስምምነት የተሰየመው አካል በይነ መንግሥታዊ የአየር ጠባይ ለውጥ ፓኔል (Inter Governmental Panel on Climate Change (IPCC)) ነው። የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የዚህ

በተባበሩት መንግሥታት ለተሰየመው በይነ መንግስታዊ አካል ለኢትዮጵያ ተጠሪ እንዲሆን በመንግሥት ውሳኔ የተወከለ መሆኑ ይታወቃል። በዚህ ዘርፍ በአገራችን ላይ በአየር ጠባይ ለውጥ ተጽእኖ ምክንያት ሊደርሱ የሚችሉ የእድገት መሰናክሎችን ለይቶ ለማስቀመጥ የሚያስችሉ የአየር ጠባይ ለውጥ ጥናትና ምርምር ተግባራትን ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህ ዘርፍ የሚከናወኑ የአየር ጠባይ ለውጥ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ለአጭር ለመካከለኛና ለረጅም ጊዜ አገራዊ ልማታዊ እቅዶችን ለመቅረጽም ሆነ ለመተግበር እንደ አንድ አጋዥ የመረጃ ምንጭና ግብአት በመሆን ለውሳኔ ሰጭዎች አስፈላጊውን የምክር አገልግሎት ድጋፍ ማቅረብ ይጠበቅበታል። በተጨማሪም የአገራችን ቁልፍ የእድገት ስትራቴጂ ለሆነው ለአየር ጠባይ ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ኢኮኖሚ ስኬት በኤጀንሲው በኩል የሚቀርቡ የአየር ሁኔታና ጠባይ አገልግሎቶችን ለማጠናከር ያስችላል። ኤጀንሲው በቅርብ ዓመታት ካቋቋማቸውን የአየር ብክለት መከታተያ ጣቢያዎች የሚገኙ መረጃዎችን በማጥናት የአየር ብክለት ደረጃ ጥናት በማድረግ የጥናት ሰነድ ማቅረብ እና የፖሊሲ አቅጣጫ ላይ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በሀገራችን በሁሉም ዘርፍ ልማታዊ እድገትን ለማፋጠን በመንግሰት የተቀየሰውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተከተለና ዘለቄታዊ የኢኮኖሚ ዕድገትን በአስተማማኝ መልኩ ለማረጋገጥ ዕገዛ ለማድረግ የሚያስችል ዘርፈ ብዙ የጥናትና ምርምር ስራዎች ማካሄድ ከአሁኑ በተሻለ መንገድ የተጠናከረ ሊሆን ስለሚገባው ትኩረት ተሰጥቶታል።

### 2.5.6. ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ በማዋል የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት አሰጣጥን ማሳለጥ

የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን በብቃት ለመተግበር ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል ሊታለፍ የማይገባ ጉዳይ ነው። አገልግሎቱ መረጃ መሰብሰብ፣ መተንተን፣ መተርጎም እና መተንበይን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በእያንዳንዱ የሥራው ሂደት ውስጥ በዓይነታቸው የተለያዩ ነገር ግን የተገናኙ በርካታ የኤሌክትሪካል/ኤሌክትሮኒክስ ኢንጂነሪንግ፣ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT፣ የጂ.አይ.ኤስ. እና ሌሎች ቴክኖሎጂዎችን በስፋት ይጠቀማል።

የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ለመሰብሰብ የምንጠቀምባቸው የመረጃ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በቁጥር በርካታ እና እያንዳንዳቸው የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን የሚጠቀሙ ሲሆኑ በሰው የሚነበቡ እና ሰው አልባ ሆነው መረጃ የሚሰበስቡ ናቸው። በመደበኛ ጣቢያ የሚገኙ ራስ መዝጋቢ (self recording) መሣሪያዎች በርካታ የመካኒካል ኢንጂነሪንግ ቴክኖሎጂ ይጠቀማሉ። ዘመናዊ ከሆኑት ሰው አልባ መሣሪያዎች መካከል አውቶማቲክ የመረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያ (AWS)፣ የከፍታ አየር መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያ (Upper Air Station)፣ የአየር ብክለት መከታተያ ጣቢያ (Air Pollution Monitoring Station)፣ የመብረቅ መከታተያ ጣቢያ (Lightening Detection Stations)፣ የከፍታ ንፋስ መከታተያ (Wind-Profiler)፣ በአውሮፕላን ውስጥ ከተገጠሙ የሚቲዎሮሎጂ መሣሪያዎች መረጃ የመሰብሰብ ቴክኖሎጂ (Aircraft Meteorological Data Relay: AMDAR)፣ ሪሞት ሴንሲንግ ጣቢያዎች (የራዳር ጣቢያ እና የሳተላይት ጣቢያ) ይገኙበታል። እነዚህ ዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች የኤሌክትሪክ፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ የኮምፒዩተር ሳይንስ እና የኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂዎችን በአንድ ላይ አጣምረው የሚጠቀሙት ናቸው።

በዓለም የሚቲዎሮሎጂ ድርጅት መመሪያ መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በየጊዜው እየተፈተሹ የጥገና እና የካሊብሬሽን ሥራ እንዲደረግላቸው ያዛል። ይህንን ለመተግበር የተለያዩ የካሊብሬሽን ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። ለአየር ብክለት ጣቢያዎችንም መረጃ ለመተንተን የሚያግዝ የኬሚስትሪ ላቦራቶሪ ያስፈልጋል። ለካሊብሬሽን ላቦራቶሪ ከሚያስፈልጉ መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች ውስጥ (Thermometer Chamber, Pressure and Humidity Chambers, Wind Tunnel, Standard and Reference Instruments, Stationary and Mobile Calibration Laboratories, Air Pollution Analyzers) ጥቂቶቹ ናቸው።

የሚቲዎሮሎጂ ክስተት ተፈጥሯዊ እንደመሆኑ መጠን በፖለቲካዊ መስተዳድር ክልሎች እና በጊዜ አይወሰንም። ከጊዜ አኳያ ለሃያ አራት ሰዓት ሳይቋረጥ በዓለም ሁሉ በተመሳሳይ ሰዓት የሚሰበሰብ እና በተቻለ ፍጥነት ወደ ማዕከል በመሰብሰብ የሚከማች፣ የሚተነተን እና የሚተነበይ ነው። ይህንን ለማሳካት እጅግ ዘመናዊ የሆነ የመረጃ መለዋወጫ መረብ ቴክኖሎጂ ያስፈልጋል።

በሀገራችን መረጃ ከጣቢያዎች ለመሰብሰና ለመለዋወጥ የመገናኛ ሬዲዮኖችን፣ ስልኮችን፣ GPRS፣ VSAT እና የኮምፒዩተር ኔትወርክ (LAN/WAN) ጥቅም ላይ ውሏል። የዓለም የሚቲዎሮሎጂ ድርጅት Global Telecommunication System (GTS) የተሰኘ የመገናኛ አውታር ዘርግቶ አባል ሀገራቱ ወቅታዊ መረጃ ለመለዋወጥ አስችሏቸዋል። ኤጀንሲው ለሚሰጠው የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አገልግሎት አስተማማኝ ሁለትዮሽ የመረጃ መለዋወጫ አውታር የሚያስፈልገው በመሆኑ VSAT ቴክኖሎጂን በስፋት መጠቀም ይገባል፡፡

የተለያዩ ደረጃ እና ዓይነት ካላቸው ጣቢያዎች የሚሰበሰቡ መረጃዎችን በቀላሉ ለተጠቃሚ ለመስጠት እና ሙያው ለሚጠይቀው ማንኛውም ተግባር ለማዋል መረጃዎቹን በዘመናዊ የመረጃ ማደራጀትና ማከማቸት ቴክኖሎጂ ማከማቸት ይገባል። ለዚህ ተፈፃሚነት በሀገራችን ORACLE and GIS ላይ መሠረት ያደረገ Climate Data Base Management System ጥቅም ላይ ውሏል። የፎቶ፣ የስካኒንግ እና የዲጂታይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ከምዕተ-ዓመት በላይ ዕድሜን ያስቆጠሩ በወረቀት ላይ የሰፈሩ መረጃዎችን ወደ ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ በመቀየር መረጃዎች ለረዥም ዓመታት ሳያበላሹ ማከማቸት እና ለተጠቃሚዎች ማቅረብ የሚያስችሉ መረጃ ማከማቻ ቴክኖሎጂዎችን በጥንቃቄ በመምረጥ መረጃዎቹን ከመውደም መታደግ /Data Rescue/ን ሥራ እየተተገበረ ይገኛል።

የሚቲዎሮሎጂ መረጃ በገጸምድር ሰፌ ሽፋንን እንዲሁም በከፍታ አየር እና በተለያዩ ጊዜያት የሚሰበሰብ ሲሆን መረጃዎቹን በግልጽ ለመተንተን እና ለመገንዘብ አራት ዳይሜንሽን (X,Y,Z,T) መረጃን ለመተንተን አመቺ የሆኑ የጂኦግራፊክ ኢንፎርሜሽን ሲስተም (GIS) ቴክኖሎጂ መጠቀም ያስፈልጋል። በተጨማሪም ጥሬ መረጃዎችን ለመተንተን የሚያግዙ የስታቲስቲካዊ መተነተኛ ቴክኖሎጂዎችንም ጥቅም ላይ ውለዋል። በሀገራችን ያሉት ጣቢያዎች ስርጭት ሁሉን ቦታ የሚደርስ አይደለም። ይህን ክፍተት ለመሙላት የሳተላይት መረጃን ከገፀ ምድር ጣቢያ መረጃ ጋር ማዳቀል ቴክኖሎጂ በኤጀንሲው እየተተገበረ ይገኛል።

የአየር ሁኔታ ትንበያ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚከናወን ሲሆን፣ ስታቲስቲካዊ፣ ዳይናሚክ እና አሃዛዊ የትንበያ ሞዴሎችን በመጠቀም

የሚከናወኑት ዋናዎቹ ናቸው። በሀገራችን የአጭር ጊዜ ትንበያን ለማከናወን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አሃዛዊ የትንበያ ሞዴሎችን (Numerical Weather Prediction: NWP) ጥቅም ላይ ውላል። ይህ ቴክኖሎጂ ከፍተኛ የመቀመሪያ አቅም ያለው ኮምፒዩተር (High Performance Computing: HCP) አቅም መገንባትን የሚፈልግ ነው።

የአየር ሁኔታ መረጃን መነሻ በማድረግ የአዝዕርት ፣ በእንስሳት፣ በውሃ ዘርፍ፣ በጤና ዘርፍ የሚያስከትሉትን አዎንታዊ እና አሉታዊ ተጽዕኖዎችን የሚያመላክት ወቅታዊ መረጃ ለመተንተን የተለያዩ ዘርፍ ተኮር ሞዴሎችን ጥቅም ላይ ውለዋል። የአየር ጠባይ ለውጥ በሀገራችን ያለበትን ደረጃ ወደፊት ምን እንደሚመስል ለማወቅና በየዘርፉ የሚያስከትለውን ጉዳት ለማወቅ የተለያዩ የአየር ጠባይ ለውጥ ሞዴሎች፣ climate change trend analysis tools, Climate Projection and downscaling ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ ውሏል።

የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ለህብረተሰቡ ለማድረስ በዘመናዊ መቅረጸ ድምጸ ምስል ስቲዲዮ በመጠቀምና በመቅረጽ በሬዲዮ እና በቴሌቪዥን በተለያዩ ቋንቋዎች እየተሠራጨ ይገኛል። ለዚህም የተለያዩ የድምጽና ምስል ቀረጻ፣ የሚክሲንግ እና ኤዲቲንግ ቴክኖሎጂዎችን ጥቅም ላይ ውለዋል። ካሜራዎች፣ ሚክሰሮች፣ ኤዲቲንግ ሶፍዌርና ሃርድዌሮች ጥቅም ላይ የዋሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ናቸው። ተንቀሳቃሽ ስልኮች፣ ዘመናዊ ድረገጽ እና ማህበራዊ ሚዲያዎችም የሚቲዎሮሎጂ መረጃን ወደ ተጠቃሚዎች በአፋጣኝ ለማድረስ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አላቸው።

አሁን ባለንበት ዘመን የቴክኖሎጂ ተለዋዋጭነት ከመቼውም በላይ ፈጣን በመሆኑ አንዱን ቴክኖሎጂ አሟጠን ሳንጠቀም ወደ ሌላው ቴክኖሎጂ ለመሸጋገር የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ቢችሉም ከወቅቱ ጋር ፈጥኖ እራስን በማላመድ እና ቀጣይነት ያለው አቅም በመገንባት አገልግሎቱ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ በሁለተኛው ዕትዕ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል።

### 2.5.7. የሰው ሃብት ልማት ና የማስፈጸም አቅም መገንባት

የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ለሀገራችን የምጣኔ ሀብት፣ በማህበረሰብ ዕድገትና ልማት ላይ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው:: በመሆኑም አገልግሎቱ ደረጃውን የጠበቀ፣ አሰተማማኝና ተደራሽነቱ የሰፋ ከማድረግ አኳያ

በሚቲዎሮሎጂ ሳይንስና ተዛማጅ ዘርፎች የሰለጠነና ብቃቱ የተረጋገጠ የሰው ኃይል ወሳኝ ነው፡፡

በዚህም መሠረት በሁለተኛው ዕትዕ የሚከተሉትን ዋና ዋና የአቅም ግንባታ ሥራዎች ታቅደዋል፣

- ❖ የሰው ሀብት ልማቱን ለማበራከትና ለማስፋት በራሱ አቅም በተለያየ ደረጃ የሚቲዎሮሎጂ ቴክኒሽያኖችን ማሰልጠን፣ በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ባሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር ትስስር በመፍጠር ከመጀመሪያ ዲግሪ እስከ ሶስተኛ ዲግሪና የተለያዩ አጫጭርና ስፔሻላዜሽን ስልጠናዎች በማካሄድ ክፍተቶችን መሙላት፤
- ❖ በአዳዲስ ቴክኖሎጂና የጥናትና የምርምር ግኝቶች በመስኩ ከሌሎች ዘርፎች ጋር አብሮ ለመጓዝ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና አቅም ግንባታ ሥራዎችን አቅዶ መሥራት፤
- ❖ ለመሰኩ የሚያስፈልጉ ባለሙያዎችን በተለያየ ደረጃ የሙያ ብቃት ማረጋገጥ፤
- ❖ የተሰጡ የትምህርትና ስልጠናዎችን በኤጀንሲው አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያመጡትን ለውጥ በመገምገም ለቀጣይ ማሻሻያነት ማዋል፤
- ❖ የትምህርትና የስልጠና መመሪያዎች ማኑዋሎችና ደንቦችን ማጥናት፣ በስራ ላይ ሲዉሉ አፈጻጸሙን መከታተል፤
- ❖ የተቋሙን የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ከአገሪቱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ጋር በማጣጣም ወቅታዊ ማድረግ፤

### 2.5.8. የሪፎርምና መልካም አስተዳደር ስራዎችን መተግበር

ጠንካራ የማስፈፀም አቅም ያለው ፈጻሚ ለመፍጠር፣ ግልፅነትን የማስፈንና ኪራይ ሰብሳቢነትን ከምንጩ የማድረቅና ተሳትፎን የማረጋገጥ አቅጣጫዎች በመያዝ 2ኛውን ዕትዕ ከሪፎርምና መልካም አስተዳደር አኳያ ሙሉ ቁመና ያለው የለውጥ ሠራዊት ለመገንባት ተጠናክሮ ለመሥራት ታቅዷል፡፡ በዚህም መሠረት፡-

- ❖ የሰው ኃይል የመፈጸም ብቃትን ከማሳደግ አንፃር ለኤጀንሲው ሰራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአቅም ግንባታ ሥራዎች

- ❖ አደረጃጀትና አሠራር የማሻሻልና ቀጣይነት ያለው የለውጥ ኮሙኒኬሽን ሥራዎች
- ❖ የግልጽነትና የተጠያቂነት አሠራርን በማስፈን የኪራይ ሰብሳብሳቢነት አመለካከትና ተግባራትን ለመቀነስ በየደረጃው የተጠናከሩ ሥራዎች
- ❖ የኤጀንስው አገልግሎት ተጠቃሚዎች ተሳትፎ የሚጠናከርበትና ከኤጀንሲው ጋር የተፈጠረውን ቋሚ የግንኙነት መድረክ አጠናክሮ በመቀጠል የሚገኙትን ግብረ መልሶች ለአገልግሎት ማሸሻያነት ማዋል፣
- ❖ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየትና መንስኤያቸውንና መፍትሂያቸውን በማመላከት ወደ ተግባር በመግባት ችግሮቹን ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የጎላ ሚና መጫወት፤
- ❖ የለውጥና የሪፎርም መሣሪያዎች በኤጀንሲያችን ተግባራዊ መሆናቸውን የማረጋገጥ ስራዎች በዕቅድ ዘመኑ ትኩረት የተሰጠው ተግባራት ናቸው፡፡

### 2.5.9. ዘርፈ ብዙ (የወጣቶችና ሴቶች ተጠቃሚነት ማረጋገጥ)

የሴቶችን በፖለቲካ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አኳያ ሴቶች በእድገት በቅጥርና በትምህርት ልዩ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንጻር ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችንና የኃይል ጥቃቶችን ለመከላከል የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎችን በስፋት ለመስራት ትኩረት ተሰጥቷል። በዚህም መሰረት የሚከተሉት ዋናዋና ተግባራት ለ2ኛው ዕትዕ ታቅደዋል፣

- ❖ ሴቶችና ወጣቶች በአየር ሁኔታና ጠባይ መለዋወጥና መዛበት ጋር በተያያዘ በእጅጉ የሚጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች በመሆናቸው የሚሰራው ሥራ ይህን ታሳቢ በማድረግ መተግበር፡
- ❖ የሴቶችና የወጣቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፣ የስርአተ ጾታ ጉዳዮች በዕቅድና በትግበራ መካተታቸውን መከታተልና ማረጋገጥ በዘርፉ የወጡ ፖሊሲዎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ከሥርዓተ ፆታ አንፃር እንዲቃኙ ማድረግ፣

- ❖ ከሥርዓተ ፆታ አኳያ ሃገሪቷ ተቀብላ ያፀደቀቻቸውን ድንጋጌዎች የድርጊት መርሃ ግብር በመንደፍ ከዘርፉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ተግባራዊ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- ❖ በኤጀንሲው ሥራዎች የሥርዓተ ፆታ ጉዳዮች እንዲካተቱ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ አፈፃፀሙን መከታተልና ክፍተቶችን እየለዩ፣ ተገቢውን ግብረ መልስ መስጠት፣
- ❖ በኤጀንሲው ተግባራዊ የሚሆኑ ኘሮግራሞች/ኘሮጀክቶች እንደአግባብነታቸው ሥርዓተ ፆታ ተኮር መሆናቸውን በመከታተል ተገቢውን የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት ፣

2.5.10. **የአረንጓዴ ልማት ትግበራ ዕቅድን ማሳካት**

የአየር ጠባይ ለውጥ መገለጫ ባህሪያቱ መካከል ዋቂቶቹ፣ የአየር ሙቀት መጨመር፣ የዝናብ ስርጭት መዛባት የአየር ጠባይ ተለዋዋጭነት መባባስ፣ የአደገኛ የአየር ሁኔታዎች ክስተት መጨመር እና ለመተንበይ ይበልጥ አስቸጋሪ መሆን ናቸው። ለአየር ጠባይ ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ከአየር ጠባይ ጋር መላመድ ሆነ ለአየር ጠባይ ለውጥ ስርአት እንቅስቃሴዎች የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ቁልፍ እና የማይተካ ሚና ያለው በመሆኑ በርካታ ሥራዎችን ሊሠራ ይገባል። ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል፡-

- ❖ የአየር ጠባይ ለውጥ መገለጫዎችን በመረጃ በማስደገፍ ህብረተሰቡ ትክክለኛና ሳይንሳዊ መረጃ እንዲያገኝ ማድረግ፣
- ❖ ለረጅም ጊዜ የሰበሰባቸውን የአየር ጠባይ መረጃን በመተንተን እና በማጥናት የአየር ጠባይ ለውጥ መገለጫ ዝርዝር መረጃ በማደራጀት እና ማሰራጨት፣ ከፍተኛ የአየር ጠባይ ለውጥ እየታየባቸው ያሉ ቦታዎች እና የለውጡን ደረጃና ዝርዝር ባህሪይ በመለየት ከአየር ጠባይ ለውጥ ጋር የመላመድ ሥራውን ማገዝ፣
- ❖ የአየር ጠባይ ለውጡ ወደ ፊት በተለያዩ የሀገራችን ቦታዎች ምን መልክ እንደሚኖረው በማጥናት እና መረጃ በማዘጋጀት ማሰራጨት፣ ከአየር ጠባይ ጋር በመላመድ ለመኖር በሚደረግ ጥረት እና የልማት አቅጣጫ ላይ መረጃ መሠረት በማድረግ የምክር አገልግሎት መስጠት፣

❖ የአየር ጠባይ ለውጥ መረጃ በማዘጋጀት የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ለለውጡ ያላቸውን ተጋላጭነት መጠን ማጥናት፤

❖ በአየር ጠባይ ለውጥ ምክንያት የሚከሰቱ የአየር ጠባይ ተለዋዋጭነት እና አደገኛ የአየር ሁኔታዎችን በጥልቀት ለመከታተል እንዲሁም አስቀድሞ በመተንበይ የመከላከል እና የማላመድ እርምጃ መውሰድ ይቻል ዘንድ የአገልግሎቱን ተደራሽነት ማሳደግ እና ብቁ ሆኖ መገኘት፤ ይህንንም ዘመናዊ የአየር ሁኔታ መከታተያ ጣቢያ በማስፋፋት፤ የትንበያ አቅምን በማሳደግ እና ወቅታዊ መረጃን ወደ ተጠቃሚ በማድረስ ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት፤

❖ ለታዳሽ ኃይል መሠረት የሆኑ የንፋስ፣ የፀሐይ ብርሃን፣ እንዲሁም የዝናብ ታሪካዊ መረጃዎችን እና ትንበያዎችን በጥራት ማደራጀት

### 2.5.11. ኮሙኒኬሽን እና የተቋሙን በጎ ገጽታ መገንባት

➢ በኤጀንሲው አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግና ከአገልግሎታችን ተጠቃሚዎች ጋር መካከል መልካም ግንኙነት እንዲዳብርና የኤጀንሲው መልካም ገጽታ እንዲጎለበት የውይይትና ምክክር መድረኮችን፣ ኤግዚብሽኖችን ማደራጀትና ለጉብኝት ክፍት የማድረግ ሥራዎችን ማስፈፀም፣

➢ ኤጀንሲውን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የሚዲያ ሞኒተሪንግና የከባቢያዊ ሁኔታ ቅኝት ሥራዎችን ማከናወን፣ ትንተና ማዘጋጀት እንዲሁም የተጠቃሚዎችንና ባለሙያዎችን አስተያየት ማሰባሰብ፣ መተንተንና ውጤቱንም ለበላይ ሀላፊ ማቅረብና በአፈፃፀሙ ዙሪያ ግብረመልስ መስጠት፣

➢ በኤጀንሲው ዕቅድ አፈፃፀም፣ አገልግሎት አሰጣጥ፣ አጠቃላይ እንቅስቃሴዎችን፣ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ለማስተዋወቅ በ15የሚዲያ ተቋማት፣ 10 መፅሄቶችንና 5 ብሮሸሮችን በመጠቀም መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግ እንዲሁም 5 የሬዲዮንና የቴሌቪዥን ፕሮግራም ዝግጅቶችን (Documentary Films) ማቀድ፣ ማዘጋጀት፣ በሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ ማድረግ፣

- የኤጀንሲውን የፎቶግራፍ፣ ኦዲዮና ቪዲዮ ቀረፃና ህትመት እንደዚሁም አርማ ዲዛይንና የድረ ገጽ አስተዳደር ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ፣
- ያልተጠበቁ ክስተቶች/ቀውስ/ በሚያጋጥምበት ወቅት ከሚመለከታቸው የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በመመካከር መረጃ ማሰራጨትና የማረጋጋት ተግባር ማከናወን፣
- የኤጀንሲውን አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነት 5 ጊዜ መገምገምና ማጥናት፣ የአገልግሎት አሰራሩ የሚሻሻልበትን አቅጣጫ መቀየስ፣ ጥናቱ ተግባራዊ የሚሆንበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- በኤጀንሲው የመልካም አስተዳደር ችግሮች አፈታተ ዙሪያ የተገኙ ውጤቶችን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ
- የውጭ ግንኙነት እና የዓለም አቀፍ ግንኙነት ተግባራትን በተሟላ መልኩ መከወን

## 2.6. የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መርሀ ግብር

### 2.6.1. የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ዝርጋታ እና መረጃ አቅርቦት ጥራትና ተደራሽነት ማረጋገጥ ዕቅድ

| | የሚከናወኑ ተግባራት | መለኪያ | መነሻ (2007) | የሚከናወኑበት ዓመት 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ.የገጸምድር መደበኛ እና ዘመናዊ (አውቶማቲክ) የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች | | | | | | | | | |
| 1 | የሣይኖፕቲክስ ጣቢያ ማቋቋም | በቁጥር | 18 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 28 |
| 2 | አብይ ጣቢያዎች ማቋቋም | በቁጥር | 173 | 8 | 10 | 10 | 10 | 10 | 221 |
| 3 | 3ኛ ደረጃ ጣቢያዎች ማቋቋም | በቁጥር | 627 | 40 | 40 | 30 | 27 | 25 | 789 |
| 4 | 4ኛ ደረጃ ጣቢያዎች ማቋቋም | በቁጥር | 403 | 50 | 100* | 100* | 100* | 100* | 853 |
| 5 | የሣይኖፕቲክስ ጣቢያ ማቋቋም | በቁጥር | 18 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 28 |
| ለ. ዘመናዊ (አውቶማቲክ) የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች | | | | | | | | | |
| 1 | አዲስ በሚቋቋሙ የከፍታ አየር ጣቢያ | ቁጥር | 2 | 1 | - | | - | - | 3 |
| 2 | አዲስ የሚተከሉ የአየር ብክለት ጣቢያዎች | በቁጥር | 1 | 1 | - | 1 | - | | 3 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | አዲስ የሚተከሉ የራዳር ጣቢያዎች | በቁጥር | 0 | 1 | - | - | 1 | - | 2 |
| 4 | Lightning Detection ጣቢያዎች ማቋ | በቁጥር | 0 | - | - | 10 | 12 | 10 | 32 |
| 5 | Aircraft Meteorological Data Relay ሲስተም ዝርጋታ | በቁጥር | 0 | - | 1 | - | - | - | 1 |
| 6 | Lysi Meter/ Neutron Prob | በቁጥር | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 5 |
| 7 | Spec. Agromet (AWS) | በቁጥር | 0 | 20 | 50 | - | - | - | 70 |
| 8 | Automatic Weather Station (AWS) ማቋቋም | በቁጥር | 107 | 100 | 70 | 120 | 120 | 113 | 630 |
| 9 | የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ መሣሪያዎችና ሲስተሞች ተከላ (AWOS/AVIMET/ SADIS/ | በቁጥር | 1/4/1 | -/6/3 | 1/-/- | -/-/- | -/3/- | 4/6/- | 5/9/4 |
| 10 | Mobile phone based dissemination tool ስራ ማዋል | በመቶኛ | 0 | | | 50% | 50% | - | 100 |

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ተግባራት | መለኪያ | መነሻ | የሚከናወኑበት ዓመት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | (2007) | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | ድምር |
| 6 | ኤጀንሲው ፈቃድ እየሰጣቸው ከሚቋቋሙ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መረጃዎችን መሰብሰብና ማደራጀት | በመቶኛ | 20% | 25% | 30% | 40% | 50% | 60% | 60% |
| 7 | የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን መሰብሰብና በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ (CLIDATA) ማደራጀት እና በሶፍት እና ሃርድ ኮፒ ጥራት ቁጥጥር ማድረግ | ቁጥር | 1327 | 220 | 272 | 262 | 259 | 250 | 2590 |
| 8 | GIS ፋሲሊቲ ላቦራቶሪ ማቋቋም | በመቶኛ | 0 | - | | 20 | 60 | 20 | 100 |
| 9 | የተለያዩ ኤለመንቶችን የአየር ጠባይ መረጃ (Climate series) በማዘጋጀት ማሳተም | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 6 |
| 10 | የመረጃ መለዋወጫ አውታር (GTS) መዘርጋት | በመቶኛ | 0 | - | 30% | 60% | 10 | - | 100 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | በ GTS ከሳይኖፕቲክ ጣቢያዎች መረጃ ማስተላለፍ | በመቶኛ | 70 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 85 |
| 12 | WMO Cg & EC ላይ መሳተፍና (GFCS, ) መተግባር | በቁጥር | 80 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 95 |
| 13 | WMO Cg & EC ላይ መሳተፍና (GFCS, ) መተግባር | በቁጥር | 80 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 95 |
| 14 | የQMS (ISO-9001-2015) ተግባራዊ ማድረግ | በመቶኛ | 0 | 0 | 0 | 25% | 75% | | 100 |
| 15 | የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ ባለሙይዎችን የብቃት ማረጋገጫ ስርአትን ተግባራዊ ማድረግ | | | | | | | | |

### 2.6.2. የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ዕቅድ

**ግብ 3. የሀገሪቱን የአየር ሁኔታና ጠባይ በመከታተል ጥራቱን የጠበቀና ወቅታዊ የሆነ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት አስተዋጾ የሚያደርግ የአየር ሁኔታና አየር ጠባይ ትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አገልግሎት ተደራሽነት ከ75% ወደ 85% ማድረስ**

| ተ.ቁ | ሚከናወኑ ተግባራት | መለኪያ | መነሻ | የሚከናወኑበት ዓመት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | (2007) | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | ድምር |
| 1 | ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የትንበያ ሞዴሎችንና ውጤቶችን ወደ ክልል፣ ዞንና ወረዳ በመቀየር (Down Scaling) የትንበያን አቅምን ማሳደግ | በመቶኛ | 70 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 80 |
| 2 | የተሰጡ የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አገልግሎቶች ተደራሽነት ማሳደግ | በመቶኛ | 75 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 85 |
| 3 | በብዙሀን መገናኛ የአየር ሁኔታና የአየር ጠባይ መረጃዎችን ለህብረተሰቡ ማሰራጨት | በቁጥር | 60 | 8 | 8 | 8 | 8 | 8 | 100 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | የአየር ጠባይ መጽሔት ማዘጋጀት | ቁጥር | 16 | 16 | 16 | 16 | 16 | 16 | 96 |
| 5 | ለአንድ ወቅት የሚሰጠውን የወቅት ትንበያ ሁለት ወቅቶች አስቀድሞ በመተንበይ የቅድመ ጥቆማን አቅም በማጠናከር ሊከሰቱ የሚችሉ የአየር ጠባይ ተለዋወጭነትን 75% መተንበይ መቻል | በመቶኛ | 0 | 63 | 3 | 3 | 3 | 3 | 75 |
| 6 | የቅርንጫፍ ሚቲዎሮሎጂ ዳይሬክቶሬቶች የአካባቢያቸውን የወቅት ትንበያ በዞንና በወረዳ ደረጃ ለመስጠት እንዲችሉ ማብቃትና የሚሰጡ ትንበያዎች ትክክለኛነት 80% ማድረስ | በመቶኛ | 70 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 80 |
| 7 | የአጭር ጊዜ የአየር ሁኔታ ትንበያዎችን አስተማማኝነት 85% ማድረስ | በመቶኛ | 75 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 85 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | የመካከለኛና የረጅም ጊዜ አየር ጠባይ ትንበያ አስተማማኝነትን 85% ማድረስ | በመቶኛ | 80 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 85 |
| | 2.6.3. የልማት ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ዕቅድ | | | | | | | | |
| ግብ 4. ጥራቱንና ወቅታዊነቱን የጠበቀ የልማት ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ተደራሽነትን ከ70% ወደ 85% ማሳደግ፤ (Based on survey study on access | | | | | | | | | |
| 1 | የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ | በመቶኛ | 70 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 85 |
| 2 | የውሃ ሚቲዎሮሎጂ የምክር አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ | በቁጥር | 60 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 70 |
| 3 | በጤናው ዘርፍ የአገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ | በመቶኛ | 70 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 80 |

| ተ.ቁ | ሚከናወኑ ተግባራት | መለኪያ | መነሻ | የሚከናወኑበት ዓመት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | (2007) | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | ድምር |
| | 2.6..4. የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት | | | | | | | | |
| | ግብ 5. ዓለም አቀፍ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮጂ አገልግሎት በአውሮፕላን ማረፊያዎች ቁጥር ከ15 ወደ 22 ማድረስ፤ | | | | | | | | |
| 1 | የአራት ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያዎ ችየኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ ቢሮዎችን አቅም ማሳደግ፣ | በመቶኛ | 65 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 85 |
| 2 | ለበረራ አደገኛ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶችን የሚከታተልና መግለጫ የሚያዘጋጅ Watch Office/ ስራ ማስጀመር | በመቶኛ | 0 | 10 | 10 | 50 | 15 | 15 | 100 |
| 3 | የሚሰጠው የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት በጥራት ስራ አመራር መመሪያዎች መሰረት ተግባራዊ ማድረግ | በመቶኛ | 18 | 16 | 16 | 16 | 16 | 18 | 100 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | በዓለም አቀፍና መጋቢ አውሮፕላን ማረፊያዎች እሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ሽፋንን ማሳደግ | በቁጥር | 15 | 1 | 1 | 2 | 2 | 1 | 22 |
| | 2.6.5. የጥናትና ምርምር ሥራዎች | | | | | | | | |
| | ግብ 6. የሚቲዎሮሎጂ እና ተዛማጅ ሳይንስ ዘርፎች ላይ ትኩረት ያደረጉና ችግር ፈቺ የሆኑ 36 ጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማሳተም፤ | | | | | | | | |
| 1 | በሚቲዎሮሎጂ እና ተዛማጅ ሳይንስ አገልግሎት ላይ ትኩረት ያደረገ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማካሄድና ማስተባበር | በቁጥር | 0 | 5 | 5 | 5 | 5 | 6 | 36 |
| 2 | ቀደም ሲል የተሰሩ የሚቲዎሮሎጂ እና ተዛማጅ ሳይንስ የጥናትና ምርምር ሰነዶችን መሳተምና ለተጠቃሚዎች ዝግጁ ማድረግ | በቁጥር | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 11 |

### 2.6.6. ሰው ሃብት አስተዳደርና ልማት

**ግብ 7.** የኤጀንሲውን የሰው ሀይል ፍላጎት የማሟላት እና አቅም ግንባታ ሥራዎችን አጠናክሮ በመቀጠል የሰው ኃይል ፍላጎቱ ከ62% ወደ 80% ማሳደግ፡፡

| ተ.ቁ | ሚከናወኑ ተግባራት | መለኪያ | መነሻ | የሚከናወኑበት ዓመት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | (2007) | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | ድምር |
| 1 | 4ኛ-7ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች | በቁጥር | 96 | 13 | 10 | | | | 119 |
| 2 | 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች | በቁጥር | 59 | - | - | - | - | - | 59 |
| 3 | 9ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች | በቁጥር | 8 | | | | | | 8 |
| 4 | 10ኛ-12ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች /የቀድሞው/ | በቁጥር | 159 | 10 | 12 | | | | 181 |
| 5 | መሰናዶ (12ኛ ክፍል) ያጠናቀቀ/ች | በቁጥር | 5 | 2 | | | | | 7 |
| 6 | **በቴክኒክና ሙያ የተመረቀ/ች በሚቲዎሮሎጂ ሣይንስ** | | | | | | | | |
| 6.1 | ደረጃ (level) 3 | በቁጥር | 238 | 49 | 36 | 36 | 36 | 28 | 423 |
| 6.2 | ደረጃ (level) 4 | በቁጥር | 22 | | 25 | 25 | - | - | 72 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6.3 | ደረጃ (level) 5 | በቁጥር | 33 | | 30 | | 33 | | 96 |
| **7** | **በምህንድስና (መስክ) ቴክኒሻን** | | | | | | | | |
| 7.1 | ደረጃ (level) 1 /2 /3 /5 | | | | | | | | |
| 7.2 | ደረጃ (level) 4 | በቁጥር | 0 | 6 | 6 | | | 12 | 12 |
| **8** | **በቴክኒክና ሙያ የተመረቀ/ች ከሚቲዎሮሎጂ ውጪ ባሉ ሙያዎች** | | | | | | | | |
| 8.1 | ደረጃ (level) 1 | በቁጥር | 2 | | | | | | |
| 8.2 | ደረጃ (level) 2 | በቁጥር | 1 | | | | | | |
| 8.3 | ደረጃ (level) 3 | በቁጥር | 14 | 10 | 5 | 5 | 5 | | 39 |

| ተ.ቁ | ሚከናወኑ ተግባራት | መለኪያ | መነሻ | የሚከናወኑበት ዓመት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | (2007) | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | ድምር |
| 8.4 | ደረጃ (level) 4 | በቁጥር | 7 | | | | | | 7 |
| 8.5 | ደረጃ (level) 5 | | | | | | | | |
| 9 | ኮሌጅ ዲፕሎማ | | | | | | | | |
| 9.1 | በተፈጥሮ ሣይንስ/የሙ.ያ መስክ | | | | | | | | |
| 9.2 | በምህንድስና ሳይንስ (Engineering) | በቁጥር | 2 | 1 | | | | | 3 |
| 9.3 | ICT | በቁጥር | 8 | 6 | | | | | 14 |
| 9.4 | ኤሌክትሪካል ኤሎክትሮኒክስ ቴክኔሽያን | በቁጥር | 1 | | 5 | 4 | 2 | | 12 |
| 9.5 | በማህበረሰብ ሣይንስ /የሙ.ያ መስክ | | | | | | | | |
| 9.6 | ሒሣብ አያያዝ (Accounting) | በቁጥር | 15 | 3 | 2 | 3 | | | 23 |
| 9.7 | Management | በቁጥር | 7 | 4 | | | | | 11 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 9.8 | Purchasing and Supply Mgt | በቁጥር | 1 | | | | | | 1 |
| 9.9 | Law | በቁጥር | - | 1 | | | | | 1 |
| 9.10 | Librarian | በቁጥር | 1 | 1 | | | | | 2 |
| 9.11 | አካውንቲንግ | በቁጥር | 7 | 3 | | | | | 10 |
| 10 | **በተፈጥሮ ሣይንስ (BSc)/የሙያ መስክ** | | | | | | | | |
| 10.1 | በሚቲዎሮሎጂ ሣይንስ (Meteorology) | በቁጥር | 135 | 83 | 90 | 30 | 40 | 21 | 264 |
| 10.2 | በምህንድስና ሳይንስ (Engineering) | በቁጥር | 1 | 4 | 1 | 1 | 1 | | 7 |
| 10.3 | ኮምፒዩትር ሣይንስ (Computer Sc.) | በቁጥር | 3 | 2 | 1 | | | | 3 |

| ተ.ቁ | ሚከናወኑ ተግባራት | መለኪያ | መነሻ | የሚከናወኑበት ዓመት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | (2007) | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | ድምር |
| 10.4 | GIS | በቁጥር | | 1 | | 1 | | | 2 |
| 10.5 | ICT | በቁጥር | 1 | 7 | 5 | | | | 12 |
| 10.6 | በማህበረሰብ ሣይንስ (BA)/የሙያ መስክ | | | | | | | | |
| 10.7 | ሒሣብ አያያዝ (Accounting) BA Deg. | በቁጥር | 15 | 3 | 2 | 3 | | | 8 |
| 10.8 | Management | በቁጥር | 28 | 6 | 5 | | | | 11 |
| 10.9 | Economics | በቁጥር | 1 | 2 | 1 | | | | 3 |
| 10.10 | Business education | በቁጥር | 6 | | | | | | |
| 10.11 | Purchasing and Supply Mgt | በቁጥር | 1 | 3 | | | | | 3 |
| 10.12 | Law | በቁጥር | 1 | 1 | | | | | 1 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | **የማስተርስ ዲግሪ** | | | | | | | | |
| 11.1 | በሚቲዎሮሎጂ ሣይንስ (Meteorology) | በቁጥር | 9 | 7 | 11 | 15 | 15 | 15 | 63 |
| 12 | **በማህበረሰብ ሣይንስ (MA)/የሙያ መስክ** | | | | | | | | |
| 12.1 | Human Resource Management | በቁጥር | 1 | | | | | | |
| 13 | ፒኤችዲ (ዶክትሬት ዲግሪ) | | | | | | | | |
| 13.1 | በሚቲዎሮሎጂ ሣይንስ (Meteorology) | በቁጥር | 1 | - | - | - | - | 10 | 10 |

| ተ.ቁ | ሚከናወኑ ተግባራት | መለኪያ | መነሻ | የሚከናወኑበት ዓመት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | (2007) | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | ድምር |
| | 2.6.7. የለውጥ ሠራዊት ገንባታ ዕቅድ | | | | | | | | |
| ግብ 8 በኤጀንሲው የሪፎርምና ልማታዊ መልካም አስተዳደር የማስፈን ስራዎችን በማስቀጠል ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት አሰጣጥን ከ70 % ወደ 75 % ማሳደግ | | | | | | | | | |
| 1 | የለውጥ ሰራዊትን ለማበራከት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ አሁን ካለበት 70% ወደ 95% ማድረስ | በመቶኛ | 70 | 75 | 80 | 85 | 90 | 95 | 95% |
| 2 | የተመቻቸ የስራ አካባቢ አሁን ካበት ከ80% ወደ 96 %ማድረስ | በመቶኛ | 80 | 83 | 86 | 89 | 92 | 96 | 96% |
| 3 | የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መተግበር | በመቶኛ | 10 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 20 |
| 4 | በአመት አንድ ጊዜ ግበረመልስ ማሰባሰብ ውጤታማና ቀልጣፋነቱን | በመቶኛ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | በአመት አንድ |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በተከታታይ መለካትና የታዩ ክፍተቶችን በማስተካከል ዘላቂነቱን ማረጋገጥ፣ | | | | | | | | |
| 5 | ከሰራተኛው ጋር በዳይሬክሬት ደረጃ ግልጽነትን፤ የባለቤትነትና የቡድን ስሜትን በማዳበር ያለበትን ደረጃ ከ65% ወደ 90% ማድረስ | በመቶኛ | 65 | 70 | 75 | 80 | 85 | 90 | 90% |
| 6 | ከደንበኞች እና ባለድርሻ አካላት ጋር በየሶስት ወሩ የህዝብ ክንፍ መድረክ በዋናው መቤትና በቅርንጫፍ ዳይሬክቶሬቶችም አጠናክሮ መቀጠል | በቁጥር | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | በአመት 3 |
| 7 | የተሻለ ተሞክሮና ምርጥ አሰራሮችን በመቀመርና ዕውቅና በመስጠት የፈጻሚ ሰራተኞችን ተነሳሽነት (አሁን ካለበት 70% ወደ 95% በማሳደግ በለውጡ አሠራር ደጋፊዎችን ማበራከት፣ | በመቶኛ | 70 | 75 | 80 | 85 | 90 | 95 | 95% |

| | ሚከናወኑ ተግባራት | መለኪያ | መነሻ (2007) | የሚከናወኑበት ዓመት | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | |
| | 2.6.8. ዘርፈ ብዙ (የወጣቶችና ሴቶች ተጠቃሚነት ማረጋገጥ) | | | | | | | | |
| | ግብ 9 በኤጀንሲው የሥርዓተ ጾታ ተኮር አሰራርን አጠናክሮ በመቀጠል የሴቶችን እኩል ተጠቃሚነትና ተሳትፎ ከ30 በመቶ ወደ 50 በመቶ ማሳደግ፣ እንዲሁም ኤጀንሲው በሚሰጣቸው የአየር ጠባይ ለውጥ እና መላመድ ጋር በሚሰጡ አገልግሎት የሴቶችን ተጠቃሚነት ማሳደግ | | | | | | | | |
| 1 | የስርዓተ ጾታ ማካተት ዙሪያ ለማዕከልና ለየሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላት ሰራተኞች ሰልጠና መስጠት | በቁጥር | 3 | 4 | 2 | 3 | 4 | 4 | 20 |
| 2 | በኤጀንሲው በሚሰሩ ስራዎች የስርዓተ ፆታ ጉዳይ መካተቱን ክትትል በማድረግ ማረጋገጥ | በመቶኛ | 50 | 60 | 70 | 80 | 90 | 100 | 100% |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችንና የኃይል ጥቃቶችን ለመከላከል የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎችን መስራት | በቁጥር | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 7 |
| 4 | ለአየር ጠባይ ለውጥ ተጋላጭ የሆኑ ሴቶች አስመልክቶ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ | ቁጥር | 0 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 | 11 |
| 5 | የአየር ጠባይ ለውጥ እያስከተለ ያለውን ተጽዕኖ ለመቀነስ ላይ ግንዛቤ መፍጠር | በቁጥር | 0 | 0 | 1 | 2 | 3 | 3 | 9 |
| ግብ 10፡ የኤጀንሲዉን በጀት ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ስራ ላይ በማዋል የመደበኛና የካፒታል የፋይናንስ አፈጻጸም ከ80% ወደ 100% ማሳደግ፤ | | | | | | | | | |
| 1 | የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ግዥዎችን በዕቅዱ መሰረት መፈጸም | % | 80% | 80% | 85% | 90% | 92% | 94% | 94% |
| 2 | የኤጀንሲዉን ንብረት በመንግስት መመሪያ መሰረት ማስተዳደር | % | 100% | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100% |
| 3 | ዘመናዊ የንብረት ማደራጀት አሰራር መዘርጋት | % | 20 | 25 | 30 | 40 | 60 | 80 | 80% |

| ግብ 11 የክዋኔ ኦዲት በማድረግ የኤጀንሲዉ በጀት እና ንብረት ወጪ ቆጣቢ፣ ዉጤታማ መሆኑንና ለታለመለት ዓላማ መዋሉን 100% ማረጋገጥ፡ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የባንክና የሳጥን ሂሳብ፣ የገቢና የወጪ ሂሳቦችን፣ የተሽከርካሪና የነዳጅ አጠቃቀም የንብረት ቆጠራ ምርመራ ማድረግ፣ | በቁጥር | 19 | 20 | 20 | 20 | 20 | 20 | |
| 2 | የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦችን፣ የግዥ አፈጻጸምን፣ የሰራተኞች ቅጥር፤ የእድገትና ዝዉዉር አፈጻጸም ኦዲት ማድረግ | በቁጥር | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | |
| 3 | በውጭና በውስጥ ኦዲት የተገኙ ግኝቶች ላይ የተደረጉ ማስተካከያዎች አፈፃፀም | % | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100% |
| 4 | የኤጀንሲውን የክዋኔ ኦዲት በዕቅዱ መሰረት ማከናወን | በቁጥር | 0 | 1 | 4 | 5 | 5 | 5 | |

### 2.6.9. ዕቅድን ለማስፈፀም የሚያስፈልግ የፋይናስ ፍላጎት

ሰንጠረዥ 1፡ የፋይናስ ፍላጎት ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሚሽን ዕቅድ ዘመን (2008-2012) የፋይናንስ ፍላጎትና ምንጭ

| ተ.ቁ | ዝርዝር | መነሻ አመት | ትንቢያ(projection) | | | | | የ5ዓመት ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የ2007ግምት | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | (2008-2012) |
| 1 | ጠቅላላ ወጪ | 120,000,000 | 222,161,000 | 249,216,000 | 278,300,000 | 374,000,000 | 317,900,000 | 1,561,577,000 |
| 1.1 | የካፒታል ወጪ | 78,000,000 | 168,150,000 | 151,800,000 | 151,800,000 | 214,500,000 | 139,700,000 | 903,950,000 |
| 1.2 | የመደበኛ ወጪ | 42,000,000 | 54,011,000 | 97,416,000 | 126,500,000 | 159,500,000 | 178,200,000 | 657,627,000 |
| 2 | ከጠቅላላ ወጪ የውጭ ምንዛሬ ፍላጎት በአሜሪካን ዶላር | 6,500,000 | 4,387,000 | 2,280,000 | 4,873,000 | 3,640,000 | 23,280,000 | 44,960,000 |
| 2.1 | ከብሔራዊ ባንክ | 820,000 | 1,500,000 | 2,273,000 | 550,000 | 273,000 | 2,730,000 | 8,146,000 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.2 | ከውጭ ብድር | | 3,200,000 | | | 3,200,000 | | 6,400,000 |
| 2.3 | ከውጭ ዕርዳታ | 780,000 | 1,800,000 | 2,114,000 | 1,730,000 | 1,400,000 | 910,000 | 8,734,000 |
| 3 | የፋይናንስ ምንጭ | 120,000,000 | 222,161,000 | 249,216,000 | 278,300,000 | 374,000,000 | 317,900,000 | 1,561,577,000 |
| 3.1 | ከመንግስት በጀት | 98,000,000 | 112,661,000 | 198,066,000 | 236,500,000 | 264,000,000 | 295,900,000 | 1,205,127,000 |
| 3.2 | ከውጭ ዕርዳታ እና ብድር | | | | | | | |
| 3.2.1 | ከውጭ ብድር | | 70,000,000 | | | 77,000,000 | | 147,000,000 |
| 3.2.2 | ከውጭ ዕርዳታ | 22,000,000 | 39,500,000 | 51,150,000 | 41,800,000 | 33,000,000 | 22,000,000 | 209,450,000 |
| 3.3 | ከአገር ውስጥ ብድር | | | | | | | |

**ማሳሰቢያ፡** ከላይ በተመለከተው ቅጽ 2በተራ ቁጥር 1 የተቀመጠው ጠቅላላ ወጪ በተራ ቁጥር 3 ከተቀመጠው የፋይናንስ ምንጭ ጋር እኩል መሆን ይጠበቅበታ

## ክፍል ሶስት

## 3. የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ

### 3.1. የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች አውታር ዝርጋታ አፈፃፀም ግምገማ



ምስል 15 ከተለያዩ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች በከፊል

### 3.1.1. የገፀ-ምድር የመረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች ዝርጋታ አፈጻጸም

በሁለተኛው የዕትዕ ዘመን ውስጥ የተለያየ ደረጃ ያላቸውን የገጸ ምድር ጣቢያዎችን ስርጭትና ቁጥር ለማሳደግ ታቅዶ በአብዛኛው ጥሩ የሚባል ውጤት ለማስመዝገብ ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት አብይ ጣቢያዎችን ከ173 ወደ 221 ለማሳደግ ታቅዶ ወደ 195 ለማድረስ ተችሏል፡፡ ይህም የዕቅዱ 88.2 % ነው፡፡ 3ኛ ደረጃ ጣቢዎችን ከ627 ወደ 789 ለማሳደግ ታቅዶ 766 ለማድረስ

ተችሏል፡፡ ይህም የዕቅዱ 97.1% ነው፡፡ በሌላ በኩል 4ኛ ደረጃ ጣቢዎችን ከ403 ወደ 450 ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ኤጀንሲው በያዘው ብዙ የሚቲዎሮሎጂ ፓራሜትር የሚይዙ ጣቢያዎች ላይ ትኩረት የማድረግ ስራ እና የዝናብ መረጃ የሚሰበስቡ ጣቢያዎችን በበጎ ፈቃደኞች የማሰራት አቅጣጫን በመከተሉ ዕቅዱ እንዲታጠፍ የተደረገ ሲሆን 20000 የሚደርሱ የዝናብ መረጃ መሰብሰቢያ ፕላስቲክ መሳሪያዎች ለተጠቃሚዎች ተሰራጭተው መረጃውን እራሳቸው ሰብስበው እንዲጠቀሙ ተደርጓል፡፡ የሳይኖፕቲክ ጣቢያዎች በዕትዕ መጀመሪያ 18 የነበሩትን ወደ 28 ለማድረስ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ጣቢያዎቹን ለመገንባት የሚያስፈልጉ እና በውጭ የምንዛሬ የሚገቡ መሳሪያዎች እጥረት ምክንያት አልተከናወነም።

የማዕከላዊ የካሊብራሽን መሣሪያዎችን በቁጥር (ማሟላት በሚቲዎሮሎጂ ኤለመንት ቁጥር ከነበረበት ሁለት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሽን ዘመን ውስጥ ቁጥራቸው ወደ 9 ለማድረስ ታቅዶ የኤጀንሲው ዋና መ/ቤት ህንጻ በግንባታ ሂደት ላይ በመሆኑ አዲስ የካሊብራሽን መሣሪያዎች ላብራቶሪ በለመዘጋጀቱ የግዥ ሂደቱ አልተከናወነም፡፡

ተንቀሳቃሽ የካሊብሬሽን መሳሪያ በማሟላት ረገድ ከነበረበት ከ5 በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሽን ዘመን ውስጥ ቁጥራቸውን ወደ 14 ለማድረስ ታቅዶ ከላይ በተገለጸው የኤጀንሲው ዋና መ/ቤት ህንጻ በግንባታ ሂደት ላይ በመሆኑ ምክንያት አልተከናወነም፡፡

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሽን ዘመን ውስጥ የተፈተሹና ካልብሬት የተደረጉ ኮንቬንሽናል ጣቢያዎች ቁጥር ከ4ኛ ደረጃ ጣቢያ በላይ ከነበረበት 818 ወደ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሽን ዘመን ውስጥ ቁጥራቸውን 1038 ለማድረስ ታቅዶ 2530 ለማድረስ ተችሎዋል፡፡

በተመረቱ የተለያዩ የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች እና አጋዥ ቁሳቁሶች (accessories) ከ5000 ወደ 10000 ለማድረስ ታቅዶ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሽን ዘመን ውስጥ ቁጥራቸውን 11342 ለማድረስ ተችሎዋል፡፡

በክልሎች ቢሮዎች መገንባትን አስመልክቶ ከነበረበት 153 ወደ 191 ለማድረስ ታቅዶ 167 ለማድረስ ተችሎዋል፡፡

በቁጥር ሀያ ዘጠኝ አንደኛ ደረጃ ጣቢያዎች በአዲስ ዲዛይን አጥር መገንባት ታቅዶ አስራሁለት መገንበት ተችሎዋል፡፡

### 3.1.2. ዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ የመረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች ዝርጋታ አፈጻጸም

- የከፍታ አየር መመዝገቢያ ጣቢያ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ 2 የነበረውን ወደ 3 ለማሳደግ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት 3 ማድረስ በመቻሉ እቅዱ 100% ተከናውኗል::
- የአየር ብክለት መከታተያና መመዝገቢያ በሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ በሀገሪቱ አንድ የነበረውን ወደ 4 ለማድረስ ታቅዶ 3 ማድረስ ተችሏል፡፡ ይህም የዕቅዱ 75% ነው፡፡
- የሳተላይት መረጃ መቀበያ ጣቢያ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንሰፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጀመሪያ ሁለት ብቻ የነበረውን ወደ 13 ለማድረስ ታቅዶ 13 ለማድረስ ተችሏል። አፈፃፀሙም (100%) ነው።
- ሰው አልባ አውቶማቲክ የአየር ሁኔታ መመዝገቢያ ጣቢያ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ 107 የነበረውን በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ መጨረሻ 700 ለማድርስ ታቅዶ 312 ተቋቁሟል ይህም የዕቅዱ (44.6 % ) ነው።
- በዓለም አቀፍ የአውሮፕላን ጣቢያዎች የሚገኙትን Automatic Weather Observing System (AWOS) በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ ለነበሩት አምስት AWOS አቅም ማሰደጊያ ተጨማሪ የሶፌትዌር ግዥ ለማከናወን ታቅዶ በእቅዱ መሰረት ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል (100% )።
- Small Automatic Weather Observing System (S-AWOS) በመጋቢ አውሮፕላን ማረፊያ በሁለተኛው ዕትዕ መጀመሪያ 4 ሲሆን፣ በዕትዕ ዘመን 16 ለማቋቋም ታቅዶ 12 በመቋቋም የዕቅዱ 75% ተቋቁሟል።
- የSatellite Distribution System (SADIS) ተከላን አስመልክቶ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ ከነበረበት አንድ SADIS) በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ ወደ አራት

ለማሳደግ ታቅዶ በእቅዱ መሰረት አራት በማድረስ የዕቅዱ 100% ተከናውኗል ፡፡

- የAircraft Meteorological Data Relay (AMDAR) ሲስተም ዝርጋታ (በቁጥር) በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ በቁጥር አንድ ለመትካል ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት አልተከናወነም ፡፡
- የመብረቅ መከታተያ ጣቢያዎች (Lightning Detection Network) ማቋቋምን አስመልክቶ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ በቁጥር 32 ለመትካል ታቅዶ ከልማት አጋሮች ሀብት የመፈለለግ ስራን በመከናወን ከኢትዮ ፊንላንድ ጋር ስምምነት ለመፈራረም በሂደት ላይ ይገኛል፡፡



Figure 16 የአዳማና ሀዋሳ የአየር ብክለት መከታተያ ጣቢያ ምረቃ

- የአየር ሁኔታ መከታታያ ራደርን ለመትካል በሁ ለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ ላይ በቁጥር አንድ የነበረውን ወደ ሁለት (2) ለማድረስ ታቅዶ ተጨማሪ ሶስት (3) የአየር ሁኔታ መከታተያ ራዳር ተከላና ግዥ ለማከናወን ከልማት አጋሮች ሀብት የመፈለለግ ስራን በመከናወን ከኢትዮ ፊንላንድ ጋር ስምምነት ለመፈራረም በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

- የኤጀንሲውን የትንበያ አቅም ለማሻሻል የሚያስችል እና በጥናትና ምርምር ዘርፍ የክላይሜት ሞዴልንግ ስራን ለመካናወን የሚረዳ ከፍተኛ አቅም ያለውን ክላሰተር ኮምፒተር (High performance computer —HPC) ግዥ ለማከናወን በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ያልነበረውን አንድ ለመግዛት ታቅዶ የሁለት (High performance computer —HPC) ግዥ እና ተከላ ተከናውኖዋል፡፡

### 3.1.3. ዘመናዊ የመረጃ አቅርቦትና ስርጭት አፈፃፀም

- የተሻለ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ጥራት ያለው የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ለመሰብሰብ በኮምፒዩተር መረብ ቢሮዎችን በማስተሳሰር የWAN እና የLAN የመገናኛ ዘዴዎችን መጠቀም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጀመሪያ በዋናው መሥሪያ ቤት ብቻ ተወስኖ የነበረውን የመረጃ መረብ የኤጀንሲው የሥልጠና፣ ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ የአቪየሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የዳይሬክቶሬት እና 11ዱንም የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላት፣ ከዋናው መሥሪያ ቤት እና እርስ በርሳቸው በማስተሳሰር የመረጃ ፍሰቱ ቀልጣፋና የተሳለጠ ለማድረግ ተችሏል፡፡
- የኤጀንሲውን ዋና መ/ቤት፣ የአቪየሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የዳይሬክቶሬት እና አስራ አንዱንም የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላትን በቪድዮ ኮንፈራንስ የመገናኘት ስራ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ተግባራዊ ሆኖዋል፡፡
- በኤጀንሲው የአይሲቲ ፖሊሲ ትግበራን አስመልክቶ internet, File services, የMail server and webhosting የመሰሰሉትን ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ተግባራዊ ሆኖዋል፡፡ አፈጻጸሙ 100% ነው፡፡
- የኤጀንሲውን የፋይናንስ ስርአትን ከማዘመን አኳያ የተቀናጀ የፋይናንስ ስርዓት (Integrated Financial Information Management System IFIMS) በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን 100% ተግባራዊ ሆኖዋል፡

- በመጀመሪያው በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ውስጥ 10 ኪሜ በ 10ኪሜ ግሪድ የተደራጀ መረጃን ጨምሮ ወቅታዊነቱን ጠብቆ የሚታደስ የሚሰረጭበት የኤጀንሲው ድረገጽ በሁለተኛው የዕትዕ ዘመን በ4ኪ.ሜ በ4ኪ.ሜ ግሪድ የተሟላ መረጃ የሚያቀርብ ሆኗል።
- ከሳይኖፕትክ ጠቢያዎች የሚሰበሰቡ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን በዓለም አቀፍ ስምምነት መሰረት ለዓለም አቀፍ ማዕከላት በዓለም አቀፍ የቴሌ ኮሙኒኬሽን ስርአት (Global Telecommunication System —GTS) በሙሉ አቅሙ ተግባራዊ ተደርጎዋል፡፡
- የሀገሪቱን የቆዳ ሽፋን ወካይ የሆነ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ አሁን ካሉት 1367 የተለያየ ደረጃ ካላቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ወደ 2600 በማድረስና መረጃ በመሰብሰብ፣ በማጠናቀርና በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ተደራሽ የማድረግ ግብ ተጥሎ፡፡
- ጥሬና የተተነተነ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን ጥያቄ ማስተናገድ በተጠቃሚ ቁጥር ከነበረበት 850 ተጠቃሚ ቁጥር ወደ5260ለማድረስ ታቅዶ 5596 በማድረስ የዕቅዱን 106 በመቶ ለማከናወን ተችሎዋል፡፡
- ለሁሉም ወረዳዎች የወረደ ክላይሜት አትላስ በማዘጋጀት ማሰራጨት ታቅዶ በኤጀንሲው ማፕሩም የሁሉንም ወረዳ የዝናብ እና ሙቀት ስርጭት ትንተና በማፕ ተጠቃሚዎች ማግኘት እንድችሉ ተደችጎዋል፡፡
- ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ማደራጀት (በመደበኛ እና ሰው አልባ ጣቢያ) ከነበረበት 1327 ወደ 2590 ለማድረስ ታቅዶ 1721 በማድረስ የእቅዱ 66 በመቶ ተከናውኖዋል፡፡
- በወጥና ዘመናዊ የመረጃ ቋት ሥርዓት (Climate Database Management System-CLIDATA) መረጃዎችን ማደራጀት (በመደበኛ እና ሰው አልባ ጣቢያ) ከነበረበት 1327 ወደ 2590 ለማድረስ ታቅዶ 1721 በማድረስ የእቅዱ 66 በመቶ ተከናውኖዋል፡፡
- በሶፍት እና ሃርድ ኮፒ መረጃዎች ላይ ጥራት ቁጥጥር በማካሄድ በኢለመንት ማጠናቀር (በመደበኛ እና ሰው አልባ ጣቢያ) ከነበረበት 1327 ወደ 2590 ለማድረስ ታቅዶ 1721 በማድረስ የእቅዱ 66 በመቶ ተከናውኖዋል፡፡

- የተለያዩ ኤለመንቶች የአየር ጠባይ መረጃ (Climate series) በማዘጋጀት ማሳተም (በህትመት) ይታተምበት ከነበረው አንድ አሌሜንት ወደ ስድስት ለማድረስ ታቅዶ አራት ለማድረስ ተችሎዋል፡፡
- ከሳተላይት መረጃ የዝናብ ግምት /RFE/ መተንተን በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ በየአመቱ 36 ለማከናወን ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ 180 ለማድረስ ተችሎዋል፡፡ይህም የዕቅዱ (100%) ነው።
- የተለያዩ የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎችና አጋዥ ቁሳቁሶችን ማምረት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ 896 የነበረውን በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ 4,896 ለማድረስ ታቅዶ ክንውኑ 4, 896 (100%)ነው፡፡

## 3.2. የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የምክር አገልግሎት አፈጻጸም



**ምስል 17 የትንበያና የምክር አገልግሎት**

### 3.2.1. የሚቲዎሮሎጂ የትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስራዎች

ብሄራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በአዋጅ ከተቋቋመበት አንዱ ለማህበረሰቡ ወቅታዊ እና ጥራቱን የጠበቀ የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያን በጊዜ ፣በመጠን፣ በቦታና በጥራት በማዘጋጀት፣ ከአየር ሁኔታና ጠባይ ጋር ዝምድና ባላቸው የተፈጥሮ አደጋዎች ዙሪያ በደንበኞች ፍላጎት ላይ የተመሠረተ፤ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያዎችን የማካሄድ ስራዎች በዚህ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎረሜሽን ዕቅድ ውስጥ በተጠነከረ መልኩ ስሰጡ ቆይቶዋል፡፡

በመሆኑም አለም አቀፋዊና አህጉራዊ የትንበያ ሞዴሎችንና ውጤቶችን ወደ አካባቢያዊ ቦታዎች ክልል፣ ዞንና ወረዳ በመቀየር (Down Scaling) የትንበያን አቅም ማሳደግ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ ከነበረበት 75 በመቶ ወደ ሰማኒያ በመቶ ለማድረስ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት 77 በመቶ ለማድረስ ተችሎዋል፡፡ የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አገልግሎት ተደራሽነትን ከማሳደግ አንፃር በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ ከነበረበት 75 በመቶ ወደ ሰማኒያ አምሰት በመቶ ለማድረስ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት 77 በመቶ ለማድረስ ተችሎዋል፡፡

የአየር ሁኔታና የአየር ጠባይ መረጃዎችን በብዙሀን መገናኛ ለህብረተሰቡ ለማሰራጨት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ ከነበረበት 60 በመቶ ወደ 100 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 80 በመቶ ለማድረስ ተችሎዋል፤ የአየር ጠባይ መጽሔት በማዘጋጀት በዕቅድ ዘመኑ ውስጥ በቁጥር96 ለማዘጋጀት ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተከናውኖዋል፡፡

ለአንድ ወቅት የሚሰጠውን የወቅት ትንበያ ሁለት ወቅቶች አስቀድሞ በመተንበይ የቅድመ ጥቆማን አቅም በማጠናከር ሊከሰቱ የሚችሉ የአየር ጠባይ ተለዋወጭነትን 75% ለመተንበይ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት 75 በመቶ ተከናውኖዋል፡፡

የክልል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የአካባቢያቸውን የወቅት ትንበያ በዞንና በወረዳ ደረጃ ለመስጠት እንዲችሉ ማብቃትና የሚሰጡ ትንበያዎች ትክክለኛነት ከነበረበት 70 በመቶ ወደ 80% ለማድረስ ተችሎዋል፡፡

የአጭር ጊዜ የአየር ሁኔታ ትንበያዎችን አስተማማኝነት ከነበረበት 75 በመቶ ወደ 85% ለማድረስ ታቅዶ 77 በመቶ ለማድረስ ተችሎዋል፡፡ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ አየር ጠባይ ትንበያ አስተማማኝነትን ከነበረበት 70 በመቶ ወደ 85% ለማድረስ ታቅዶ 77 በመቶ ለማድረስ ተችሎዋል፡፡



ምስል 18 ከሚቲዎሮሎጂ አገልግሎቶች ጋር የተደረጉ የምክክር መድረኮች

### 3.2.2. የልማት ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የ2ኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም

የልማት ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ለተለያዩ ሴክተሮች ማለትም ለግብርና ፣ለውሃ ፣ ለጤና እንዲሁም ለሰብሎች እንሹራንስ የሚቲዎሮሎጂ የምክር አገልግሎት የሚሰጥ ዘርፍ ነው፡፡ በመሆኑም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ፣የሀይድሮ ሚቲዎሮሎጂ እና የጤና ሚቲዎሮሎጂ የምክር አገልግሎት የዘርፉ ተጠቃሚዎችን ፍላጎት ባገናዘበ መልኩ ወቅቱን የጠበቀ ጥራት ያለው እና ተደራሽ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ስራች ስሰሩ ቆይቶዋል፡፡ በመሆኑም አገልግሎቱን የበለጠ ወደ ተጠቃሚው ለማድረስ እና

ተጠቃሚዎች በቀላሉ አገልግሎቱን እንድያገኙ እና እንድረዱ የሚያስችላቸውን የተለያዩ የአሰራር ማኑዋሎችን በማሰተም ማሰራጨት ተችሎዋል፡፡

ከግብርና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት አኳያ የሃገራችን ግብርና በዝናብ ውኃ ላይ መሠረት ያደረገ ስለሆነ፤ የአየር ሁኔታና ጠባይ በመከታተል ለዘርፉ የሚሰጥ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ የምክር አገልግሎት ,ለግብርና ምርትና ምርታማነት ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ በግብርናው መስክ የግብርና ምርትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የግብርና ግብዓቶችን አጠቃቀም፣ ዕለታዊ፣ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊና ወቅታዊ የሰብሎች ዝናብ መጠን ፍላጎት ስርጭትን፣ የዘር ጊዜ፣ የደረቅ ሰሞኖችና ያልተጠበቀ ዝናብ እንዲሁም የሰብል የዕድገት ደረጃ ትንበያ፣ ግምገማና የሰብሎች የውሃ ፍላጎት እርካታ ጠቋሚ መረጃዎች፤ የተቀላጠፈ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ትንበያና ምክር አገልግሎቶች በተጨማሪም የአርብቶ አደርና የከፊል አርብቶ አደር አካባቢን የውሃና ግጦሽ አቅርቦት ሽፋን የሚያግዝ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃና የምክር አገልግሎት በመስጠት የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነትን ለማሰደግ የሚያስችል አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቶዋል፡፡

በመሆኑም ለአርሶ አደሩና ለአርብቶ አደሩ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ተደራሽነት ማሳደግ፣ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ በየአመቱ በመቶኛ 60% የነበረውን የግብርና ሚቲዎሮሎጂ የምክር አገልግሎት መጽሔት ስርጭት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ 80 % ለማድረስ ታቅዶ 80% ደርሷል፡፡ ይህም የዕቅዱ (100%) ነው።

ከሀይድሮ ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት አኳያ የሃይድሮሚቲዎሮሎጂ ኢንዴክስ ጣቢያዎችንና የዘመናዊ አውቶማቲክ የሃይድሮሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ሽፋን በማስፋፋት የአገሪቱን ተፋሰሶች መሠረት ያደረገ የሀይድሮሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን በመተንተን ከከባድ ዝናብ ክስተቶች ጋር በተያያዘ የጎርፍና ቅፅበታዊ ጎርፍ ክስተቶችን በመከታተል በተፋሰሶችና በንዑስ ተፋሰሶች ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖዎችን በመከታተልና በመተንበይ የውሃውንና ኢነርጂን ዘርፍ ለማገዝ የሚያስችል አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቶዋል፡፡ በሀገሪቱ ያለውን የውኃ በጀትን (water balance) ለማቀድ የሚያስችሉ የሃይድሮሚቲዎሮሎጂ

ትንተና በማጠናከር፣ ከውኃው ዘርፍ ጋር ለተያያዙ የመሠረተ ልማት ሥራዎች የምክር አገልግሎቶችን በስፋት እየሰጠ ይገኛል።

በመሆኑም የሀይድሮ ሚቲዎሮሎጂ ትንበያንና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የምክር አገልግሎት ተደራሽነትን በማሳደግ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ በመቶኛ 50% የነበረውን የሀይድሮ ሚቲዎሮሎጂ የምክር አገልግሎት እና የመጽሔት ስርጭት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ በየአመቱ 75 % ለማድረስ ታቅዶ 75 % ደርሷል። ይህም የዕቅዱ (100%) ነው ።





**ምስል 19 ከምስል ጋር ተመሳሳይ**

ከዘርፍ ተኮር ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት አካያ በአየር ሁኔታና ጠባይ ምክንያት የሚፈጠሩ በሽታዎችን ለመከላከል ለጤናው ዘርፍ አመቺ ያልሆኑ የአየር ሁኔታና ጠባይ መረጃዎችን በመከታተል ለጤና ሴክተሩ አገልግሎት መሻሻል

የጤና ምክር አገልግሎት በመስጠት ከዘርፉ ተጠቃሚዎች ጋር በቅንጅት ስስራ ቆይቶዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የአየር ሁኔታና ጠባይ መሠረት ያደረገ የሰብልና የእንስሳት ሀብት ልማትን ያማከለ የመድህን ሽፋን በማስፋፋት ከአየር ሁኔታ መዛባት ጋር ተያይዞ የሚደርሱ ጉዳቶችን አርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን ለማገዝ ትኩረት ተደርጎ እየሰራ ይገኛል።

በመሆኑም በጤናው ዘርፍ የአገልግሎት የአፕላይድ ሚቲዎሮሎጂ ትንበያንና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተደራሽነትን በማሳደግ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ በቁጥር በአመት 60% የነበረውን የጤና ሚቲዎሮሎጂ የምክር አገልግሎት እና የመፅሄት ስርጭት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ በአመት 80% ለማድረስ ታቅዶ 80 % የዕቅዱ (100%) ደርሷል።

### 3.2.3. የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የ2ኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም

የአየር ትራንስፖርት ለአየር ሁኔታ ክስተቶች የተጋለጠ ነው፡፡ በአየር ትራንስፖርት ከሚከሰቱ አደጋዎችና የአደጋ አጋጣሚዎች ዋንኛውና ግልጽ ምክንያት የሚሆኑት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀና ጥራቱ የተረጋገጠ የኢሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ደህንነቱ ለተጠበቀ መደበኛና ኢኮኖሚያዊ የአየር በረራ ስራ/Air Navigation Operation/ ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም ጊዜውን ለጠበቀ፣ መደበኛና ደህንነቱ ለተሟላ የአውሮፕላን በረራ አገልግሎት መሣካት ከሚያስፈልጉ ግብዐቶች አንዱ የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ነው። ደህንነቱና አስተማማኝነቱ የተረጋገጠ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት በሀገሪቱ ተግባራዊ እንዲሆን የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን በዘርፉ ለተሰማሩ ተጠቃሚዎች መስጠት የኤጀንሲያችን ተግባርና ኃላፊነት ነው።

በዚሁ መሰረት የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት በአለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ስምምነት (ተቀጽላ ሶስት) ሰነድ መሰረት ጥራቱንና ጊዜውን የጠበቀ ኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰብሰብና ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣

እንዲሁም ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ፣ መግለጫና የምክር አገልግሎት በመስጠት፣ የአቪየሽን የበረራ ደህንነትን አስተማማኝ የማድረግ ስራ በሁለተኛው ዕትዕ ውስጥ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ሲተገበር ቆይቷል። ለአየር ትራንስፖርት ደህንነትና ስኬታማነት አለም አቀፍ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮጂ አገልግሎት አሰጠጥን ከ65% ወደ 85% የማድረስ ግብ ተቀምጦ በሁለተኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ማጠናቀቂያ ላይ የተቀመጠው የአጠቃላይ 85 በመቶ ግብ ተከናውኖዋል፡፡ በመሆኑም የአራት አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያዎች የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ ቢሮዎችን አቅም ማሳደግ፣/ Strengthen Aerodrome Meteorological Offices / በሁለተኛው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን መጀመሪያ ላይ ከነበረበት 60 በመቶ ወደ 85 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች በመትከል ለሰው ሀይል የብቃት ማረጋገጫ እንድያገኙ በማደረግ በተቀደው መሰረት 85 በመቶ ለማድረስ ተችሎዋል፡፡ በኢትዮጵያ በረራ ክልል ለበረራ አደገኛ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶችን የሚከታተልና መግለጫ የሚያዘጋጅ የሚቲዎሮሎጂ ክትትል ቢሮን /Meteorology Watch Office / ማደራጀትና ስራ የማስጀመር ስራ በሁለተኛው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን መጀመሪያ ያልነበረውን 100% አገልግሎት መስጠት ተችሎዋል፡፡ በአለም አቀፍ እና መጋቢ አውሮፕላን ማረፊያዎች የሚሰጠው የኤሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የአለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅትና አለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ባወጣቸው የጥራት ስራ አመራር መመሪያዎች መሰረት ተግባራዊ ማድረግ በሁለተኛው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን መጀመሪያ ላይ ከነበረበት 18 በመቶ ወደ 100 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ የጥራት ስራ አመራር ስርአት QMS ISO-9001/2015 ክለሳ በማድረግ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመረከብ 98% ተከናውኖዋል፡፡ በአለም አቀፍ ና መጋቢ አውሮፕላን ማረፊያዎች እሮኖቲካል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ሽፋንን ለማሳደግ በሁለተኛው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን መጀመሪያ ላይ ከነበረበት 15 አውሮፕላን ማረፊያዎች ወደ 22 አድጓል ፡፡ አፈፃፀም 100% ለማድረስ ተችሎዋል፡፡

## 3.3. የሚቲዎሮሎጂ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት 2ኛው ዕትዕ አፈጻጸም

የአየር ሁኔታና ጠባይ በተለያዩ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ላይ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖና ለዘርፎቹ እድገት የሚያበረክቱትን ድርሻ በሚገባ ለማወቅና ለመጠቀም የሚቲዎሮሎጂ ጥናትና ምርምር ማካሄድ ወሳኝ ተግባር መሆኑን በመረደት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ውስጥ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ታቅዶዋል፡፡ የሚቲዎሮለጂ የሳይንስ ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ብዙ ጥናቶች የሚያስፈልጉት ሲሆን፣ በተለይ ሀገራችን በምትገኝበት የሀሩር ክልል በቂ ጥናት ያልተካሄደ በመሆኑ የሚቲዎሮለጂ ጥናትና ምርምር በስፋት ማካሄድ ያስፈልጋል። የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ተጠቃሚዎችን መሰረት ያደረገ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ለመስጠት እንዲቻለው የሚቲዎሮሎጂ ጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል። በመሆኑም በሚቲዎሮሎጂና ተዛማጅ የሳይንስ ዘርፎች ላይ የሚከሄዱ_የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በ2ኛ ዕትዕ መጨረሻ ስድሳ (60) ለማድረስ ታቅዶ ስልሳ ስድስት (66) ለማድረስ ተችሏል፡፡ ይህም የዕቅዱ 110% ነው፡፡ አፈጻፀሙ የጨመረው የሚቲዎሮሎጂ ባለሙያዎች ለሙያ መሰላሉ ዕድገት የሰሩት ማኑዋሎችን በማስተባበራችን ነው፡፡ በተጨማሪም ቀደም ሲል በሚቲዎሮሎጂና ተዛማጅ የሳይንስ ዘርፎች ላይ የተሰሩ__የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በማሳተም ለተጠቃሚዎችና ባለድርሻ አካላት ለማድረስ በ2ኛ ዕትዕ መጨረሻ አስራ አንድ (11) ለማድረስ ታቅዶ አስራ ሶስት ለማድረስ ተችሏል፡፡ ይህም የዕቅዱ 118% ነው፡፡

## 3.4. የሰው ሀብት ልማትና የአቅም ግንባታ አፈጻጸም ግምገማ

የኤጀንሲውን የሰው ሀይል ፍላጎት በመጀመሪያው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ (2007ዓ.ም) ከነበረበት 887 የሰው ሀይል በሁለተኛ እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ (2012ዓ.ም) ወደ 1487 ለማድረስ ታቅዶ፤ 954 መድረስ ተችሏል፡፡





Figure 20 የኤጀንሲው የሰው ሀይል

ባለፉት በሁለተኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን በጡረታና በተለያዩ ምክንያቶች የለቀቁ ሰራተኞች ቁጥር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡





Figure 21 በተለያየ ምክንያት ከኤጀንሲው የለቀቁ

ከሰው ኃይል አቅም ግንባታ አኳያ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽኑ ዘመን በጀማሪ ፣በመካከለኛና በከፍተኛ ሚቲዎሮሎጂ ቴክኒሽያን የሀገር አቀፍ

የሙያ ደረጃ/Occupetional Standard / የምዘና ስርዐት /Assesment Tools/ እና የምዘና ማዕከል / Assesment Center / በማጥናት እውቅና እንዲያገኝ በተደረገው መሰረት በጀማሪ ፣በመካከለኛና በከፍተኛ ሚቲዎሮሎጂ ቴክኒሽያን የሀገር አቀፍ የሙያ ደረጃ/Occupetional Standard ያገኙ ሰራተኞች ቁጥር 289 መደረስ ተችሎዋል፡፡

የሰው ሀብት ልማቱን ለማበራከትና ለማስፋት በራስ አቅም፣ በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ባሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር ትስስር በመፍጠርና በተገቢው ሁኔታ ክፍተቶችን መሙላት ፣ ከአዳዲስ ቴክኖሎጂና የጥናትና የምርምር ግኝቶች በመስኩ ከሌሎች ዘርፎች ጋር አብሮ ለመጓዝ በተለያየ እርከን የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በአቅዱ መሰረት ተከናውኖዋል፡፡ በመሆኑም **ከአጭር ጊዜ ስልጠናዎች አፈጻጸም አኳያ** ለሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማሻሻያ የሚያግዙ ስልጠናዎች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር /በኢጋድ የአየር ጠባይ ትንበያና ትግበራ ማዕከል፣ በአውሮፓ የመካከለኛ ጊዜ አየር ሁኔታ ትንበያ ማዕከል የአፍሪካ ሚቲዎሮሎጂ ትግበራና ልማት ማዕከልና በተለያዩ የአለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት የሚቲዎሮሎጂ የስልጠና ማዕከላት ወዘተ ተስጥዋል፡፡

**ከረጅም ጊዜ ስልጠናዎች አፈጻጸም አኳያ** በአለም የሚቲዎሮሎጂ ድርጅት እና በሀገር ውስጥ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በተደረገ ግንኙነት እና ስምምነት መሰረት በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መጨረሻ ላይ 9 ብቻ የነበረውን በሁለተኛ ድግሪ የተመረቁ ባለሙያዎች ቁጥር በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽ እቅድ ዘመን ውስጥ ወደ 46 ለማድረስ ተችሏል፡፡ በሚቲዎሮሎጂ ዲፕሎማ ድህረምረቃ (PGD) ፕሮግራም በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን በሁለት ዙር በማሰልጠን በቁጥር 85 ባለሙያዎችን ማስመረቅ ተችሏል፡፡

አስር በሶስተኛ ድግሪ የሚቲዎሮሎጂ ሳይንስ (PHD) ፕሮግራም በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን ለማሰልጠን ታቅዶ አንድ ሰው በመሰልጠን ላይ ይገኛል፡፡ ይህም የእቅዱ 10 በመቶ ነው፡፡

### 3.5. የባለ ብዙ ዘርፍ ስራዎች አፈጻጸም

#### 3.5.1. የሴቶች ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ

የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አኳያ ሴቶች በእድገት በቅጥርና በትምህርት ልዩ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንጻር ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችንና የኃይል ጥቃቶችን ለመከላከል የግንዛቤ የማስጨበጥ ሰፊ ሥራዎች በኢጀንሲው ተሰርቷል። በዚህም መሰረት በኤጀንሲው በሁሉም መስክ ተሳታፊና ተጠቃሚነት በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መጨረሻ ከነበረው 35 በመቶ ወደ 50 በመቶ ለማሳደግ ታቅዶ የሴቶች በውሳኔ ሰጭነትና አመራር ተሳትፎ ወደ 35% ለማድረስ ተችሏል፡፡

#### 3.5.2. የአረንጓዴ ልማት ትግበራ አፈጻጸም (የአካባቢ ጥበቃ)

ለአየር ጠባይ ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ከአየር ጠባይ ጋር መላመድ ሆነ ለአየር ጠባይ ለውጥ ስርአት እንቅስቃሴዎች የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ቁልፍ እና የማይተካ ሚና ያለው በመሆኑ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ውስጥ በርካታ ሥራዎች ተከናውኖዋል፡፡

- የአየር ጠባይ ለውጥ መገለጫዎችን በመረጃ በማስደገፍ ህብረተሰቡ ትክክለኛና ሳይንሳዊ መረጃ እንዲያገኝ የማድረግ ስራዎች በዕቅዱ መሰረት ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ተከናውኖዋል፡፡
- በኤጀንሲው ለረጅም ጊዜ የተከማቹ የአየር ጠባይ መረጃን በመተንተን እና በማጥናት የአየር ጠባይ ለውጥ መገለጫ ዝርዝር መረጃ በማደራጀት እና ማሰራጨት፤ ከፍተኛ የአየር ጠባይ ለውጥ እየታየባቸው ያሉ ቦታዎች እና የለውጡን ደረጃና ዝርዝር ባህሪይ በመለየት ከአየር ጠባይ ለውጥ ጋር የመላመድ ሥራውን ለማገዝ በጥናትና ምርምር የተደገፉ የምርምር ውጤቶች ተከሂዶዋል፡፡




**ምስል 22 የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር**

> የኤጀንሲው ሠራተኞችና በምስራቅ አፍሪካ የልማት በየነመግስታት የአየር ጠባይ ትንበያና ትግበራ ማዕከልና አባል ሀገራትን በመወከል ተሳታፊዎች ችግኝ ሲተክሉ

- የአየር ጠባይ ለውጡ ወደ ፊት በተለያዩ የሀገራችን ቦታዎች ምን መልክ እንደሚኖረው በማጥናት እና መረጃ በማዘጋጀት ማሰራጨት፣ ከአየር ጠባይ ጋር በመላመድ ለመኖር በሚደረግ ጥረት እና የልማት አቅጣጫ ላይ መረጃ መሠረት በማድረግ የምክር አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ዘርፍ ተኮር የሆኑ የጥናትና የምርምር ስራዎች እና የምክር አገልግሎት ተግባራት ተከናውኖዋል፡፡
- ከተባበሩት በየነ መንግስታት የአየር ጠባይ ለውጥ የሚወጡ ሪፖርቶችን መሰረት በማድረግ በአየር ጠባይ ለውጥ ምክንያት የሚከሰቱ የአየር ጠባይ ተለዋዋጭነት እና አደገኛ የአየር ሁኔታዎችን በጥልቀት በመከታተል የማላመድ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስራዎችን ለማከናወን የ IPCC ሪፖርቶች በግብአትነት ተወስደዋል፡፡

❖ ለታዳሽ ኃይል መሠረት የሆኑ የንፋስ፣ የፀሐይ ብርሃን፣ እንዲሁም የዝናብ ታሪካዊ መረጃዎችን እና ትንበያዎችን በጥራት ማደራጀት ስራዎች በዕቅዱ መሰረት ተከናውኖዋል፡፡

### 3.5.3. የኤጀንሲው አገለግሎትን የማስተዋወቅ፣ የገፅታ ግንባታ እናኮሙኒኬሽን ስራዎች

በዓመታዊ ዕቅዶችና አፈፃፀሞች፣ በአገልግሎት አሰጣጥና አጠቃላይ የኤጀንሲውን እንቅስቃሴ በሚያሳዩ ወቅታዊ አጀንዳዎች ዙሪያ ሁነቶችን፣ የምክክር መድረኮችን ከአገልግሎታችን ተጠቃሚዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር በማዘጋጀት የኤጀንሲውን አገልግሎት የማስተዋወቅ ስራ ተከናውኖዋል፡፡



Figure 23 በተለያየ ጊዜ የተሰጡ መግለጫዎች

በሚቲዎሮሎጂ ሳይንስና በኤጀንሲው ወቅታዊ እንቅስቃሴ ላይ ትኩረት ያደረጉ የህትመት ውጤቶችን በማዘጋጀትና በማሰራጨት፣ከሚዲያ ተቋማት ጋርም ጠንካራ ትስስር በመፍጠር የተለያዩ የኮሙኒኬሽን ሥራዎች በመሠራታቸው ወቅታዊ መረጃዎችን በፍጥነት ወደ ህብረተሰቡ ከማድረስም ባሻገር ህብረተሰቡ በሚሰጡ አገልግሎቶችና በመረጃው አስፈላጊነት ዙሪያ ያለው ግንዛቤን በማሻሻል

የግንዛቤ ደረጃውም በሁለተኛው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅደ መጀመሪያ ላይ ከነበረበት 70% ወደ 79 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

### 3.5.4. የለውጥ እና የሪፎረም ስራዎች አፈጻጸም

በኤጀንሲው የለውጥ ፕሮግራሞች እንዲተገበሩ ለማድረግ ለውጡን በመምራት እና በመገምገም የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን በተደጋጋሚ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን በመሥራት አዳዲስ ከሚመጡ ሁኔታዎች ጋር አጣጥሞ ለመተግበር የሚያስችል ትንተና እና ጥናቶችን በማካሄድ ለውጡን ተቋማዊ የማድረግ ስራዎች ተከናውኖዋል፡፡

የኤጀንሲውን ውስጣዊና ውጫዊ አደረጃጀት ያለበትን ችግሮች በመቅረፍና ለለውጡ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ተጠቃሚዎችንና ሰራተኞችን ባሳተፈ መልኩ የግብረ መልስ ልውውጥ ስርዓት በማጠናከር በየስራ ዘርፎች በቅንጅት የመስራት አቅጣጫዎች ተይዘው በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል።

የኤጀንሲው የበላይ አመራር በመንግሥት ደረጃ የተቀመጠውን ግልጽ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ለመፈፀም የሪፎርም ሥራዎችን በየደረጃው ያለው አመራር በአግባቡ ይዞ እንዲተገብር ለማድረግ በሁሉም ደረጃ የሚስተዋለውን የአመለካከት፣የክህሎትና የአቅርቦት ማነቆዎችን ለመፈታት በርካታ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ በሀገር ደረጃ የመጠውን ሀገራዊ ሪፎርምን በመስቀጠል ረገድ ከመለው ሰራተኞች እና በየደረጃው ከሚገኘው አመራር ጋር ውይይቶችን በማከሄድ ለውጡ ስር እንድሰድ እና ተቋማዊ እንድሆን አስፈለጊው መግባባት ላይ ተደርሶዋል፡፡

ምቹ የስራ አከባቢን ከመፍጠር አኳያ በኤጀንሲ የጋጠመው የሂንፃ መሳንጠቅ በሠራተኛው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳይኖረው ለማድረግ በጊዜያዊነት ቀደም ሲል በጥቁር አንበሳ ሆስፕታል የተወሰደውን ሕንፃ በአጭር ጊዜ ውስጥ በማስመለስ ሙሉውን ሰረተኛ ወደዚያ በማዘወር ችግሩን በዘለቄታ ከመፍታት አኳያ ከመንግስት ጋር በመነጋገር ዘመን ተሻጋሪ ሂንፃ ለማስገንባት በተቀደው ዕቅድ መሰረት እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በመሆኑም በሁለተኛው የእድገትና ተራንስፎርሜሽን ዘመን ቦሌ በሚገኘው በኤጀንሲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ጥራቱን የጠበቀና ዘመናዊ የአጀንሲው ዋና

መ/ቤት ህንጻ ለማስገንበት ከመንግስት በተፈቀደው መሰረት በ2010 የመሰረተ ድንጋይ ተቀምጦ በ2012 የግንባታው ስራ ተጀምሮዋል፡፡

የግብአት ችግሮችን ከመፈታት አንጻር ከልማት አጋሮች ሀብት በማፈላላግ እና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ በተባባሩት መንግስታት በአፊርካ የልማት ባንክ በኮሪያ ዓለምአቀፍ የትበብር ኤጀንሲ ከፍተኛ አቅም ያለቸው ኮምፒተሮችን፣ ላፕቶፖችን እንዲሁም ለመስክ ስራ ከፍተኛ አስታውጽኦ እያበረከቱ የሚገኙትን ተሽከሪካሪዎች ግዥ ማከናወን ተችሎዋል፡፡ ለአብነትም በዕቅዱ ዘመን ብቻ 21 ተሽከሪካሪዎችን መግዛት ተችሎዋል፡፡

የህዝብ ክንፍ አፈጻጸም ሁኔታኤጀንሰው ከወቅት ትንበያ ጋር በማቀናጀት በአመት ሶሰት ጊዜ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን ሳይቋረጥ በየግዜው ከአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ጋር መደረክ በመፍጠር በአፈፃፀም ሂደት የታዩትን ክፍተቶች ለቀጣይ የህዝብ መድረክ የተሻለ አፈፃፀም ይዞ ከመቅረብ አንፃር ተጨባጭ ውጤትና በርካታ ልምዶች የተገኙበት መደረክ በተሟላ መልኩ ተከሂዶዋል፡፡

በኤጀንሲው የሪፎርምና ልማታዊ መልካም አስተዳደር የማስፈን ስራዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት አሰጣጥን ከ70 % ወደ 75 % የማሳደግ ግብ በተጠለው መሰረት ተከናውኖዋል፡፡



ምስል 24 የበሌ የሚቲዎሮሎጂ ዘመናዊ ህንፃ የማስገንባት ሂደት

### 3.6. የዓለም አቀፍ ትብብር እና ግንኙነት ስራዎች

ሀገራት የተበበሩት መንግስታት ድርጅቶችን ጨምሮ እርስ በራሳቸው በትብብር ላይ የተመሰረተ በማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና በፖለቲካዊ መስኮች አለምአቀፋዊ፣ አህጉራዊ እና ቀጠናዊ ግንኙነት ያደርጋሉ፡፡ በሚቲዎሮሎጂ መስክ ያለው ዓለም አቀፍ ትብብር ወደ 137 ዓመታት አካባቢ እንደሚጠጋ የዓለም ሚቲዎሮሎጂ ታሪክ ያመለክታል፡፡ ለዚህም ዋነኛ መንስኤ የአየር ጠባይ በአገሮች ድንበር የሚወሰን ሳይሆን፣ የራሱ የሆነ የተፈጥሮ ሕግጋት ስላለዉና በአንድ አካባቢ የደረሰው የአየር ሁኔታ ና ጠባይ በሌላ አካባቢ ካሉት የከባቢ አየር ክስተቶች ጋር የተዛመደ በመሆኑ፣ በመረጃ ልውውጥ እንዲሁም ብዙ አገሮችን ሊነኩ የሚችሉ የአካባቢ አየር ክስተቶችን በመከታተል ዓለም አቀፋዊ ትብብር አስፈላጊ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያን ጨምሮ በርከታ ሀገራት የዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት አባል በመሆን አሰፈለጊውን የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ለሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መሻሻል አስተውጽኦ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ከዚህም በመነሰት ብሄራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጄንሲ በአዋጅ ስቋቋም ከተሰጡት ተግበርና ኃለፊነት አንዱ ኢትዮጵያ በገባችው ዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ልውውጥን ማካሄድ ተግባር አንዱ በመሆኑ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን አቅድ ዘመን ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ስሰራ ቆይቶዋል፡፡

በዚህም መሰረት በለፉት እድገትና ትራንስፎርሜሽን አቅድ ዘመን ውስጥ የኤጄንሲውን የአገልግሎት አሰጣጥን የሚያሻሽሉ በሚቲዎሮሎጂ መሰረተልማት ዝርጋታ፣ በግብአት አቅርቦት፣ በስልጠና እና ክህሎት እንዲሁም በአቅምግንባታ እና የልምድ ለውውጦች መስክ በርካታ ዓለም አቀፍ ትብብሮች ተከሂዶዋል፡፡











- ሀገራችን ለመቀመጫነት ከተመረጠች ብኋላ ከኢ.ፌዴሪ ርዕሰብሔር ጋር የተደረጉ ምክክሮች የቢሮ ርክክብና ስብሰባ
- በዓለም የሚቲዎሮሎጂ ድርጅት በኩል ለጽፈት ቤቱ መቀመጫነት በዕጩነት ወደተወዳደሩ ሀገራት በመንቀሳቀስ ያሉትን መሠረተ ልማትና ሌሎች ጉዳዮችን እንዲገመግሙ የተላኩ ኮሚቴዎች

### 3.6.1. ከሀገራት ጋር የተደረጉ የሁለትዮሽ ትብብሮች

ከሀገራት ጋር የተደረጉ የሁለትዮሽ ትብብሮችን በተመለከተ በለፉት በእድገትና ትራንስፎርሜሽን አቅድ ዘመን ውስጥ ከኮረያ ሚቲዎሮሎጂ አስተዳዳር፣ ከቻይና ሚቲዎሮሎጂ አስተዳደር፣ ከፊንላንድ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲዩቲዩት፣ ከቱርክ መንግሰት የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት፣ ከዩኬ ሚቲዎሮሎጂ ጽ/ቤት የመሳሰሉት ጋር የተደረጉ ትብብሮች ለኤጀንሲው አገልግሎት መሻሻል እና መጠነከር ከፍተኛ አስተውጽኦ አድረጓል፡፡ በዚህም መሰረት ከኮሪያ ሚቲዎሮሎጂ አስተዳዳር ጋር በነበረው ግንኙነት የአጀንሲው ከፍተኛ እና መካከለኛ አመራር እንዲሁም ባለሙያዎች ስልጠናና የልምድ ለውውጥ እንዲያገኙ ተደርጎዋል፡፡ ከኮረያ ሚቲዎሮሎጂ አስተዳዳር እና ከኮሪያ ዓለም አቀፍ ትብብር ኤጀንሲ ጋር በተደረገው ስምምነት የአራት ሚሊዮን ዶላር ፕሮጀክት ስምምነት በመፈራረም ሃያ አውቶማቲክ የሚቲዎሮሎጂ እና የሃይድሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያ ተከላ ማከናወን ፣ በሚቲዎሮሎጂ መረጃ አሰበሰብ፣ በአጭር፣ መካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ትንበያ አሰጣጥ ዙሪያ እንዲሁም የጎርፍ እና የድርቅ ቅድሚያ

ማስጠንቀቂያ አገልግሎት ዙሪያ በኮሪያ እና በሀገር ውስጥ በርካታ ስልጠናዎች ተሰጥቶዋል፡፡ ለሁለት ሴት ባለሙያዎች በውሃን የሴቶች ዩንቨርስቲ የሁለተኛ ዲግሪ ዕድል እንዲያገኙ ተደርጎ ትምህርተቸውን አጠናቆዋል፡፡ በሚቲዎሮሎጂ እና ሀይድሮሎጂ የተቀናጀ አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚያገለግሉ መሰረተልማት ተዘርግቶዋል ፡፡ የየኤጄንሲውን የግብአት ችግር ለመፌታት በፕሮጀክቱ የሚደገፍ የሁለት ተሽከርካሪ ግዥ ተፈጽሞዋል፡፡

ከቻይና ሚቲዎሮሎጂ አስተዳደር ጋር የነበረው ግንኙነት የአጀንሲው ከፍተኛ እና መካከለኛ አመራር እንዲሁም በለሙያዎች በርካታ የአጭር ጊዜ ስልጠናና የልምድ ለውውጥ እንዲያገኙ ተደርጎዋል፡፡ ከረዥም ጊዜ ስልጠና አኳያ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በኒያንዣንግ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዩንቨርስቲ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን ትምህርት ያጠናቀቁ አምስት፣ በመከተተል ላይ የሚገኙ ሁለት በለሙያዎች እና የሶስተኛ ዲገሪውን በመከታተል ላይ የሚገኝ አንድ በለሙያ በድምሩ ዘጠኝ የአጀንሲው በለሙያዎች የትምህርት ዕድል አግኝቶዋል፡

ከፊንላንድ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲዩቲዩት ጋር የነበረው ግንኙነት የአጀንሲው ከፍተኛ እና መካከለኛ አመራር እንዲሁም በለሙያዎች ስልጠናና የልምድ ለውውጥ እንዲያገኙ ተደርጎዋል፡፡










ምስል 26 ዓለም አቀፍ መድረኮችና ግንኙነቶች በከፊል

ብሄራዊ የሚቲዎሮሎጂ አጀንሲ፣ የፊንላንድ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲዩቲዩት እና ፊንላንድ ከሚገኘው ቫይዛላ ኩባንያ ጋር በሰው ሀይል ስልጠና አቅም ግንባታ እና በዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ መሰረተልማት አውታር ዝርጋታ እንዲሁም በሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት አሰጠጥ ዙሪያ የሚያተኩር አቅም ግንባታን አስመልክቶ የሶስትዮሽ የስራ ስምምነት ተፈራርመናል፡፡ ለአቅም ግንባታ፣ ለሶስት የአየር ሁኔታ መከታተያ ራዳር ጣቢያ ፣ የአምስት መብረቅ መከላከያ ጣቢያ ተከላ ፣ ለአየር ብክለት መከታተያ ጣቢያ፣ ለዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት አሰጠጥ የሚያገለግል (የsmart met Technology) ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል የአስራ ሶስት ዩሮ ከወለድ ነጻ የብድር ስምምነት ሰነድ ተዘጋጅቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር ተልኮዋል፡፡

ከቱርክ መንግሰት የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት፣ ከዩኬ ሚቲዎሮሎጂ ጽ/ቤት ጋር የተደረጉ ትብብሮች አስራ አንድ በአጀንሲው ምክትል ዋና ዳይሬክተር የሚመራ የመካከለኛ አመራር በቱርክ መንግሰት የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት በመገኘት ለአንድ ሳምንት የዘለቀ የልምድ ለውውጥ እንዲያገኙ ተደርጎዋል፡፡




**ምስል 27 ዓላም አቀፋዊ ትብብሮች**

ከአጀንሲው፣ ከውሃ መስኖና ኢነርጅ እና ከብሔራዊ የአደጋ ስጋት አመራር የተወጣጣ በድምሩ አስራ ስምንት የባለሙያዎች ቡድን በቱርክ መንግሰት

የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት በመገኘት ለሁለት ሳምንት የዘለቀ የልምድ ለውውጥ እና የስራ ላይ ስልጠና አግኝቶዋል፡፡ ከዩኬ ሚቲዎሮሎጂ ጽ/ቤት (UK Met office) ጋር በፕሮጀክቶች እና በሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሁለትዮሽ የትብብር ስምምነት በመፈራረም የስልጠና ድጋፍ ተደርጎልናል፡፡

### 3.6.2. ከልማት አጋሮች ጋር የተደረጉ የብዘሀ ዘርፍ (Multilateral cooperation) ትብብሮች

GEF በተበለው በተባበሩት የልማት ድርጅቶች ፕሮግራም (UNDP) የሚደገፍ ከሶስት ተቋማት ማላትም ከውሀ መስኖና ኢነርጂ፣ ከብሄራዊ የአደጋ ስጋት አመራር ጋር በጣምራ በአራት ነጥብ አምሰት ሚሊዮን ዶላር የሚተገበር ፕሮጀክት በለፉት ሁለት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን ለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስራ ተግበር ላይ ውሎዋል፡፡ በዚህም ፕሮጀክት በርካታ የኤጀንሲውን የአቅም ግንባታ ስራ በማከናወን የግብአትና ክህሎት ችግሮችን ለመፍታት ተችሎዋል፡፡ ለአብነትም ኤጀንሲው ያለበትን የግብአት ችግር ለመፍታት የስምንት ተሽከርካር ግዥ ተፈጽሞዋል፡፡









**ምስል 28 ከተለያዩ የልማት አጋሮች ጋር የተደረጉ ውይይቶች**

በዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት እና በአይሪሽ ድጋፍ በአነስተኛ ማሳ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ የምክር አገልግት በመስጠት ምርትናምርታማነት እንዲያድግ በትግራይ እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ክልሎች በአራት መቶ ሺህ ዩሮ በሁለት ዙር ተግባራዊ ሆኖዋል፡፡

የአፍርካ ልመት ባንክ በመጀመሪያው ዙር እና በሁለተኛው ዙር ክሊምዴቭ በሚበለው ፕሮገራም የአንድ ሚሊዮን ዮሮ ድጋፍ በማድረግ የግብአትና ክህሎት ችግሮችን ለመፍታት ተችሎዋል፡ ከኮሪያ ዓለም አቀፍ ትብብር ኤጀንሲ ጋር በተደረገው ስምምነት የአራት ሚሊዮን ዶላር ፕሮጀክት ስምምነት በመፈራረም የአጀንሲውን የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል የግብአትና ክህሎት ችግሮችን ለመፍታት ተችሎዋል፡፡

3.6.3. አህጉራዊ እና ቀጠናዊ የትብብር መስኮችን በተመለከተ

ሀገራችን የኢጋድ አበል እና የወቅቱ የኢጋድ ሊቀመንበር በመሆኗ አጀንሲው ከኢጋድ የአየር ጠባይ ትንበያ እና ትግበራ ማዕከል ጋር በቅንጅት እየሰራን እንገኛለን ፡፡ በለፉት ሁለት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመንም የማዕከሉ የቦርድ ሰብሰቢ በመሆን የግንባር ቀደምትነት ሚና ተጫውተናል፡፡ የሚሰጠውን የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት በቀጠናው ደረጃ የተነበበ እንዲሆን የተለያዩ አቅም ግንባታ ስራዎች በተላይም የወቅት ትንበያ ከመሰጠቱ በፊት በየሶስት ወሩ (pre Climate Outlook Forum Capacity Building Training workshop) ስልጠና ላይ በለሙያዎችን በማሰተፍ የአቅም ግንባታ ስራዎች ተከናውኖዋል፡፡ የኤጀንሲው ዋና ዳይረክተር የቦርድ ሊቀመንበር የሆኑበት የአፊርካ ሚቲዎሮሎጂ ትግበራና ልማት ውሰጥ በሙሉ አቅም በመሰተፍ የመሪነት ሚናችንን በመወጣት አህጉራዊ ግዴታችንን በመወጣት ላይ እንገኛለን፡፡

ከአሜሪካ National Oceanic and Atmospheric Adminstration —NOAA) ጋር በነበረን መልካም ግንኙነት የልምድ ለውውጥ እና በሁለተኛው የዕድገትና ተራንስፎርሜሽን ዘመን ለአምሰት የኤጀንሲው በለሙያዎች እያንደንደቸው የአራት ወራት አሜሪካን ሀገር በሚገኘው National Oceanic and Atmospheric Adminstration —NOAA ብቃት ያለውን የስራ ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጎዋል፡፡



**ምስል 29 የተለያዩ አህጉር ዓቀፍ ዎርክሾፕና የአንድነት ፓርክ ጉብኝት**

### 3.6.4. ከዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት ጋር የተደረጉ ትብብሮች

ባለፉት ሁለት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን የአጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት የኢትዮጵያ ቋሚ ተጠሪ እና የድርጅቱ ስራ አስፈጻሚ ምክርቤት አባል ሆኖ በመገልገል በዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት አለምአቀፋዊ ግዴታችንን በመወጠት ላይ እንገኛለን ፡፡ ኤጀንሲው የተባበሩት በየነመንግስታት የአየር ጠባይ ለውጥ ፓናል ፎካል ፖይንት በመሆን ከማገልገላችን በተጨማሪ የኤጀንሲው ባልደረባ የነበሩት ዶ/ር ዲሪባ ቆሪቻ ሀገራችንን በመወከል እ.አ.አ. ከ2016 ጀምሮ የተባበሩት በየነመንግስታት የአየር ጠባይ ለውጥ ፓናል የቢሮ አባል እና የወረኪንግ ግሩፕ ሶስት 3ኛ ምክትል ሊቀመንበር (IPCC-Working Group III Third vice chaire and Bearou Member) በመሆን ተመርጦ እያገለገለ ይገኛል፡፡





**ምስል 30 የዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት የአፍርካ አህጉር ጽ/ቤትን በኢትዮጵያ የማስጀመር ሂደት**

በኣለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት የአፍርካ አህጉር ጽ/ቤትን ጄኔቫ ከሚገኘው የዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት ጽ/ቤት ወደ አፊርካ እንዲዛወር በኮንገረንሱ በተወሰነው መሰረት የድርጅቱን የአፍርካ አህጉር ጽ/ቤትን ተቀብሎ ለማስተናገድ ፍላጎት ካሳዩት አስር ሀገራት ጋር በመወዳደር በተደረገው ጠንካራ ዲፕሎማሲ ጽ/ቤቱ ወደ አዲስ አባባ እንድዘወር ተወስኖዋል፡፡ በዚሁ መሰረት

ህምሌ 4 ቀን 2010 ከኢፌዲሪ መንግሰት ጋር (የHost Country Agreement-HCA) የስምምነት ሰነድ ተፈራርሞዋል፡፡ የስምምነት ፊርማውን ተከትሎ ጥቅምት 2012 የዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት ዋና ፀሐፊ በተገኙበት በጊዜያዊነት በተዘጋጀው የአጀንሲው ግቢ ውስጥ በዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት የአፍርካ አህጉር ጽ/ቤቱን በመረከብ በይፋ ስራ ማስጀመር ተችሎዋል፡፡

## 3.7. በጀትና ፋይናንስ አፈጻጸም





Figure 31 በሁለተኛው ዕትዕ ዓመታት ለኤጀንሲው የተፈቀደ በጀት

## 3.8. የክትትል እና ግምገማ ስርአት፣ ጥንካሬዎች ድክመቶች እና ችግሮች

### 3.8.1. የእቅዱ የክትትል እና ግምገማ ስርአት፣

- ❖ የክትትልና ግምገማ ሥራ በየደረጃው ማከሄድ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶዋል፡፡
- ❖ የእቅድ አፈጻጸሙ በየአመቱ ያለበት ደረጃ ስገመገም ቆይቶዋል፡፡
- ❖ በሪፖርት፣ በአካላዊ ግምገማ እና በሱፐርቪዥን መልክ የክትትልና ግምገማ ተካሂዷል፡፡

### 3.8.2. በእቅድ ትግበራው ሂደት የነበሩ ጥንካሬዎች፣

- ❖ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችና ሲስተሞች ተጠቃሚ መሆን መቻሉ
- ❖ በተሰጠው የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ አገልግሎት የትንበያው ተዐማኒነት መጨመሩ
- ❖ የማህበረሰቡን ለሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ መቻሉ

- ❖ የሰለጠነ የስው ኃይል ለማበራከት የአቅም ግንባታ ሥራዎች መሰራት
- ❖ ከልማት አጋሮች ጋር የተፈጠረው መልካም ትብብር መጠናከሩና በዘርፉ የተገኘው ሀብት ለዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ መሣሪያዎች ማስፋፍያና ለአቅም ግንባታ አስተዋፆ ማድረጉ
- ❖ ከሀገራት፣ አህገራዊ፣ ቀጠናዊ እና ዓለም አቀፋዊ ትብብሮች በእጅጉ መጠነከር
- ❖ በጥናትና ምርምር ተሳትፎ ማድረግ እና በርካታ ምርምሮች ለህትመት ማባቃት መቻሉ በጥንካሬ የሚታዩ ናቸው፡፡

3.8.3. በእቅድ ትግበራው ሂደት የነበሩ ድክመት

- ❖ የአንዳንድ የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ከታቀደው በላይ መጓተቱ
- ❖ የኤጀንሲው የእቅድ ፣ክትትልና ግምገማ ስርዓት ጠንካራ አለመሆን ፣
- ❖ በታችኛው የአስተዳደር እርካን ደረጃ የተቀናጀ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል አደረጃጀት አለመፍጠር እና ለታችኛው የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ አለመሆን፣
- ❖ ቀልጣፋ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎትን ለመስጠት የሚያስችልየኢንፍርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ውስንነት

3.8.4. ያጋጠሙ ችግሮች

- ❖ በሚቲዎሮሎጂ ሙያ የሰለጠነና ልምድ ያለው የሰዉ ሀይል ከገበያ ተሟልቶ አለመገኘት፣
- ❖ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ላይ የሚፈፀም ስርቆት፣
- ❖ የቴሌኮምና የኤሌክትሪክ አገልግሎት ሽፋን የተሟላ አለመሆን እና መቆራረጥ
- ❖ ለሚቲዎሮሎጂ መሣሪያዎች ግዥ የውጭ ምንዛሪ መናር፣ በተፈለገው ጊዜ አይነትና መጠን አለመገኘት፣
- ❖ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ለማቋቋም ወካይ ቦታ እና የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ አለማግኘት፣
- ❖ የምርምር አቅምና ልምድ አናሳ መሆን እና በጊዜ አለመከወን

## በሀገር መሪ ደረጃ የተካሄደ የአየር ጠባይ ምክክር መድረክ



የኢፌድሪ ፕሬዘደንት
ወ/ሮ ሳህለወርቅ ዘውዴ





የፊላንድ ሪፐብሊክ ፕረዝደንት
ሱይመን ተስቫለን





የአገልግሎት ማዕከላትን የማጠናከር አካል የሆነው እንዲሁም ምቹ የሥራ ከባቢን በመፍጠር አሠራርን ለማዘመንና አገልግሎቱን ለማሻሻል የሚያግዝ ህንፃን በምስራቅና መካከለኛ ኦሮሚያ አገልግሎት ማዕከል ለመገንባት መሠረት ድንጋ ሲቀመጥ





አድራሻ፡- ስልክ 0116615779/5512299
ፋክስ፡-0115517066/6625292
ፖ.ሳ.ቁ 1090
ኢሜይል፡-nmsa@ethionet.et; nmsa.mafd@ethionet.et
ዌብሳይት፡ www.ethiomet.gov.et:www.meteo-ethiopia.net



Designed & Printed by: Master Print +251 116 29 87 77